# ከወልወል

እስከ

# ማይጨው

ከብርሃኑ ድንቄ።

ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ ዘመን መንግሥቱ
ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

አዲስ አበባ መስከረም ፳፮ ቀን ፲፱፻፵፪ ዓ.ም
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

# ከወልወል

## እስከ

# ማይጨው ፡

ከብርሃኑ ድንቄ።

ተኅትመ ዝንቱ መጽሐፍ በ፳ ዘመን መንግሥቱ
ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

አዲስ አበባ መስከረም ፳፪ ቀን ፲፱፻፶፪ ዓ.ም
በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ።

**በምክርና በተግሣፅ ላሳደጉኝ ለአባቴ**

**ለሊቀ ጠበብት ድንቄ መታሰቢያ።**

# መቅድም።

ይህ አጭር ጽሑፍ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ከደረሰው ከወልወል ግጭት ጀምሮ እስከ ማይጨው ጦርነት መጨረሻ ድረስ የተደረገውን አንዳንድ ነገር ያስታውሰናል። የቃሉ አሰካከና የታሪኩ አገላለጥ ገር ስለሆነ እንዲያነቡት አደራ የሚባሉት ከፍተኛ፣ ጽሑፍ ለማንበብ ገና በመደራጀት ላይ ያሉ ወጣቶች ናቸው።

ድርጊቱ ትውልድ ባላሳለፈ ዘመን ውስጥ የተፈጸመ ስለሆነ፣ ምናልባት ብርቅ አናደርገውም ይሆናል። ግን ለተከታዩ ትውልድ ማስትወሻ እንዲሆነው ተስፋ አለን

ደራሲው።

## ማውጫ

የጦርነቱ አነሣሥ ፡ ........ 5
የጦር ወታደር ስብሰባ። ........ 14
የዘማቾች ድርጅት። ........ 21
የቃፊሮች ተከላካይነት ........ 30
ግርማዊ ን ነ ወደ ጦሩ ግንባር ለመሄድ ያደረጉት ድርጅት። ........ 37
ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጅጅጋን ስለ መጐብኘታቸው። ........ 42
ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሰሜን ግንባር ስለ መጓዛቸው። ........ 46
የደቡብ ጦርነት። ........ 49
አዋጅ። ........ 54
የሲዳሞ የጦር ሠራዊት። ........ 54
ግርማዊነታቸው በደሴ። ........ 57
የልዑላን ራስ ካሣና ራስ ሥዩም ፡ የራስ ሙሉጌታም ፕላን። ........ 63
የባዶሊዮ ፕላን። ........ 66
የተንቤን የመጀመሪያ ጦርነት። ........ 70
የአምባራዳም ጦርነት። ........ 73
የግርማዊነታቸው ከደሴ መነሣት። ........ 78
የሺሬ ጦርነት። ........ 81
፪ኛው የተንቤን ጦርነት። ........ 85
የጀነጋብ ጦርነት። ........ 90
የማይጨው ጦርነት። ........ 96
የጦር ሠራዊቱ መፈታት። ........ 104

# ምዕራፍ ፭።

## የጦርነቱ አነሣሥ ፡

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መካከል ስለተደረገው ጦርነት መንሥኤ የሆነው የወልወል ግጭት ነው እየተባለ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ይነገራል። ነገር ግን በእውነተኛው አስተያየት የተገመተ እንደሆነ የወልወል ግጭት ምክንያት ከመሆኑ በቀር የጦርነት መንሥኤ ነው ሊባል ከቶ አይገባም። እንዲሁም አንዳንዶቹ ደግሞ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም ዓድዋ ላይ ስለተደረገው ድል መመታት ብድር ለመክፈል ወይም ለመበቀል የሆነ ነው ሲሉ ይተርካሉ።

ስለዚህ ጀኔእራል ግራዚያኒ ገና ጦርነቱ ሳይነሣ በጥር ወር ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በድንገት ወደ ሮማ ተጠርቶ የሶማሌ ገዥነትና የጦር ኃይል አዛዥነት በተሰጠው ጊዜ ወደዚሁ አውራጃ ሲጓዝ የተመለከተውንና የጦርነቱን ሁኔታ በሚተረክበት «የደቡብ ግምባር» በሚለው ድርሰቱ (ገጽ ፳፫) እንዲህ ይላል።

«የዓድዋ ጦርነት የተደረገበት የዓመት በዓል ፡ ልክ በሚታወስበት ቀን እምጽዋ ላይ ከበርከብ እንድንወርድ ዕድል ፈቀደ። ይህ አጋጣሚ ነገር የመልካም ምልክት ነው ብዬ እገምተዋለሁ። መስተበቅል ለመሆን እችል ዘንድ እግዚአብሔር ሕሊናዬንና ልቤን፣ ክንዴንም ያበረታ»

ከዚህም አያይዞ በ፳፺ኛው ገጽ እንዲህ ይላል።

«በዓድዋ ሰለወደቁት ሰዎች የቆመውን ሐውልት ለማየት ወደ ዓዲ ኳላ ባንድነት መንገዳችንን ቀጠልን። በሩቅ ጥንድ አውሬዎች መስለው በሚታዩበት በዓድዋ ተራራዎች ላይ ካራንዛ የተላኩ አዳኝ አውሮፕላኖች ሲያንዣብቡና ወደዚያው ሲያመሩ በምድር ቤቱ ውስጥ ለአንድ ደቂቃ ዝምታ (ጸጥታ) አደረግን። እርጥብና ቀዝቃዛ በሆነችው መቃብር ቤት ገና

ብድራቷ ያልተከፈላት የሞት ስቅጥጥታ ተሰማኝ። ይጀመር ዘንድ ስለሚዘጋጀው ጉዳይ ራሴን አሳልፌ ለመስጠት ማልኩ። የትሩቶና የሌሎችም እዚያ የተኙት ጀግኖች አጥንት ስላነዋወጻቸው ድንጋዮቹ የሚንቀጠቀጡ መሰሉን»

ከዚህ እብላይ የጠቀስነው የግራዚያኒ ጽሑፍ ያንባቢው አሳብ ጦርነቱን ያነሣሣው የዓድዋን ቁርሾ ብድር የመመለስ ሁኔታ ነው ወደ ማለት እንዲያዘነብል የሚገፋፋ ነው።

ይሁን እንጂ ብድር መክፈል ወይም መበቀል የተባለው ሁለት ዓይነት ትርጓሜ ስለሚሰጥ አሁን ለምናነጣጥረው ግብ አንደኛው ትርጓሜ ሳይመሳሰለው አይቀርም። ይኸውም በ፲፱፻፹፰ ዓ.ም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የጦርነት መንሥኤ የሆነው የውጫሌ ላይ የተደረገው ውል በተለይም ፲፯ኛው አንቀጽ በመሆኑ ምንም እንኳ በዚያን ጊዜ እንደዛሬው የቅኝነት ጉዳይ ባይነሣ በጥገኝነት ተሸፍኖ የተሠራ የዜግነት አሳብ የተመሠረተበት ስለነበረና ያውም በኢትዮጵያ ጀግኖች ትጋት በዓድዋ ላይ ሰለ ተሠረዘ በ፲፱፻፷፰ ዓ.ም በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል የጦርነት መንሥኤ የሆነው የዓድዋ ድል መመታት ብድር ለመክፈል ነው ሲባል ይስማማል። ይኸውም ስለወታደር ጀግንነት ክብር ሳይሆን የቅኝ አገርን ጥቅም ለማስፋፋት ነው የተባለ እንደሆነ ነው።

ወልወል በሐረር ግዛት በውጋዴን ውስጥ የምትገኝ የኢትዮጵያ መሬት ናት። በ፲፱፻፷ ዓ.ም ኢትዮጵያና እንግሊዝ በሱማሌ አገር በኩል ያለውን ወሰናቸውን በመሬቱ ላይ እያመለከቱ ለመከለል ተስማምተው ወሰን ተካላዮች ላኩ። የክልሉም ስምምነት ሥራ በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም ግንቦት ፳፰ ቀን በተደረገው ውል መሠረት ነበር። በዚያን ጊዜ የወሰኑ መስመሮች ከተመለከቱ በኋላ የእንግሊዝ መልክተኞች የግጦሹን ስፍራ በ፪ቱም ወገን እየዞርን እንጐብኘው ሲሉ ጥያቄ አቀረቡ። ቀጥሎም በእንግሊዝ ግዛት በኩል እስከ ባሕር ድረስ እንኳ እየተጐዳኙ ቢያግጡ ግድ የለንም ሲሉ ምክንያቱን

አሳጠሩ። ይህን ማለታቸው ጠቃሚ የግጦሽ ስፍራ የሚገኘው በኢትዮጵያ ግዛት በኩል መሆኑ ያውቁ ስለነበረ ነው።

የኢትዮጵያ መልክተኞች የግጦሹን ጉዳይ ከየጐሣው በመጠየቅና በካርታው ላይ በመመልከት እንዲፈጸም እንጂ በየስፍራው በመዞር ለጊዜው አልፈቀዱም። ምክንያቱም የግጦሽ ሥፍራ የሚባለው ከወልወል በታች ባለው በጋለዱ ወረዳና በኢጣልያኖች ወሰን አጠገብ ያለው ሁሉ ስለሆነ የኢጣልያኖች አምባጓሮኝነት በመጠርጠር ነበር። ዳሩ ግን የእንግሊዝ መልእክተኞች መላልሰው ከመጠየቃቸው የተነሣ በኅዳር ፲ ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ከጅጅጋ ተነሥተው ወደ ወጋዴን ተጓዙ። እንዲሁም ከ፱ ወር በፊት የኢሳ ወምበዴዎች በወሰን ተካላዮች ላይ አድርገውት የነበረው አደጋ ትምህርት ሆኖ የጉርሱመ አበጋዝ ፊታውራሪ ዓለማየሁና የጅጅጋው አበጋዝ ፊታውራሪ ሽፈራ ወሰን ተከላዮቹን እንዲከተሉና እንዲጠብቁ ታዘዙ።

ወሰን ተካላዮቹ በደጋሀቡርና በአዋሬ በገሮና በአዶ በኩል አልፈው ኅዳር ፲፬ ቀን ወልወል ላይ ሲደርሱ የኢጣልያ ባንዶች በድንገት ከዚያው ተገኙ። እነሱም ሰፈር ለመከልከል አስበው አምባጓሮ አብቅለው ስለነበረ ጊዜው ሳይዳረስ ቀረ እንጂ ግጭቱ በዚሁ ቀን በተፈጸመ ነበር።

ወልወል ከ፪፻ የሚበልጥ የውሃ ጉድጓድ ያለበት ሥፍራ ነው። የያንዳንዱ ጉድጓድ ርዝመቱ እስከ መቶ ክንድ የሚደርስ ይገኝበታል። እነዚህን ጉድጓዶች ያስቆፈረ ዘርዐ ያዕቆብ የተባለው የሐበሻ ንጉሥ ነው እያሉ ባላገሮቹ ይተርካሉ። እንዲሁም ደግሞ በታችኛው ወጋዴን በዋቢ ሸበሊ ወንዝ ዳርቻ የሚገኙት ጥቋቍር ነገዶች የዚሁ ንጉሥ አሽከሮችና አቢላሞች እንደነበሩ ይነገራል።

ወሰን ተካላዮቹ የወልወል ጸጥታ ደስ የማያሰኝ መሆኑን ከተመለከቱ በኋላ ነገሩን በዲፕሎማሲ መንገድ ለመፈጸም ሲሉ በ፫ኛው ቀን ወደ ኋላ ተመልሰው አዶ ላይ ሰፈሩ። ለጥበቃ የታዘዙት ፊታውራሪ ዓለማየሁና ፊታውራሪ ሽፈራ ግን በወሰን ተካላዮቹ ፈቃድ ከዚያው ከወልወል ቀርተው

ነበርና ፲ ቀን ያህል በሰላም እንደተቀመጡ ኅዳር ፳፮ ቀን ረቡዕ ከእኩለ ቀን በኋላ ኢጣልያኖች በድንገት አደጋ ጥለው ውጊያ ሆነ። ኢጣልያኖች በነገሩ አስበው ተነስተውበታልና ከላይ በአውሮፕላን ቦምብ ከታች በታንክ ይዋጉ ጀመር።

የኢትዮጵያ ወታደሮች ከምሽቱ እስከ ፱ ሰዓት ድረስ እየተከላከሉ በጀግንነት ከተዋጉ በኋላ በሰልፉ ውስጥ የሞቱትን የፊታውራሪ ዓለማየሁን ሬሳ ይዘው ወደ አዶ ተመለሱ። በዚህ ቀን ከኢትዮጵያ ፡ ወገን የሞቱት ፻፯ ናቸው ተብሎ በመጀመሪያ ተነግሮ ነበር። በኋላ ግን ሞተዋል ከተባሉት ውስጥ ፲፫ ሰዎች መንገድ በመሳሳት ወደ ሌላ ስፍራ ጠፍተው ኑሮ በ፫ኛው ቀን ውጋዴኖች መንገድ እየመሩ ወደ ገራሮ ስላመጧቸው እርግጠኛው ቍጥር ፺፬ ሆነ።

ከጠላትም ወገን ባላምባራስ አሊ ኑር በርሱ ግምባር ብቻ ፴፯ ባንዶች መሞታቸውን ሲያረጋግጥ፣ በሌላው ግምባር ፫ የሚሆኑ ሞተዋል ተብሎ ተነገረ።

ኢጣልያኖች ጦርነት ለማንሣት ከብዙ ጊዜ ሲመኙት የነበረው ምኞት በወልወል ላይ ስለተፈጸመላቸው ኢትዮጵያን ወዲያው ዕለቱን እንደጨበጡ መስሎ ታያቸው። ነገሩም ወደ ዓለም መንግሥታት ማኅበር ተላልፎ ሳለ ኢትዮጵያን አጥፊ ለማስመሰል ከመጣጣራቸው በላይ ክርክሩ በዕርቅ ወይም በፍርድ እንዳይፈጸም ነገሩን በማሰናከል ደከሙበት።

ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት በዓለም መንግሥታት ማኅበር ላይ ያለውን ተስፋ ሳያቋርጥ የውስጥ ድርጅቱን ማከናወንና የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ማድረግ ግዴታ ሆነበት።

በዚያን ጊዜም ጠቡና ዛቻው እየበረከተ በመሄዱ ስለ ድንገተኛ የአሮፕላን አደጋ ጥንቃቄ ከዚህ በታች የተመለከተው ጽሑፍ በተባራሪ ወረቀት ታትሞ እንዲነዛ ተደረገ።

ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ

ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

የጠላት አኤሮፕላን ከተማና በከተማውም ያለውን ሕዝብ፥ በድንገት ደርሶ ቦምብ ጥሎ ለማጥፋትና ለማቃጠል የመጣ እንደሆነ ፡ በዚሁ ምክንያት የከተማው ሕዝብ ጉዳት እንዳያገኘው አስበን ከዚህ ቀጥሎ ፡ ያለውን መጠንቀቂያ የአዲስ አበባ ሕዝብ አውቆት ከአደጋ የሚድንበትን ከዚህ በታች ያለውን ጥንቃቄ ደንብ አድርገን ሰተናል።

ይህም ትእዛዝ በአዲስ አበባ ላሉት ለኮሚሴር ሹማምንቶችና ዋና ዋና የዘበኞች ሹም ፡ ደግሞ ለሰፈር ሹማምንቶች ተሰጥቶ በየሠፈሩ ያለው ሕዝብ እየተሰበሰበና እየተነበበለት እንዲያውቀው አዘናል።

፩ኛ ፡ ከተማ የሚያጠፋ አኤሮፕላን በመጣ ጊዜ ለሕዝብ የሚሰጡት ምልክቶች እነዚህ ናቸው። ፫ ጊዜ መድፍ ይተኰሳል። የመኪናዎች ጩኸት ፡ የቤተ ክርስቲያኖች ደወል ሳያቋርጥ ብዙ ጊዜ እየጮኸ ድምጡን ያሰማል፡

፪ኛ ፡ ይህን በሰማችሁ ጊዜ ቤታችሁን ዘግታችሁ እየለቀቃችሁ አኤሮፕላኑ የሚፈልገው ቤትና የተከማቸ ሰው ስለሆነ በየቤታችሁ አቅራቢያ ቤት ከሌለበት ሥፍራ ደን እየፈለጋችሁ መበታተንና መደበቅ ነው።

፫ኛ ፡ በቤታችሁ አቅራቢያ ደን ባይገኝ በተገለጠውም ሥፍራ ቢሆን እየተራራቃችሁና አንድ ባንድ እየተበታተናችሁ አደጋው እስኪያልፍ ድረስ ጸጥ ብሎ መቆየት ነው።

፬ኛ ፡ አደጋው ባለፈ ጊዜ እንደ ገና ተመልሳችሁ ወደቤታችሁ እንድትገቡ ፮ ጊዜ መድፍ ይተኰሳል ይህን ስትሰሙ በየቤታችሁ ተመልሳችሁ ለመግባት ትችላላችሁ።

፫ኛ ፡ ይህ ጥንቃቄ እንዲለመድና እንዲታወቅ በደህና ጊዜ ይደረጋል፥ ምክንያቱም በሰማችሁ፥ ጊዜ እንደታዘዘው ለማድረግ ተሰናድታችሁ ጠብቁ።

፬ኛ ቤታችሁን ለቃችሁ በምትሔዱበት ፡ ጊዜ በቤታችሁም በናንተም ፡ ላይ ማናቸውም ክፉ ነገር እንዳይደርስብችሁ የከተማ ዘበኞች ከከተማ ሳይወጡ በጥንቃቄ እንዲጠብቁ ታዘዋል።

፭ኛ የጠላት አውሮፕላን የሚያቃጥል ቦምብ ፡ በሚጥልበት ቦታ የእሳቱን አደጋ ለማጥፋት የሚያስፈልገው ጥንቃቄ ተደርጓል።

፮ኛ ከዚህ በቀር አለቆቻችሁና የሰፈር ሹሞቻችሁ የሚያስታውቋችሁን እየተከተላችሁ መሥራት ነው።

፱ኛ ፡ ይህ ከዚህ በላይ ያለው ጥንቃቄ የሚደረገው በከተማም በሰፈርም ላይ ነው። ነሐሴ ፲፰ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም»

የጦርነት ማንሻ ምክንያት ይሆናል የተባለው የወልወል ግጭት አላፊነት፥ የኢጣልያ መንግሥታት እንዳነጣጠረው በኢትዮጵያ ላይ ሳይወድቅ በመቅረቱ ሌላ ሐተታ እንዲፈልግ አደረገው።

ካቀረባቸውም ከብዙዎቹ ሐተታዎች ጥቂቶቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ውሎችን አያከብርም።

፪ኛ ሥልጣኔው ብዙ ዘመን ወደ ኋላ ከመቅረቱ የተነሣ ለመንግሥቱ ትክክል የሆነ የአስተዳደር ደንብ የለውም። እይባርያንም ንግድ ሊያስቀር አልቻለም።

፫ኛ በኢትዮጵያ ግዛት የሚኖሩ የውጭ አገር ሰዎች በየጊዜው የሚደርስባቸው ውርደትና ጭቆና ይህን ያህል ነው ለማለት ግምት የለውም እያለ አስመስሎ በመናገር ለዓለም መንግሥታት ማኅበር የወንጀል ክስ አቀረበ። ይህንን ወንጀል እያጋነነ ከማውራት በላይ በየጊዜው የጦር ወታደር እያበረከተ ወደ ኢትዮጵያ ጠረፍ መላኩ በግልጽ ከመታወቁ የተነሣ የዓለም

መንግሥታት ማኅበር አጥብቆ አሳሰበው። ስለዚህ ጉባኤው በመስከረም ፬ ቀን ፩፱፻፴፭ ዓ.ም (እንደ ኢትዮጵያ አቈጣጠር ነሐሴ ፳፱ ቀን ፩፱፻፳፯ ዓ.ም) በጀኔብ ስብሰባ እንዲደረግና በኢትዮጵያና በኢጣልያ መንግሥት መካከል ያለውን ክርክር እንዲወሰን ቀጠሮ ሰጠ።

በዚሁ ቀን ጉባኤው ተሰብስቦ ሳለ የኢጣልያ መንግሥት ወኪል ከ፩፰፻፹ ዓ.ም ጀምሮ መንግሥቱ ስላለው ግንኙነት የኢትዮጵያን ሁኔታ በማጕደፍ ይጠቃቀስ ጀመረ። እንዲሁም በሰፊው ተናግሮ ሲጨርስ ጉባኤውን ጠቅጥቆ ወጣ። መልስ እንዳይሰማ በንቀትና በትዕቢት ጉባኤውን ጠቅጥቆ ወጣ። ጉባኤውም ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር ቁርጥ አሳብ እንዳደረገች ሲያውቅ ጉዳዩን የአምስቱ መንግሥታት ኮሚቴ እንዲመረምረው ሲል ነገሩ እንዲወዘፍ አደረገ። ምክንያቱም ጃፓን በማንቼሪ ምክንያት ከማኅበሩ እንደወጣች ኢጣልያም በኢትዮጵያ ምክንያት ከማኅበሩ ትወጣና ሁከት ይሆናል በማለት ለመበጥበጥ ነበረ። ይሁን እንጂ በምኞት ነበልባል የተንቀለቀለውን የኢጣልያ ጉራ እንዲያበርደው ተብሎ ኢትዮጵያን አሳልፎ ለመስጠት በተመደበው አሳብ ቢጸና ልዩ አላፊነት ያለውን የመታመኛ ሥርዓት ከንቱ አድርጎ የመቍተር ያህል ይገመታል ሲል ጉባኤው ነገሩን ማመዘን ግድ ሆነበት። ስለዚህ በምንም አኳኋን የኢጣልያን ምኞት ጨቍኖ ለማስቀረት የሚቻልበትን የዘዴ መንገድ ፈለገ። ነገር ግን ኃይልን በማሳየትና በቀጥታው ጎዳና ከሚሆነው በቀር በተዘዋዋሪ የፖለቲካ ስላች ነገሩ ሊፈጸም የማይቻል ሆነ። እንዲሁም ይህ ግልጽ የሆነው አጥቂነት በጉልህ ሊታይ የተገባ ፍርድ ፈጥኖ ባለማግኘቱ ከፍተኛ ኮሚሴር የነበረው ጄኔራል ዲቦኖ የኢትዮጵያን ግዛት ድንበር አልፎ ጦርነቱን እንዲጀመር ትእዛዝ ተላለፈለት።

«ጄኔራል ዲቦኖ ስለ መጀመሪያዎቹ ግጭቶች መዘጋጀት» በሚለው ድርሰቱ እንዳስታወቀው ጦርነቱን ከመጀመሩ አስቀድሞ ቀጥሎ የተመለከተውን ቴሌግራም ለዱቼ አስተላልፎ ነበር።

«የጦርነት ማስታወቂያ ይደረግ እንደሆነ እንዲሁም የተረጋገጠ ሲሆን የጦር ሠራዊቱ ወደፊት እንዲገፋ የሚሰጠው ትእዛዝ በግርማዊነታቸው ፡ ባንተ ወይም በኔ እንደሆነ ፡ በጊዜው ባውቀው መልካም ነው። በዚህ በመጨረሻው አኳኋን በአሥር ቃላት እወስናለሁ።»

ከዚህ በላይ ለተመለከተው ቴሌግራም መሶሊኒ የሰጠው መልስ እንደሚከተለው ነው።

«አንዳች የጦርነት ማስታወቂያ አይኖርም። ንጉሡ በኦፊሲዬል ለጄኔብ ባስታወቁት ጠቅላላ የክተት ሥራ ፊት ፡ የሚዘገይን ነገር ሁሉ በፍጹም መቁረጥ ያስፈልጋል። በ፫ (ሦስት ማለቴ ነው) ጥቅምት ከመጀመሪያዎቹ ሰዓቶች መቃወም (ውጊያ) እንድትጀምር አዝሃለሁ። ፍጠንት ያላትን ማረጋገጥ እጠብቃለሁ።»

ጄኔራል ዲቦኖ ይህን መልስ ከመሶሊኒ እንዳገኘ ወዲያው ፡ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የጦር መኰንኖችና ወታደሮችን ፡ ሰብስቦ ቀጥሎ የተመለከተውን ተናገረ።

የጦር መኰንኖች ፡ የመሬት ፡ የባሕርና የአየር ወታደሮች ፡ ጥቁር ለባሽ አሽከሮች ሆይ ፡

ጠንካራ በሆነ ሥነ ሥርዓትና ዓርዓያ በሚሆን ትዕግሥት እስካሁን ጠበቃችሁ። እነሆ ቀኑ ደረሰ። ድንበሩን ታልፉ ዘንድ ግርማዊነታቸው ይፈቅዳል የጦር ሚኒስትር ቢኔቶ ሙሶሊኒም ይዟችኋል።

እናንተን ለመምራት ክብርና ኩራት እየተሰማኝ በአዛዦች ግምት ፡ በወታደሮች ሞያና ሥርዓት ላይ ፡ ተስፋ ለማድረግ መቻሌን አውቃለሁ። ድካምንና መሥዋዕትን መሆንን መታገሥና ፡ ጦረኛና ብርቱ ለሆነ ጠላት መመከት አለባችሁ። የምናነጣጥራት ድል ማድረግ ከፍ ያለ ዋጋ ይኖራታል። ደግሞም ፋሽስታዊ ለሆነችው አዲሲቱ ኢጣሊያ የተጣራ ድል ይሆንላታል።

በእንደዚህ ያለ ሁናቴ የወረራው አኳኋን ተጀመረና በዚሁ ቀን የኢጣሊያ ወታደሮች መረብን ተሻገሩ። እንዲሁም ወረራውን በማስፋፋት ጥቅምት ፳፭ ቀን አዲግራትን ፡ ጥቅምት ፳፮ አድዋን ያዙ።

ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ስላደረገችው ጦርነት ወታደሮቿ ድንበር አልፈው ወረራውን እንዲቀጥሉ ከማዘዟ በቀር እንደሚገባ የጦርነት ማስታወቂያ አልሰጠችም ነበርና ይህ በድንገት የጀመረችው ወረራ አዲግራትና ኢንቴችን በመያዝ ፡ ከዚያም በኋላ አስፋፍታ በምታደርገው የአዋቂነት ሥራ ፍጹም ጠቧን እስከታረጋግጥ ድረስ በሰሜን ግንባር ያሉት የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት አድዋን ትተው ወደ ኋላ እንንዲያፈገፍጉ መንግሥቱ ትእዛዝ ሰጠ። ይሁን እንጂ የኢጣሊያ ጦር በምድር ከሚያደርገው ወረራ በላይ የዚያኑ ዕለት የአድዋን ከተማ በቦምብ ከመደብደብ አልተወሰነም ነበር።

ይህ የግፍ ጦርነት እየቀጠለ ሳለ የዓለም መንግሥታት ማኅበር መስከረም ፳፭ (ጥቅምት 5) ቀን ኮሚቴ ዲ ሲስ የተባለው በፖርቱ ጊዜ በሙሴ ሞንቴሮ ፕሬዝዳንትነት ነገሩን እንዲመረምር አዘዘ። ነገር ግን የወልወል ግጭት ከተነሣ ከ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ከኅዳር ወር መጨረሻ አንስቶ እስከ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም እስከ መስከረም ፳፫ ቀን ድረስ በሽምግልና ዳኝነት ወይም በቀጥታ ማኅበሩ ላደረገው ጉባኤ የጠፋው ጊዜ ለጠላት መሰናዶ ጠቃሚ ከመሆኑ በላይ እርግጠኛው ጦርነት ከተነሣ በኋላ፣ አጥቂውን በኃይል በመጨቆን ፋንታ በዓለም መንግሥታት ማኅበር አሳቢነት የቆመው ይህ ኮሚቴ የጠላት ወራሪነት የሚወልደውን ፍጻሜ ለመመልከት በሚቻልበት መንገድ ለመጠበቅ ብቻ ምክንያት ከመሆኑ በቀር ለኢትዮጵያ መንግሥት ጠቃሚነት የሌለው መሆኑ ተገምቷል። እንዲያውም እላይ እንደጠቀስነው በጠቅላላው የጀኔብ ጉባኤ ይመለከተው የነበረው በኢትዮጵያ ላይ ያላት ምኞት በማኅበሩ ኃይል ይቀንስና ችግር ይሆናል ወደ ማለት ነበረ ሲሉ ብዙ ጸሐፊዎች ተባብረዋል። እንግዴህ በዚህ አስተያየት ሲገመት የጄኔብ ጉባኤ

አጥቂዎችን ለመቃወም ቅን ከማሰኘት የሚጠነቀቅ ከሆነ ጥንቱን የተመሠረተው ለማናቸው ይሆን? እስከ ማለት የአስተዋዮችን ሕሊና በመመርመር ላይ ጣለው።

## ምዕራፍ ፪።

## የጦር ወታደር ስብሰባ።

የኢጣሊያና የኢትዮጵያ መንግሥታት ፖለቲካዊ ግንኙነት እየከፋ መሄዱ ከተረጋገጠ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ግዛት ጸጥታ ለመጠበቅ በግድ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ በተቻለ መጠን የወታደር ስብሰባ ተጀመረ። ይልቁንም በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በመጀመሪያው ወር ፲፯ኛ ቀን በሚኬብረው የመስቀል የዋዜማ በዓል ዕለት ፡ የግዛቱ ማዕከላዊ ስፍራ በሚሆን በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘውን የጦር ኃይል ብዛትና ሁናቴ ለማሳየት ልዩ ሰልፍ ተደርጎ ነበር። (በዚህ ዕለት በያመቱ የወታደር ሰልፍ ለማሳየት ምንም እንኳ የተለመደ ቢሆን በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የታየው የሠልፍ ሥነ ሥርዓት ከማናቸውም ጊዜ የተለየ ነው ለማለት ያስደፍራል)

በዓሉን ለማክበር የንጉሠ ነገሥቱ ዙፋን የተዘጋጀበት ዛሬ የአፄ ምኒልክ አደባባይ ተብሎ በተሰየመው የአፄ ምኒልክ ሐውልት በሚገኝበት ስፍራ ነበር።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በፈረሰኞች ታጅበው እንደደረሱ ወዲያው በ፱ ሰዓት የተለመደ ጸሎት ሲደርስ ድንገተኛ ዝናም መጣል ጀመረ። ይህም ዝናም የበረዶ ውሽንፍር በመቀላቀል እየበረታ ከመሄዱ የተነሣ በደንብ ከተሰለፈው ወታደር በቀር ፡ ተመልካቹ ሁሉ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ሱቆች መጠለያ እንዲፈልግ አደረገው።

ምንም እንኳ ይህ ዝናም ፋታ ባይሰጥ በየክፍሉና በየረድፉ የተሰለፈው ወታደር በታቀደው መጠን ማለት በመሸለልና በመፎከር ፡ እርምጃን በማቀልጠፍና በማሳመር ይህን በመሳሰለው አኳኋን የጥንታዊውንና የዘመናዊውን የጀግንነት መንፈስ በዓይነት በዓይነት ከማሳየት አልቦዘነም ነበር።

በዚያን ዕለት በወታደርነት መንፈስ ስሜታቸውን ፡ ለመግለጽ ከተሰለፉት ኢትዮጵያውያን ውስጥ ከደንበኛው ክፍል ከጦር ሚኒስቴር ባልደረቦች በቀር የሲቪል አድሚኒትራሲዮን ማለት የጽሕፈት ሚኒስቴር ፡ ያገር ግዛት ሚኒስቴር ፡ የገንዘብ ሚኒስቴር የርሻ ሚኒስቴር የፖስታ ሚኒስቴር ፡ እነዚህንም የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ክፍሎች ነበሩ።

ከዚህ ቀድሞ ኢትዮጵያ በሰላም ጊዜ በወታደር ክፍለ የምታስተዳድረው ሰው እስከ ፫፻ሺ ተገምቷል። በጦርነት ጊዜ ክተት ሲባል ግን እስከ ፩ ሚሊዮን ድረስ ለመሆን ይችላል። የሚተዳደርበትም የድንብ ክፍል ልዩ ልዩ አጠራር አለው። ይሁን እንጅ ከዚህ በላይ ባለው ፓራግራፍ እንዳስታወስነው የጦር ሚኒስቴር በተወሰነ ቁጥር ከሚያስተዳድራቸው በቀር እንደ ዛሬው ጊዜ ሁሉ የጦር ወታደሮችን ጠቅላላ አላፊነት ካለመውሰዱ የተነሣ በልዩ ልዩ፣ አድሚኒስትራሲዮን የሚገኙ ሠራተኞች ደንበኛ አይሁኑ እንጂ ባስፈልገ ጊዜ የወታደር አገልግሎት ለመፈጸም ከደንበኞቹ ትክክል የሆነ ግዴታ ነበረባቸው። ስለሆነ የሰልፍና ለወታደር አስፈላጊ የሚሆን ትምህርት እንደዛሬው ሁሉ በጣም አልተስፋፋም ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት የጦር ወታደሮች በዘመናዊው ሥርዓት ለማሰልጠን የጀመረው በ፲፱፻፲ ዓ.ም ነው። ከዚያም በፊት በ፲፱፻፪ ለማሰልጠን የጀመረው በ፲፱፻፲ ዓ.ም ነው። ከዚያም በፊት በ፲፱፻፪ ዓ.ም ስለ ፖሊስ ሥራ የወታደር ሰልፍ ማስተማር የጀመሩ አቃ ገብሩ የተባሉት የውራጌ ተወላጅ ናቸው። እርሳቸውም ለማስተማር የቻሉበትን አኳኋን በመጠኑ እንደሚከተለው እንተርካለን።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ዶክቶር ትራቬርሲ የሚባል ኢጣልያዊ ሐኪም አገር ለመጎብኘት መጥቶ ሳለ አቃ ገብሩ ከርሱ ጋራ ይከታተሉ ነበርና ወደ ኤርትራ ሲመለስ አብረውት እንዲሄዱ ከአፄ ምኒልክ አስፈቅዶ ወሰዳቸው። በዚያም ለኢጣሊያኖች ወታደር ሆነው በ፬ኛው ባታሊዮን ክፍል ሲያገለግሉ የሹምባሽነት ማዕርግ አገኙ። በአድዋም ጦርነት ጊዜ ከኢጣሊያኖች ጐን ተሰልፈው ነበር ይባላል።

በኋላ ግን ኢጣሊያኖች የኤርትራን ሕዝብ እንደምን ባለ ልዩነትና ዝቅ ባለ አኳኋን እንደሚመለከቱት ማየታቸው የነፃነትን ክብር እንዲገምቱ አደረጋቸው። ስለዚህ ከኢጣሊያኖች ተሰናብተው ወደ አገራቸው ለመመለስ በቁ። ወዲያውም በተመለከቱት መጠን ወታደሮችን ለማሰልጠን ከልጅ ኢያሱ ጠይቀው ለከተማው ፖሊስነት የተመረጡትን ወታደሮች ሰልፍ ማስተማር ጀመሩ። እነዚህም ወታደሮች በሕዝቡ አጠራር ጥርምቡሊ ይባሉ ነበር። ምክንያቱም አስተማሪያቸው አቃ ገብሩ ኢጣሊያኖች ወደ ትሪፖሊ በዘመቱ ጊዜ በወታደርነት አብረው ተሰልፈው ስለ ነበረ ነው።

አቃ ገብሩ የወታደር ማሰልጠንን ሥራ እያስፉ ሳሉ ፡ ልጅ ኢያሱ እርሳቸውን ሽረው ነጋድራስ ኢድልቢ የተባለው የሶርያ ሰው ሾሙባቸው ፡ ነገር ግን በ፲፱፻፱ ዓ.ም መስከረም ፲፯ ቀን ልጅ ኢያሱ ከመንግሥት ሥራ በተወገዱ ጊዜ አቃ ገብሩ ከሹመታቸው ተመልሰው እንደ ገና እንዲያስተምሩ ተፈቀደላቸው።

በዚያን ጊዜም የሰገሌ ዘመቻ ይታሰብ ነበረና ሕዝብ የወታደሮቹን እርምጃ መቀልጠፍና ማማር ሲመለከት እነዚህ ለዓይን አምሮትና ለደስታ ወይም ለፈንጠዝያ ጊዜ ከመሆናቸው በቀር በጦርነት ላይ ሞያ ይሠራሉ ብሎ ተስፋ አላደረገባቸውም ነበር። ይሁን እንጂ የጦርነቱን ገፈት ከመቅመሳቸው በላይ ግንባራቸውን ወደ ኋላቸው ሳይመልሱ በጀግንነት ስለወደቁ ይህ የወታደር ማሠልጠን ሥራ ጠቃሚነት ያለው መሆኑን ለማመዛዘን መልካም አርአያን ትተው አለፉ።

ከዚህም በቀር ከሰገሌ ጦርነት በኋላ በ፲፱፻ ዓ.ም በልዑል አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ትእዛዝ ግራዝማች ገብረ ዮሐንስ የሚባሉ የሸዋ ተወላጅ በቀርሳ ላይ የሐረርን ሰው እየሰበሰቡ ሰልፍ እንዲያስተምሩ ተላኩ። እኒህም ሰው የወታደርነት ትምህርት የተማሩት በእግሊዝ የቅኝ አገር በኬንያ ነው ይባላል።

ከዚህ በላይ የጠቀስነው የአቃ ገብሩና የግራዝማች ገብረ ዮሐንስ አስተማሪነት በወታደር መንፈስ ላይ የተለመውን ዘመናዊ ሥልጣኔ አስፋፍቶ ለመሥራት እንዲቻል ፡ ልዑል አልጋ ወራሽ አውሮፓን ጐብኝተው ከተመለሱ በኋላ በ፲፱፻፲፱ ዓ.ም የቤልጅግና የሱዌድን ኦፊሰሮች ቀጥረው የጦር ትምህርት ቤት በደንብ ለማቋቋም ተቻለ። ይሁን እንጂ በትምህርት ቤቱ የኢትዮጵያን መንግሥት የጦር ሠራዊት በአንድ ጊዜ ለማሰልጠን የማይቻል ስለ ነበረ በአዲሱ ደንብ ከሚተዳደረው ይልቅ በቀድሞው ልማድ ውስጥ የነበረው ወታደር ቁጥር እጅግ ብዙ ነበር። ከዚሁም አብዛኛው በአውራጃ ገዥዎች ውስጥ ይተዳደር የነበረው የቁጥር ጦር ነው።

ከእንግዲህ ወደቀደመው ፡ አሳባችን እነመለስ።

መስከረም ፲፮ ቀን (የደመራ ዕለት) በአዲሱም ሆነ በቀድሞው ሥርዓት የተሰለፈው ወታደር በልዩ ልዩ ስሜቱን ሲገልጽ ተስፋ ሊደረግበት የሚቻል ነው ተብሎ ተገመተ። ይልቁንም ደጃዝማች በየነ አባ ስብስብ በሰጋር በቅሎ ሆነው ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ «እኔ ፖለቲካ አላውቅም ፡ ነገር ግን በደሜ እክስሃለሁ» ሲሉ በፎከሩ ጊዜ ሳያወላውል የተፈጸመው አነጋገራቸው ሰሚውን በጣም አስደንቆታል።

ይህ ተስፋ ሊደረግበት የሚቻል የሰልፍ ሁኔታ ከታየ ከጥቂት ቀን በኋላ የኢጣልያ ጦር ወታደር መረብን ተሻግሮ አገሩን መውረሩ ስለተሰማ በደንብ የክተት አዋጅ ተነገረ። እንዲሁም በየአውራጃው የሚገኘው የጦር ሠራዊት

በየአገረ ገዥዎች መሪነት ወደ አዲስ አበባ ከተማ እየተባ በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሰልፉን ማሳየትና የጦረኝነት

| ስም | አውራጃ | ሰልፉን ያሳየበት | |
|---|---|---|---|
| | | ወርና | ቀን |
| ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ | ከምባታ | ጥቅምት | ፮ |
| ደጃዝማች አበበ ዳምጠው | ጎፋና ባኮ | ጥቅምት | ፫ |
| ራስ ጌታቸው አባተ | ከፋ | ጥቅምት | 10 |
| ደጃዝማች ሀብተ ማርያም ገብረ እግዚአብሔር | ወለጋ ነቀምቴ | ጥቅምት | |
| ቢትወደድ መኰንን ደምሰው | ወለጋ | ኅዳር | ፯ |

እነዚህ ከዚህ በላይ የተጠሩት መኳንንት በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ተሰልፈው ሲያልፉ አንዳንዶቹ በዲስኩር ፡ አንዳንዶቹም በፉከራ ስሜታቸውን ይገልጹ ነበር። ይልቁንም ጥቅምት ፫ ቀን በተደረገው የወታደር ሰልፍ የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ ፡ እኔ አሽከርህ፣ እኔ ባርያህ ቀድሜ ሳልሞት ጠላት ከፊትህ አይደርስም እያሉ ፈክረው ስለ ነበረ ግርማዊ ንጉሠ ነገሥትም የሚከተለውን ቃል በዚያ ለተሰበሰበው ወታደር ተናገሩ።

«ላገርህ ነፃነትና ለኛ ለንጉሠ ነገሥትህ ክብር ደምህን ለማፍሰስ ቆርጠህ መነሣትህን ማየታችን ደስ የሚያሰኝ ነው።

ጌታ ገንዘቡን የሚያስጠብቀው ላመነው አሽከሩ ስለሆነ ፡ አንተም እምነትህን በእግዚአብሔር ላይ አድርገህ የጦር ሠራዊታችንን እየጠበቅህ በማንኛቸውም ችግራቸው ሁሉ እየረዱ ለጠላት እንድትመከት አዘንሃል።

አሁንም የመጣብህ ጠላት ደም የተቃባነው ከጥንት የቆየ ነው እንጂ አዲስ ድንገተኛ ጠላት አይደለም ሰላም ፈላጊ የሆነውን የመንግሥታችን ማኅበር አምነን ጦራችንን ወደ ግንባር ባለማስቀደማችን አሁን ያገኘውን ሁሉ በጭካኔ ከመግደል በቀር እንኳን ለወታደር ለሽማግሌና ለሴት ለሕፃናትም ይራራል ተብሎ አይጠረጠርም። ለሴቶችና ለሕፃናትም አለመራራቱን ባጀማመሩ ሰምትነዋል።

በማናቸውም ቢሆን ሞት አይቀርምና እገሌ በሳልና በጉንፋን በተስቦ ሞተ ከመባል ላገሩ ነፃነት ለንጉሡ ክብር፣ ለትውልድ ስም ደሙን አፍስሶ ሞተ መባል ትልቅ ጥቅም ያለው መሆኑን መዘንጋት አይገባም። በጦርነት ላይ አንዱ ቢሞት ተራውን ተወጣ ይባላል እንጂ እገሌ ሞቷል ብሎ መደናገጥ የጀግንነትን ክብር የሚያዋርድ መሆኑን ማወቅ ነው።

ለወታደርም ለባላገርም ለነጋዴም ቢሆን ትልቅ ፡ ኵራት ያገሩ ነፃነት መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ስለዚህ ከመካከላችሁ ጠብና ተንኮል እንዲጠፋ ፍቅርና አንድነት እንዲሰፋ ፡ ሎሌ ለጌታው ጭፍራ ላለቃው ፡ መታዘዝን እንዲያውቅ በሚቻላችሁ ፡ ሁሉ ማስረዳት ነው። ኢጣልያኖች በመሣሪያቸው ቢኮሩብን እኛም ትልቁ መሣሪያችን የእግዚአብሔር እርዳታ በመሆኑ እንኮራባቸዋለን።

ቀይና ብጫ አረንጓዴ ባንዲራችን ፡ ሞዓ አንበሳ የሚለው ማኅተማችን የነፃነታችን ምልክት ነውና ይህ የነፃነታችን ምልክት እንዳይጠፋ እስከመጨረሻዋ ጠፍታ ደማችንን እያፈሰስን ብንሞትም ሰለስማችንና ለታሪካችን ፡ ትልቅ ክብር ነው።

ይህንንም ስላልናችሁ እንደ ዘመኑ ዓይነት ጦርነት እየተዋጋችሁ ኢትዮጵያን ከጠላት እጅ ማዳን ነው እንጂ ባለመጠባበቅና ባንዲት እንደ እሳት ራት በጦርነት ውስጥ እየገባችሁ ለመሞት ብቻ የሆነ እንደሆነ ለጠላት የተመቸ ይሆናል።

የምታደርጉትም ጥንቃቄ ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

፭ኛ ፡ ድንኳን ስትተክሉ በየሻምበሉ እየተለየ ሥፍራ ቢያጋጥም በጐድጓዳና በዛፍ ፡ በዱር ውስጥ መትከል ነው አተካከሉም ካንዱ ድንኳን እስከ ፴ ክንድ እንዲራራቅ ማድረግ ነው።

፮ኛ ፡ አይሮፕላን ሲበር በታየ ጊዘ ገላጣውንና ትልቁን መንገድ ሰፊውንም ሜዳ ትቶ በዘብጥና በጎድጓዳ በዘወርዋራ መንገድ ዛፍና ዱር ባለበት ሥፍራ መጓዝ ነው።

፯ኛ ፡ አይሮፕላን ቦምብ ለመጣል ሲመጣ ፪ ሜትር ያህል ዝቅ ካላለ አይመቸውምና ለዚሁ ሥራው ዝቅ ባለ ጊዜ በመልካም በረጃጅም ጠመንጃ ሮምታ ተኩሶ በፍጥነት መበታተን ነው። ሶስት ወይም አራት ጥይት ከመታው አይሮፕላን መውደቁ አይቀርም። ስለዚህ ተኩሱ የተመረጠን መሣሪያ ይዘው ለመተኮስ የታዘዙት ብቻ፣ ይተኩሱ እንጂ ጠበንጃ ያለው ሁሉ ቢተኩስ ጥይት ከማባከንና ያሉበትን ስፍራ ከማሳየት በቀር ጥቅም የለውም።

፰ኛ ፡ አይሮፕላኑ ገና ብቅ ሲል የተበታተናችሁ እንደሆነ ፡ የምትበታተኑበትን አቅጣጫ እንዳያየው ጥቂት ቀረብ እስቲል በጥንቃቄ ቆይቶ መበታተን ነው። ጦርነት በሚደረግበት ጊዜጣፋ ጋሻ ጉሜ ፡ ብርና ወርቅ ለምድ ፡ ግምምጃ ቀሚስ፣ ይህን የመሰለ ሁሉ ለጠላት ጠበንጃ ማነጣጠር ይመቻልና ክኮት ያለው ኮቱን ኮት የሌለው ያደፈ እጀጠባብ ብቻ መልበስ ነው። ይህም የወርቅና የብር ሽልማታችሁን እግዚአብሔር ረድቶን ስንመለስ ታደርጉታላችሁ። እየተችሁ መሄድ ነው ይህንንም የምክር ቃል ማስታወቃችን ባለመጠንቀቅ ትልቅ ጉዳት እንዳያገኛችሁ ብለን ነው እንጂ በሐምሌ ፲፭ ቀን በተናገርነው ዳስኩር እንዳስረዳናችሁ በጦርነቱ ጊዜ በመካከላችሁ ሆነን ስለ ኢትዮጵያ ነፃነት ደማችንን ለማፍሰስ የተዘጋጀን መሆናችንን ስናረጋግጥላችሁ ደስ ይለናል።

# ምዕራፍ ፫።

# <u>የዘማቾች ድርጅት።</u>

ምንም እንኳ የኢጣልያ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር ፕላኑን ያቀደበት አኳኋን ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች መገለጽ የጀመረበት ጊዜ ከ፬ ወይም ከ፩ ዓመት በላይ ቀደም ብሎ ቢሆን ፡ ሕዝቡ እንዲያውቀው ለማድረግ አስቸጋሪ መስሎ ታይቶ ነበር። ምክንያቱም በምኞት የተቃጠለውን የኢጣልያን አሳብ ለማብረድ ልዩ ልዩ ሰላማዊ መንገድ በማሳየት በከንቱ ይደክም ነበርና የሕዝቡ መንፈስ ሊታገሡት በማይቻል በዚህ በኢጣልያ ተግዳሮት ላይ ፈጥኖ እንዳይገነፍል ለማድረግ ነው። በብዙ ፈሊጥና በብዙ ሁናቴ የተደከመበት ሰላማዊው መንገድ ፈር እንዳያዘ ከታየ በኋላ ግን ፡ የኢጣልያን አሳብ ለሕዝቡ ዘርዝሮ ማስረዳት ግዴታ ሆነ። እንዲሁም ጦርነቱ ከመነሣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ የወታደር ትምሕርት በየአውራጃውና በየወረዳው ተጀመረ። አስተማሪዎችም ጥቂቶቹ የውጭ አገር ሰዎች ሲሆኑ ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ይሁን እንጂ በጦርነት ጊዜ ወታደር፣ ለጠላት አደጋ ፈጥኖ እንዳይገኝ ለማድረግ ፡ የሚስማማው በካኪ ጨርቅ ወይም በሌላ ዓይነት የተደራጀው ልብስ በክተት ለተጠራው ወታደር ሊያደርስ ካለመቻሉ የተነሣ የቀረው ወታደር ያንኑ ነጭ የነበረውን የራሱን ልብስ በልዩ ልዩ ዓይነት ቀለም ደበዝ እንዲያደርገው ታዘዘ።

የሚያስፈልገው ሥርዓትና ደንብ ከተሰጠ በኋላ ጦሩን በ፫ ግንባር ለማሰማራት በታቀደው መጠን ማስተንተን ተጀመረ። ሦስቱም ዋና ዋና የጦር ግንባሮች የተባሉትን የነዚህ ክፍል ጠቅላይ አዝማቾች የሚከተሉት ናቸው።

| ጠቅላይ አዝማች ስም | ማዕርጉ | ዋና የጦር ግንባር |
|---|---|---|
| ራስ ሙሉጌታ | የጦር ሚኒስትር | ትግሬ ፡ (ሰሜን) |
| ራስ ደስታ ዳምጠው | የሲዳሞና የቦረና ገዢ | ዶሎ ኔጌሌ (ደቡብ) |
| ደጃች ነሲቡ ዘአማኑኤል | የሐረር አውራጃ ገዢ | ውጋዴን (ምሥራቅ) |

እነዚህ የሦስቱ ዋና ዋና ግንባሮች አዝማቾች በውስጣቸው ያሉትን የጦር አለቆችና ወታደሮች በሚገባ እንዲያሰማሩ በሚቻልበት መንገድ እያንዳንዳቸው ቀጥሎ የተመለከተውን ማስጠንቀቂያ ከግርማዊነታቸው ተቀበሉ።

«ምንም የሥራው መጨረሻና ፍጹም እውቀት እግዚአብሔር ቢሆን እርሱ በሰጠን እውቀት እኛም እንደምናውቀውና እንደምናስበው ምንም የዓለም መንግሥታትና ሕዝብ ሁሉ አሳቡ ወደኛ ቢሆንና የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገው የማይገባ መሆኑን ቢፈርድልን ኢጣልያኖች በመጨረሻ ጦርነት ለማድረግ ቆርጠዋል። የጦርነቱም አደራረግ እንደምንሰማው ፡

፩/ ጦሩ ግልጥ ሲሆን አስመራና በወሰን ባጠራቀሙት ወታደር ብዙ መሣሪያ በታላቅ ኃይል ገፍተው በአኤሮፕላንና በመድፍ ልብ የሚያስደነግጥ ሥራ ሠርተው ወደ አድዋ፣ ወደ መቀሌ፣ ወደ ጐንደር በሌላውም በየወሰናችን ለመግፋት ነው።

፪/ ኢጣልያኖች ከጥንት ጀምሮ በታሪካቸውም የሚያጽፉት በልባቸውም ዋና መመኪያ የሚያደርጉት የኢትዮጵያ የጦር አለቆችና ዋናው አዝማች ሲሞት የሚሰበሰበው ሲያጣ ይበተናል ፡ በዚህ ድል እናገኛለን ማለትን ስለሆነ ይህ እርግጠኛ ነገር ተፈጽሞ እንዳይጐዳን ሺአውል ሲሞት ሺ ይሙት

የተባለው ምሳሌ ጥቅም ያለው መሆኑን አስበህ ጦራችን በዚህ በኢጣልያኖች ፕሮግራም እንዳይፈታ አንተም ሌሎችም አዝማቾች እንድትጠነቀቁበት ይሁን። ወታደሩ ካዝማቹና ካሠማራው መለየት ልማድ ስለሌለው ዋናው ባላሰበበት ጉዳይ ለምን እንሞታለን ብሎ እንዳይሰንፍ ዋና ዋናዎቹ አዝማቾች ብቻ አውቀውት በዘዴ የሚፈጸም ነው እንጂ ከፍርሃት አደራረግ እንዳይቆጠር ለማናቸውም ሰው ሁሉ የሚገለጥ አይደለም።

፫/ ኢጣልያኖች በዋና በዋና ከተማችን በአውሮፕላን አደጋ በመጣል ሴትም ሽማግሌም ልጅም ወታደርም ገድሎ አስፈራርቶም የጦር ሠራዊታችንን ልብ ለማስነፍ ነውና ስለዚህ ጦርነቱ ሳይገለጥ አሁኑኑ ሴትም ሽማግሌም ሕፃናትም ዕቃም ለአውሮፕላን አደጋ በማይመች በየዋሻውና በየተራራው ቦታ ተደርጎ የሚጠጉበትን ማሰብና ጦርነቱ ሲገለጥ ደረቅ ጦር ሆኖ መጠበቅ ነው። የሚጐዳን ሰው። ሲሞትብን የጦር ሠራዊታችን ሲቀንስብን ነውና ቤት ብቻ ቢቃጠል ጉዳታችን በጣም ያነሰ ይሆናል።

፬/ አትክልት የሚተክል ሰው ፍሬውን ካልበላ በመትከሉ ብቻ ደስ አይለውም። እንዲሁም የጦር ፍሬው ድል ከማድረግ ላይ ነው። ጠላት ለጊዜው ገፍቶ መሬት ቢይዝ ድል ፡ የሚገኘው አንድ ክፍል መሬት በመያዙ አይደለም።

ከዚህ በላይ ባንደኛው ቁጥር እንደተመለከተው ኢጣልያኖች ጦርነቱን እየጐተትን አደጋ እየጣልን ብዙ ቀን ስንታገል ያቆየናቸው እንደሆነ በአውሮፓ ጠላት እንዲነሣባቸው ፡ ባገራቸውም ሽብር የሚነሣባቸውና ድል እንዲሆኑ ስላወቁት ፡ እንደምንሰማው አሳባቸው በሁለት ወይም በሦስት ወር ጦርነቱን ጨርሶ በአውሮፓ ጠላት እንዳይነሣባቸው ድል አድርገን አገር ማቅናት ብቻ ይዘናል ብለው ለማውራትና በዚያ ያለውን ጠላት ለማስተኛት ስለሆነ ለኛ የሚጠቅመን ጦርነቱ ብዙ ወራት እንዲቆይ መጐተት ነው። በትሪፓሊ ጦርነት ምንም ፡ ጦርነቱ ብዙ ዘመን ከጐጃምና ከበጌምድር እሄዱ የሚሞቱላቸው የኛ ሰዎች በመሆናቸውና ብዙ የኢጣልያ ወታደሮች

ባለማምጣታቸው ነው። ለኢትዮጵያ ጦርነት ግን ጥቁሩን የሚያምኑት በመሆናቸው የሚበዛው ጦር ነጭ ነውና ይህ የሚመጣው ከዋናው አገራችን ከኢጣልያ በመሆኑ ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ እኛ ስንጐተት እነርሱ ሰው እያነሰባቸው ከሮማ ሲያስመጡ ሽብር የሚነሣባቸው ይሆናል።

፩/ ምንም የጦር መሣሪያ የኢጣልያኖችን ያህል ባይኖረን በዚሁ ባለን የጦር መሣሪያችን ብዙ ሰው እንዳያልቅብን አድርገን በኃይል ብቻ ሣይሆን በብልሃት ጭምር የእግዚአብሔርን እርዳታ ተማምነን ከጠበቅናቸው ሳንጐዳቸው አንቀርም አደራረጉም ቀጥሎ እንዳለው ሲሆን ይጠቅማል።

፪/ አሁን ያለውን የጦር ሠራዊት በወሰን አቅራቢያ። አሳልፎ ኢጣልያኖች ወሰን አልፈው እንዳይመጡ ግድ የተባለ እንደሆነ በትኩስ ጉልበትና በኃይልኛ መሣሪያ ይፈጁታልና ዋናው የጦር ሠራዊት ወደ ኋላ ቀርቶ ፳ ኪሎ ሜትር ከወሰኑ በሚርቅ ሥፍራ ቦታ እየተመረጡና እየተያዩ ቃፊሮች በዝርዝር ሆነው እንዲጠብቁ።

፫/ በወሰን አቅራቢያ የወሰኑን እርዝመት ተከትለው የሚቆሙት ቃፊሮች ኢጣልያኖች ከወሰን አልፈው ካጠሩት ሽቦ ከሠሩት ምሽግ ሲወጡ የተቻላቸውን ያህል ተከላክለው የጠላት ኃይል የበረታበትን የሚበዛው ወታደር የመጣበትን ለዋና ጦር በቶሎ እንዲነግሩ የኢጣልያ ጦር ከሠፈረ በኋላ የተረፉት ቃፊሮች ሌሊት አደጋ ጥለው አስደንብረውና በትነውት እንዲሸሹ።

፬/ የመጀመሪያው ቃፊሮች የተቻላቸውን ያህል ተከላክለው ቦታ ከለቀቁ በኋላ ደግሞ ዳግም እንደገና ቃፊሮች አቁሞ ዋናው የጦር ሠራዊት ወደ ኋላው የሚመች ቦታ ፈልጐና ይዞ እንዲቆይ።

፭/ ኢጣልያኖች በዚህ ብልሃት እየተጐተቱ ወደ አገራችን ሲገቡ መቸም በቀን ከ፳ ኪሎ ሜትር ይበልጥ አይሄዱምና ተዋጊውን ጦር በስተ ግምባር አድርገው ለጦር የሚያስፈልገውን ነገር ከወሰን የሚያቀብለው ወታደር

የሚተላለፍበትን ወደ ኋላ ያለውን አገር ለማስጠበቅ ግድ ይሆንባቸዋል። በዚያን ጊዜ በመንገድ ጠባቂው ወታደር ላይ ሌሊት አደጋ መጣልና ማሸበር ነው። ይህ ሲሆን ጠባቂውን ወታደር ቁጥር ለማብዛት ከአባራሪው ወታደር እየቀነሱ መተው ግድ ይሆንባቸዋል።

፲/ ለእኛ ጥቅም የሚሆነው የኢጣልያ ወታደር አገር በመጠበቅ ስንቅ በማቀበል እንዲበታተን ማድረግና ዋናው መጨረሻ የሚደረገው ጦርነት ሲደረግ የኢጣልያ ጦር በመባከኑ ገጣሚው ቁጥሩ ያነሰ እንዲሆን ደግሞ በቃፊሮች ላይ ብዙ ጥይት እንዲተኩሱ አድርጐ ጥይታቸው እኛን ሳይጐዳ እንዲያልቅባቸው ማድረግ ነው። ከዚህም በቀር በየጊዜው ወታደሩ እንደ ሽፍታ እየሆነ ሌሊት ከጀርባ እየገባ አደጋ እንዲጥል ማድረግ ነው።

፲፩/ አባራሪው ጦር ከጓደኛው እየተለየ አቅም እያነሰው ሲሄድ ካገራችን መሬት ቢይዝ ሌሊት አደጋ እየተጣለበት ፡ ከኋላ መንገድ እኒቆረጥበት እየተደረገ ቀን የረዘመበት እንደሆነ በኋላ ታይቶና ተገምቶ ቦታ ተመርጦ መጠበቅና በሙሉ ግምባር ገጥሞ መዋጋት ይቻላል።

፲፪/ የነፃነቱን ጥቅም የሰበክንለት ሕዝባችን ቢታገሥ ይልቁንም እንደምንም ብለን ጦራችን ብዙ ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቀን እስከ ሚያዝያ ብናደርሰው እግዚአብሔር በመካከሉ የሚሠራልን ታላቅ ነገር ይገኛል።

ስለዚህ ምሳሌ በታላቁ ጦርነት ዘመን ጊዜ የቤልጂግና የጀርመን ጦርነት አኳሆን እንዴት እንደነበረ ብናስብ ይጠቅመናል ፡ በዚያን ጊዜ ጦርነቱ እንደተጀመረ እንኳ አገሩን ዋናውን ከተማ ብሩክቤልን ጀርመኖች ይዘውት ነበር። ምንም የጀርመን ጦር ዋናውን ከተማ ቢይዝ ታላላቆች የመንግሥት ሰዎችና የጦር አዝማቾች አለመታጣትና የሕዝቡና የሠራዊቱ ልክ አለመፍታት ድሉ በተገኘ ጊዜ ካባራሪዎቹ ይልቅ አስለቃቂዎቹ ታላቅ ጭንቅ ፡ ሆነባቸው። ደግሞ ከዚህ በቀር የጀርመን የጦር ሠራዊት፥ ወደ ፈረንሳዊ ከተማ ወደ ፓሪስ በተጠጋ ጊዜ የመንግሥቱ ሰዎች ቦታ ለውጠው የጦር ሠራዊታቸውን

በብልሃት እንዲገጥም አድርገው ወደ ሌላ ከተማ ተዛወሩ። በቁርጥ ጊዜ ከሚደረገው ጦርነት በቀር በፍርሃትና በመደንገጥ ሳይሆን ቦታ ወደ ኋላ ማፈግፈግና ሲመች ጠላት የሚጐዳበትን ቦታ መርጦ መግጠም የዛሬው ጦርነት ድል የሚገኘው በብልሃት ጭምር ስለሆነ ከእግዚአብሔር እርዳታ ጋራ ይጠቅማል።

ከዚህም በኋላ ፡ የወረራዋ አኳኋን ስለ ተጀመረ ዋናውን ጦርነት ግጥሞያ እስከሚያደርጉበት ጊዜ ድረስ በየወሰኑ አቅራቢያ የሚገኑት የጦር አለቆቹ ምቹ ስፍራ እያዘጋጁና የጠላትን አደራረግ እያጠኑ እንዲቆዩ ተነግሮዋቸው ስለ ነበረ በሰሜን ግንባር የልዑል ራስ ሥዩም ጭፍሮች ፡ ማለት እነ ቀኛዝማች ዐባይ ካሣ በደሮ ተክሌ እነ ደጃዝማች ወራሴ አውግር በሚባለው ተራራ በኩል እርድ እየሠሩ ታጥቀው ይጠባበቁ ጀመር። ነገር ግን መጀመሪያ ጊዜ ኢጣልያኖች የድንበሩን መስመር አልፈው አገሩን ሲወሩ ቢራማና በዓዲ አርባዕቲ በኩል ከነበረው ከደጃዝማች ሣህሌ ጦር ጋራ ስለተገናኙ ምንም እንኳ በሚገባ ጦርነት ለማድረግ ባይፈቅድ ግጭቱን ለማስቀረት የማይቻል ሆነ ስለዚህ ደጃዝማች ሣህሌ በቴኔንቴ ምርጋንቲኒ አዝማችነት የሚጓዘውን የኢጣልያ ጦር ከጥቂቶች የሺሬ ወታደሮች ጋራ ሁነው በተጣራ ሜዳ ላይ ገጠሙት። በተደረገው ግጭት አዛዡ ቴኔንቴ ሞርጋ ንቲኒ ቆስሎ ስለ ወደቀ የጠላት ወታደር ተበታተነ። እብዚያን ጊዜ ከጀግኖቹ አንደኛው የቴኔንቴውን መለዮና መሣሪያ ገፎ ለልዑል ራስ ሥዩም ግዳይ ጣለ። ልዑል ራስ ሥዩምም ስለ ጀግኖቹ ፡ የቅልጥፍና አደራረግ ከተደነቁ በኋላ ከአዲስ አበባ የተጠየቀው የጦር መሣሪያና ስለ ጦርነቱ አገጣጠም የተወሰነው ፡ ፕላን እስኪደርስ ድረስ ማንኛቸውንም አደጋ እንዲጠነቀቁበት ለወታደሩ አስረዱ።

በዚያን ጊዜ ከውጭ አገር የጦር መሣሪያ እንደሚበቃ ለማግኘት ተስፋ የተደረገበት ነገር ሁሉ በማወላወል ላይ ስለ ነበረ ብዙዎቹ የጦር አዝማቾች የብስጭት ሁኔታ ከመግለጻቸው የተነሣ ኢጣልያ በአጥቂነት አድዋን ስትይዝ በብዙ አኤሮፕላን ዛቻ ሲሆን ኢትዮጵያ የለ መሣሪያ ባዶ እጅዋን እንደ

ነበረች እያሳሰበ የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቀጥሎ የተመለከተውን ቴሌግራም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አስተላለፈ።

«በ፳ አኤሮፕላን የታጀቡ የኢጣልያ የጦር ሠራዊቶች አዲግራትን ከያዙ በኋላ አንዳች መቃወም ሳያገኛቸው ትናንትና አድዋ ገቡ። ከአድዋ ከተማ ውጭ የሚገኙት የኛ የጦር ወታደሮች አሁንም እዚያው ናቸው። እስካሁን የደረሱት ግጭቶች ከወሰን ጠባቂዎችና ከጥቂቶች ተለይተው ከሚገኙ የጦር ክፍሎች ጋራ ነው። የኛ የጦር ወታደሮች ጦርነቱን አልጀመሩም። ለመከላከያ የጦር መሣሪያ እንዳታገኝ በፍጹም በተከለከለችው በኢትዮጵያ ላይ ከብዙ ወራት በፊት የተዘጋጀው የኢጣልያ አጥቂነት ወሰኑ ተጣርቶ በማያወላውል ስምምነት በተወሰነበት አውራጃ በመረጋገጥ ተፈጸመ።

ይህ ቴሌግራም ከደረሰ በኋላ ኮሚቴ ደኮአርደናሲዮን ተብሎ የተሰየመው ጉባኤ በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ጠብ ለመመርመር ስብሰባ አድርጎ ነበርና ከኢትዮጵያና ከኢጣልያ መንግሥታት የቀረበውን አስተያየት ምክንያት በማድረግ ስለ መሣሪያም ነገር በሰፊው ተነጋገረበት። በመጨረሻውም ከማንም መንግሥት ቢሆን በሽያጭ ወይም በእርዳታ በጠቅላላው በማንኛቸው ዓይነት ሆኖ ሁለቱ ጠበኞች መንግሥታት የጦር መሣሪያ እንዳይላክላቸው ሲል ይኸው ኮሚቴ ጥቅምት ፲ ቀን (11) ያቀረበው አሳብ በ፶፪ቱ መንግሥታት ዘንድ ተረጋገጠ። ይሁን እንጂ ይህ አደራረግ ለማን ወይም በማን እንደሚፈጸም ለመርመርና ለማወቅ አስቸጋሪ አልነበረም።

ኢጣልያ ከብዙ ዓመታት በፊት ኢትዮጵያን ለመውረር በቂ ነው ተብሎ በተገመተው መጠን ፡ እንዲያውም ምናልባት ስለ ኢትዮጵያ ወዳጅነት ኃይሉን የሚያቀላቅል ሌላም የውጭ አገር መንግሥት ቢገኝ ስትል በመጠራጠር ለዚያም ጭምር አሸናፊ የሚሆናት መሣሪያ አዘጋጅታ ነበር። ኢትዮጵያ ግን ከጥቂት ዓመታት በፊት ከጄኔብ ማኅበረተኝነት ስለ ተደመረች በማኅበረተኞቹ ዘንድ ሞገስን በምታገኝበት መንገድ አሮጌ ልማዷን ለማሻሻል

እጅግ ከፍ ያለ የውስጥ ሥራ ነበረባትና ከውጭ ጠላት ለመከላከያ የሚያስፈልጋትን በሚገባ ታደራጅ ዘንድ በቂ ጊዜ አላገኘችም። እንግዲህ በዚህ አያያዝ ኢጣልያ ከውጭ አገር መሣሪያ እንዳታገኝ ጭቆና ተደረገባት በማለት ፈንታ ኢትዮጵያ የፌጥኝ ታሥራ ለጠላቷ ተጣለች ማለት ይቀና ይመስላል።

ወዲያው ጦርነቱ ከመነሣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ የኢትዮጵያ መንግሥት ፡ ስለ ጦር መሣሪያ ግዢ ከጀርመን ከቤልጅክ ከዳነማር ከፈረንሳይ ከስዊስ ፡ ከስዊድን ፡ ከቼኮዝሎባኪያ ከቱርክ መንግሥታት ጋራ ተነጋግሮ ስለ ነበረ ፡ ይህንኑ ምክንያት በማድረግ የኢጣልያ መንግሥት ከመቃወሙ የተነሣ ታገደ። ከዚያ አስቀድሞ እንደ ተወራው ግን ከልዩ ልዩ የኤውሮፓ መንግሥታት ለኢትዮጵያ መንግሥት በግዢ ፲ሺ መውዜር ጠመንጃ ፪፻ መትረየስ ፪ ሚሊዮን ጥይት እስከ ሚያዝያ ፺ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም (15 4 35) ድረስ ፈጽሞ ይላክለታል እየተባለ ተስፋ ነበረ። እንደዚሁም የዚህ ዋጋ አከፋፈል የአምስት ዓመት ወሰን ተደርጎለት በቡና ከሚገኘው ሀብት ይሆናል ተብሎ ነበር። ይሁን እንጂ ስለዚሁ አንዳች የተፈጸመ ነገር የለም። ይልቁንም የስዊስ መንግሥት ለኢትዮጵያ መንግሥት ሊልካቸው አዘጋጅቷቸው ስለ ነበሩት አኤሮፕላኖች የኢጣልያ መንግሥት ከአፌስዬል እንደራሴዎቹን ወደስዊስ መንግሥት ልኮ ክርክር ከማድረጉ የተነሣ የሌለውንም መንግሥት በጎ ፈቃድ ለማሰናከል የመጀመሪያ እርምጃ ሆነለት። ስለዚህም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባይሆን እንኳ ዋጋቸው አስቀድሞ ተከፍሎባቸው ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት ከተላኩ በኋላ እበር ላይ የታገዱት መሣሪያዎች እንዲቀለቁልንና በነፃ እንዲደርሱልን ሲሉ አቤቱታቸውን ማቅረብ ግዴታ ሆነባቸው። ከዚህም በቀር የእንግሊዝ መንግሥት በንግድ ምክንያት ለኢትዮጵያ መንግሥት ይላኩ ስለ ነበረ የጦር መሣሪያዎች ፈቃድ መስጠቱ እንዲታገድ በማድረጉ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከነበሩት የእንግሊዝ ሚኒስትር ሲድኔይ ባርቶን (Sydney Barton) ጋራ በሰፊው ተነጋግረውበታል።

ኮሚቴ ደኮኦርደናሲዮን። ተብሎ የተሰየመው ጉባኤ ካቀረበው አስተያየት በቀር ኢትዮጵያ መሣሪያ እንዳታገኝ በሚቻልበት መንገድ ኢጣልያ በየጊዜው ትጠቅሰው የነበረው ማስጠንቀቂያ እንደፈረንጅ ቁጥር ነሐሴ ፳፩ ቀን ፲፱፻፴ ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት አውራጃ ሰለሚገባው የጦር መሣሪያ መቈጣጠር የተስማሙበትን ውል ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ስምምነት ፈቃድ ለሌላቸው ሰዎች እንዳይሸጥ ከመወሰኑ በቀር የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከውጭ አጥቂ የሚከላከልበትና በውስጡም የአገሩን ጸጥታ የሚጠብቅበት አስፈላጊውን ያህል መሣሪያ ይገዛ ዘንድ አይከለከልም ነበር።

ደግሞም አንዳንድ እንደ ቸኮስሎባኪያ ያሉ መንግሥታት እንኳን በጦር መሣሪያ በኩል ያለውን ንግድ ለኢትዮጵያ ቢፈቅዱ በአስፈላጊው ጊዜ እንዲደርስ ለማድረግ በልዩ ልዩ አኳኋን እየተቸገረ የታሰበው በቶሎ ይፈጸም ዘንድ ሳይቻል ቀረ። ከብዙዎቹም ምክንያቶች አንደኛው ወዲያው ጦርነቱ እንደ ተጀመረ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ ያለው ባቡር በጦር መሣሪያ ትራንስፖርት በኩል የኢትዮጵያን መንግሥት የማያገለግል ከሆነ የኢጣልያን መንግሥት ይህ ባቡር የተለመደ ሥራውን ሲቀጥል አደጋ እንዳያደርግበት ተስፋ ሰጥቶ በኢጣልያና በፈረንሣይ መካከል ልዩ የቃል ስምምነት በመፈጸሙ ነው። ስለዚህ የመሣሪያ ማመላለሻዎች የባሕርን መንገድ ተከትለው በመጡ ጊዜ በዘይላ በር (የእንግሊዝ ሱማሌ) ይራገፉና ሲቻል በካሚዮን ያለዚያም በግመል እየተጫኑ ከዚያው ወደ ጡሩ ግንባር ይላኩ ዘንድ ግድ ሆነ። እንግዲህ በዚህ አያያዝ ኢትዮጵያ የምታደርገው ትግል ባንድ በጠላት የጦር ግንባር በኩል ብቻ ሊወሰን አልተቻለም ማለት ነው። ስለዚህ በሌላው በኩል የደረሰውንም እንደሚከተለው በጥቂቱ መጥቀስ አለብን።

፩ኛ ከአጥቂው ለመከላከል የጦር መሣሪያ በገንዘባችን ስንገዛ ልንከለከል አይገባም በማለት ለዓለም መንግሥታት የቀረበው ክርክርና የፈቀደው ጊዜ

፪ኛ ትክክል ፍርድን በኢጣልያ መንግሥት ወዳጅነት ሊለወጡ ካልፈቀዱ አንዳንድ መንግሥት የጦር መሣሪያ በግዢ ለማግኘት ሲቻል ትራንስፖርት በመካከል የተደረገው ጭቆና

፫ኛ በግዢ የሚመጣው የጦር መሣሪያ በትራንስፖርት ማጣት ምክንያት ከዋናው ከተማ ሳይደርስ ከዚያው ከዘይላ በር ለየጦሩ ግንባር እንዲላክ በመሆኑ በሚገባ ለማከፋፈል አለመቻሉና ይህን የመሰለው መሰናክል ለጠላት አጥቂነት ደጋፊ ሆኖት ነበር።

## ምዕራፍ ፬።

## የቃፊሮች ተከላካይነት

የኢጣልያ የጦር ሠራዊት ሦስት እጅ የሚያህለው በሰሜን ግንባር (በኤርትራ) በኩል ሲሆን ፡ ከጄኔራል ግራዚያኒ ጋራ በደቡብ የተሰለፈው አንዱ እጅ ነው። በሰሜን ግንባር የበለጠው የወታደር ክፍል እንዲሰለፍ የተደረገበት ምክንያት የአማሴን ሕዝብ ከድቶ ከኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ጋራ ይደባለቃል እየተባለ ይወራ ስለ ነበረ ለመጠባበቅ እንዲቻል ነው። በውነትም ፵ ዘመን ሙሉ በጠላት ግዛት ውስጥ የተሠቃየው የአማሴን ሕዝብ ኢጣልያኖችን ለመክዳት ምክንያት የሚሆነው ነገር ይፈልግ እንደ ነበረ የታወቀ ነው። ስለዚህ ወዲያው የኢጣልያ ጦር የወሰኑን መስመር እንዳለፈ የኢትዮጵያ ተከላካዮች ወደ ኋላ በማፈግፈግ ፈንታ ወዲያው ገጥመውት ቢኖር ኑሮ በአዲስ ኃይል ወሰኑን ለመጣስ የሚያዳግት ካለመሆኑ የተነሣ በዚያን ጊዜ የአማሴን ወታደሮች ያለ ጥርጥር ጌቶቻቸው የሆኑትን ኢጣልያኖችን እየገደሉ ከወንድሞቻቸው ከኢትዮጵያውያን ጋራ ለመደመር የፈለጉት ምክንያት በተቃና መንገድ በተፈጸመላቸው ነበር ሲሉ አንዳንድ ሰዎች ያስባሉ። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የታቀደው የፖለቲካ መንገድ ከዚህ አደራረግ ጋራ በጣም የተራራቀ ነበር። ምክንያቱም

፩ኛ ኢትዮጵያ በፍጹም ጠብ ፈላጊነት እንደሌላትና ጠላት በተጋፊነት እንደወረራት ለማስረዳት የጦር ሠራዊቱ 30 ኪሎ ሜትር ያህል መሬት ላቀው ወደ ኋላ በመመለስ ሰላማዊነታቸው ይገልጹ ዘንድ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ ነው።

፪ኛ ጠላት ለአጥቂነቱ መፈጸሚያ በሚበቃው ፡ እንዲያውም በሚተርፈው መጠን የተጣራ ዘመናዊ መሣሪያና ወታደር ስላደራጀ ይህን የጠላት መሰናዶ ፊት ለፊት በመጋፋት ለመወዳደር አለመቻሉን ከመገመት የተነሳ ያልታሰበ አደጋ በመጣል የሚሆነው ጦርነት ለረዥም ጊዜ መከላከል ጠቃሚ ስለ ነበረ ነው። እንግዲህ አማሴኖች በኢትዮጵያ ስንደቅ ዓላማ ስር መሥዋዕት እንዲሆኑ የተመኙት ዕድል እነ ቀኛዝማች ሰላባንና እነ ፊታውራሪ ጸጋዬን በመሳሰሉት አንዳንድ ቁራጦች ሲፈጸም ለሁሉም ይሆን ዘንድ ጊዜው ስላልፈቀደ ቆየ።

የኢትዮጵያ ተከላካይ ወታደሮች በሚገባ ለማድረግ እስኪፈቀድላቸው ድረስ ምንም ወደ ኋላ ቢያፈገፍጉ ፡ ወደ አንዳንድ ጊዜ ሊያልፉት የማይቻል አጋጣሚ ነገር ሲደርስባቸው በሚያደርጉት መከላከል ታላላቅ የጀብዱ ሥራ ከመሥራት አልቦዘኑም ነበር። በመጀመሪያውም ጊዜ በግንባር ለመገኘት የቻሉት ልዑል ራስ ሥዩም (የምዕራብ ትግሬ ገዥ) ደጃዝማች አያሌው ብሩ (የሰሜን ገዥ) ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ (የሰቆጣ ገዥ) አንዳች አገልግሎት ሳያሳይ የከዳውን ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ (የምሥራቅ ትግሬ ገዥ) ሌሎቹም ጥቂቶች ነበሩ። በዚያን ሰዓት ልዑል ራስ ሥዩምና ሊከዳ ያሰበው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ በማናቸውም አኳኋን ፡ ንኑነት ስላልነበራቸው ለጦሩ አመራር በሁለታቸው መካከል የተደረገ ስምምነትና ምክር የለም።

ጥቅምት ፳፬ ቀን ልዑል ራስ ሥዩም አድዋን ለቀው ማርያም ሸዊቱ ወደ ሚባለው ስፍራ ተዛውረው ነበርና ከዚያ ሁነው የጠላት ጦር ያመራበትን አንፃር እየመረመሩ የሚያስታውቋቸው ሰዎች በየክፍሉ ላኩ። በዚያን ዕለት

ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ በሚገኙበት በዓዲ አርባዕቲ በኩል የጠላት ጦር ድንገት ስለ መጣ ታላቅ ግጭት ደረሰ። ስለዚህ ጀግናው ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ባዘጋጁት እርድ ውስጥ ሁለት የጠላት ታንኮች ወድቀው ታንከኞቹ የሚገባቸውን አገልግሎት ተቀበሉ።

ከዚህ በኋላ ወደ ማታ ልዑል ራስ ሥዩም ይህን የመሳሰለውን ሁኔታ ለንጉሠ ነገሥቱ በቴሌግራም ሲያስታውቁ በነገሩ እንዲታሰብበት አመለከቱ።

በማግሥቱ ጥቅምት ፳፫ ቀን በአንድ ቡሉቅባሽ መሪነት ፶ የሚያህሉ ሐማሴኖች ኢጣልያኖች ከድተው ከኛ ወታደሮች ተቀላቀሉ። እነርሱም ወዲያው እንደደረሱ ለአገራቸውና ለወገናቸው መሥዋዕት ለመሆን ቆርጠው መምጣታቸውን ለልዑል ራስ ሥዩም አስረዱ። እነዚህ ወታደሮች በህውላ እንደገለጹት ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ባለበት በመቀሌ በኩል ለመኰብለል የቀና መንገድ እያላቸው እራስ ሥዩም በሚገኙበት በኩል አሳብረው መምጣታችው ፡ የደጃች ኃይለ ሥላሴን ማወላወል አስቀድመው ተረድተውት ስለ ነበረ ነው። ደግሞም እንደነርሱ ብዙ አማሴኖች ኢጣልያኖችን ለመክዳት አሰፍስፈው እያሉ በመንገድ ምክንያት መቸገራቸውን በግልጽ ተናገሩ። ስለዚህ ልዑል ራስ ሥዩም በመስከረም ፳፯ ቀን ደጃዝማች ሣህሌንና ደጃዝማች ደስታን ፊታውራሪ መስፍንና ሌሎችንም ጥቂቶች የጦር አለቆች በስተቀኝና በስተግራ እየተዛወሩ ከኛ ለመቀላቀል የሚያስቡትን አማሴኖች ሲያገኙ መንገድ እንዲያመለክቱአቸውና ወዲያውም ጠላት ያመራበትን አንፃር እንዲመረምሩ ላኳቸው። እነርሱም በአድዋ ምሥራቅ በኩል ወደ ዳሮ ተክሌ ሲጓዝ ከጠላት ጦር ጋራ ተገናኝተው ታላቅ ግጭት ደረሰ። ይልቁንም በሆያ በኩል ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ በሚያስደንቅ አኳኋን ተዋግተው ለጊዜው የጠላት ኃይል በወታደር ብዛትና በመሣሪያ ብልጫነት ስለተጫናቸው ጥቂት ወደ ኋላ ካፈገፈጉ በኋላ እንደገና አስቀድሞ የነበሩትን ስፍራ መልሰው ከመያዛቸው በላይ ጠላትን ወደ ኋላ አሸሽተው ብዙ ምርኮ አገኙ። በዚያን ጊዜ የጠላት ወታደር የተሰማራበት መስመር ብዙ ስለነበረ የደጃዝማች ገብረ መድኅን ወታደሮች በነበሩት በአክሱምና በሽሬ

በኩልም ይህንኑ የመሰለ ግጭት ደርሷል። እንዲሁም ደጃዝማች ማሩ በዳሮ ተክሌ ምዕራብ ሲከላከሉ ቆይተው በኋላ ወደ ተንቤን ማፈግፈግ ግድ ሆነባቸው።

ይህን ሁሉ የመሰለው ግጭት እየቀጠለ ሳለ ልዑል ራስ ስዩም ጦርነት ይገጥሙ ዘንድ አልተፈቀደም ነበርና የጠላት ጦር ወደ ፊት እርምጃውን ከማፋጠኑ የተነሣ አደጋ እንዳይሆን ሠራዊታቸውን ይዘው ወደ ተንቤን ለመሄድ ቆረጡ።

በዚያው ሰሞን የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ከኢጣልያኖች ጋራ መነጋገር በአንዳንድ አስተዋዮች ዘንድ ስለተመረመረ የዚሁ ሁኔታ ተዘርዝሮ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀረበላቸው። ንጉሠ ነገሥቱ ግን የአፄ ዮሐንስ ዘር ሲሆን ከኢጣልያኖች ይስማማል ብሎ መጠርጠር እጅግ የሚያስቸግር ነገር ነው ሲሉ ለጊዜው አልተቀበሉትም ነበር ይባላል። ይሁን እንጂ የንጉሠ ነገሥቱ እምነት እንዳይነዋወጽ «የጠላቶቹን ስብቀት አይስሙብኝ» እያለ ብዙውን ቀን በማታለል አሳለፈው።

ይልቁንም እነ ቀኛዝማች ሰለበ ከኢጣልያኖች ከድተው ሲመጡ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴን ማወላወል ሳያውቁ ወደ መቀሌ በደረሱ ጊዜ ይኸው ደጃዝማች መልካም ተቀባይነቱን እያመሰለ ጥቂት ቀን በእንግድነት ካሰነባታቸውና ከንጉሠ ነገሥቱም ሽልማት እንዲያገኙ ካደረገ በኋላ ወደ ኢጣልያኖች እንዲመለሱ በተሰወረ አማርኛ የአሳቡን ዝንባሌ ገለጸላቸው። ስለዚህ እጃችንን አሳልፎ ለኢጣልያኖች ከሚሰጠን አስቀድሞ በቶሎ ብንለየው ይሻላል ፡ ብለው ስንብት ጠየቁት። እርሱም ምንም ወደ ኢጣልያኖች ለመግባት የቈረጠ ቢሆን ሕዝቡን ለማሳበር ጊዜ አስፈልጎት ነበርና እነ ቀኛዝማች ሰላባን ወዲያው አሳልፎ መስጠቱ ለሕዝቡ ማሳበር የጀመረውን ሥራ ቶሎ በመግለጽ አሳቡን የሚያሰነካክልበት ከመሆኑ የተነሣ የጠየቁትን ስንብት ለመከላከል አስቸጋሪ ሆነበት። ነገር ግን ከኢጣልያኖች

ያመጡትን የጦር መሣሪያ «በየመንገዱ የሚገኙ ወታደሮች ባለማወቅ ይቀሟችኋል» የሚል ምክንያት ሰጥቶ አስቀረባቸው።

በመጨረሻው ሕዝቡን ለማታለል ያደረገው ፈተና ከንቱ በመሆኑ ሕዝቡ ስለነቃበት ከፊታውራሪ ፀጋዬ ኃይሉና ከፊታውራሪ ረዳ ካሣ ፡ ቀኛዝማች ሀጐ ዳንጉልና ከቀኛዝማች ሰገጥ ደስታ ከሌሎችም ጥቂቶች መሰሎቹ ጋር መስከረም ፴ ቀን አገሩን ከድቶ ሄደ። እንዲሁም እርሱና ተከታዮቹ የኢጣልያን ባንዲራ ይዘው ጄኔራል ሳንቲኒ በሚገኝበት ግምባር በኩል ከኢጣልያኖች ተቀላቀሉ።

የትግሬ ሕዝብ በክዳት የማያብርለት መሆኑን ኢጣልያኖች ከተረዱት በኋላ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ምሥጢራዊ አገልግሎት እየሠራ መቀሌ እንዲቆይና አስፈላጊ ፡ ሆኖ እርሱ ምልክት በሰጠ ጊዜ ብቻ አኤሮፕላን መቀሌ ከተማ ወርዶ እንዲወስደው ተነጋግረው ነበረ ፡ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ግን የሕዝቡን መንፈስ አጠነካከር ስለ ተመለከተ ለአኤሮፕላን ምልክት እንኳን መስጠት ሳያደርስ ቀርቶ ከመቀሌ አዲግራት ፻፲ ኪሎ ሜትር የሚያህለውን መንገድ በመሬት መጓዝ ግድ ሆነበት።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ከጄኔራል ሳንቲኒ ጋር ተገናኝቶ ለኢጣልያ ታማኝነቱን ካስረዳ በኋላ ከጠቅላይ አዝማቹ ፡ ከጄኔራል ደቦኖ ጋር እንዲነጋገር ጠየቀ። ስለዚህ በማግሥቱ ፲ ሰዓት ከ፴፫ ደቂቃ ሲሆን በኰአቲት ከጄኔራል ዲቦኖ ጋር ተገናኘ። ከዚያም የተናገረው ይህ ነው። «እኔ የኢጣልያ ወዳጅ ነኝ። ስለዚህ የሥልጣኔ አምጭ የሆነውን የኢጣልያን ጦር ሠራዊት ሥራ በማናቸውም ረገድ አልቃወምም።» ይህንንም ከተናገረ በኋላ በፋሽስታዊ ሥርዓት እጁን ዘርግቶ ሰላምታ ሰጠ።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ከደቦኖ እንደተገናኘ ወዲያው የጠየቀው ሮማ እንዲሄድና ከሙሶሊኒ እንዲገናኝ ስለ ነበረ ፡ ከኢጣልያ ሹማምንቶች ጉን ተሰልፎ የኢትዮጵያን ጦረኞች ለመውጋት ፈርቶ ይሆን? በማለት ደቦኖ

ታዝቦታል ይባላል። በውነትም ቪቶሪዮ ዲኩርቲ የሚባለው ጸሐፊ እንዳስታወቀው ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ወዲያው ከጄኔራል ደቦኖ እንደተገናኘ ሙሶሊኒን በመገናኘት ምክንያት ወደ ሮማ ለመሄድ ጠይቆ እንደሆእን ከጦርነቱ ለመሸሽ ነው ቢባል አያከራክርም።

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ምንም እንኳ ብዙ ሰው ለማሳበር ባይችል የርሱ ክዳት ለጊዜው የታሰበውን የጦር አቅድ በማበላሸት እንደመጠኑ ጉዳት ማድረጉ አልቀረም። ስለዚህም ጥቅምት ፳፱ ቀን ኢጣልያኖች መቀሌን ለመያዝ በቁ።

መቀሌን የያዘው የጠላት ጦር የዳንከልን ባንዳ ጨምሮ ወደ ፊት ለመግፋት በሚሰናዳበት ጊዜ ኅዳር ፫ ቀን ደጃዝማች ካሣ ስብሐት

በአጽነራ ውስጥ ወምበርታ በሚባለው ክፍል ገጥመውት ከጧት እስከ ዕርበተ ፀሐይ በኋላ የጠላትን መግፋት ለያግዱት ቻሉ። በተደረገውም ውጊት ከጠላት ወገን የሞቱት ወታደሮች ሹማምንቶች ግምት ያላቸው ነበሩ። በዚህ ጦርነት ውስጥ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ አሽከሮችም ከኢጣልያ ጐን ሆነው ተሰልፈው ነበር ይባላል። ነገር ግን ደጃዝማች ካሣ ስብሐት የክልተ አውላሎ ገዥ ሆነው በደጃች ኃይለ ሥላሴ ቆራጥነት ውስጥ ሲኖሩ ቆራጩን የሚቆርጥበትና የሚቆራረጥበት ጊዜ በመሆኑ ይህን መልካም ጊዜአቸውን በሚገባ ስለሠሩበት ያልተደሰተ የለም።

በጥርጣሪ ላይ የነበረው የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ክዳት በሥራው ከተረጋገጠ በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ የክሕደት ሥራ እጅግ ተደነቀ።

ስለዚህ እንዲህ ተብሎ ተገጠመ።

አላያችሁሞይ በመዓራ ሜዳ

በወይዬት አለፈ ግዳማይ ይሁዳ

ማተቡን በጥሶ ቃል ኪዳን የከዳ

ምን ያሸሽገዋል እሱ ለተጐዳ

ያጋሜው ደጃዝማች የንደርታው በሊጋዳ

አቆማዳ አውልቀህ አረግህ አቆማዳ

አዬ ልጄ ሆዬ የገባኸውን ዕዳ

ሳትል አትቀርም ወይ መውጫ ቀዳዳ

እንዴት ትታዘብህ እደጋ ሐሙስ

ጠርቡሽህን አጥልቀህ ስትመላለስ

ምንኛ ይረግሙህ አፄ ዮሐንስ

የጽላተ ሙሴን ሥርዓት ስታፈርስ

ዓድዋ ከተማቸው ሲነድ ሲጤስ

የስሁል ሚካኤል ቅጽራቸው ሲፈርስ

በክንፍም አታመልጥ እንኳን በፈረስ

መጨነቅ ሳይመጣ መጠበብ ሳይደርስ

አትቀርምና ያች ፀአት ነፍስ

ነውር አይምሰልህ ይልቅ ተመለስ

ግዴለውምና መሐሪ ንጉሥ

ይቅርታ ልማዱ ነው እንደ ክርስቶስ

# ምዕራፍ ፰

## ግርማዊ ን ነ ወደ ጦሩ ግንባር ለመሄድ ያደረጉት ድርጅት።

ልዑል ራስ ሥዩም ባልፈው የተደረገውን ሁኔታና የመቀሌን መያዝ ከተመለከቱ በኋላ ረዳት ጦርና መሣሪያ ተጨምሮላቸው የሚያስፈለገን እንደሚያደጉ ይፈቀድ ዘንድ ወደ አዲስ አበባ በቴሌግራም ጥያቄያቸውን አቀረቡ። ንጉሠ ነገሥቱም ፊት ለፊት በመግጠም የሚደርሰውን ጉዳት በማመዛዘን አደጋ እየጣሉ ብቻ እንጂ ፊት ለፊት ገጥመው እንዳይዋጉ ፡ አስፈላጊውም በቶሎ እንዲደርስላቸው መታሰቡን እየገለጽጡ መለሱላቸው። ስለዚህ ወኔው የሚፈነቅለው ጀግና ሁሉ ሌት ተቀን ሳይል አደጋ እየጣለ የጀብዱ ሥራ ለመሥራት ይሽቀዳደም ጀመር። ይልቁንም ደጃዝማች ገብረ ሕይወት ባገረአልታ ስሜን በአድዋ በኩል አደጋ ጥለው በጠላት ላይ የፈጸሙት የወድነት ሥራ የማይረሳ ነው።

በየክፍሉ የተሠማሩት ጀግኖች በዚህ አኳኋን መልካም አገልግሎታቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ በሰሜን ግምባር ከሕዝባቸው ጋራ ለመሰለፍ የተጣደፈ ዝግጁነት ያደርጉ ነበር። ስለዚህም አብረዋቸው ለሚሰለፉት የጦር ወታደሮች እንደ ችሎታቸውና እንደ ተገቢነታቸው መጠን የሹመት ስም ስለመስጠትና ሰንደቅ ዓላማ ለመሸለም ኅዳር ፪ ቀን ጥሪ አደረጉ። በዚሁም ቀን ከጧቱ ከ፫ ሰዓት ጀምሮ ባላይኛው ግቢ ውስጥ ከታላቁ ቤተ መንግሥት አጠገብ ባለው ሰፊ ሜዳ የወታደር ሰልፍ ሆነ።

የሰልፉ መስመር እንደሚገባ ለመመልከት ጃንሆይ ፡ በታላቅ ድንጉላ ፈረስ ሆነው ሲዘዋወሩ በአዲሱ ዓይነት የተዘጋጀ የጦር ልብስ ለብሰው ነበር። ከግርማዊነታቸው ጋራ ልዑል አልጋ ወራሽ መርድ አዝማች አስፋ ወሰን ፊታውራሪ ብሩ ደጃዝማች ዳምጠው ፡ ደጃዝማች አደፍርሰው ደጃዝማች

መኰንን እንዳልካቸው የጦር ልብሳቸውን ለብሰው እንዲሁ በንጉላ ፈረስ ግርማዊነታቸውን በማጀብ ይከተሉ ነበር።

ለሹመት የታጩት መኰንኖች በልጅ አበራ ግዛው አቅራቢነት «ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ታማኝ ሆኜ ያወጡትን ሕግ ለመፈጸም ምያለሁ» ሲሉ እያንዳንዳቸው እየቀረቡ መሐላቸውን ከፈጸሙ በኋላ ግርማዊነታቸው ቀጥሎ ያለውን ተናገሩ።

«ዛሬ ይህንን ሰንደቅ ዓላማ ስንሰጣችሁ በዚህ ሰንደቅ ዓላማ አሁን ለተመረጣችሁበት የጦር ክፍል ክብር ለንጉሠ ነገሥታችሁና ለኢትዮጵያ ሕይወታችሁን የምታሳልፉበት ምልክት መሆኑን እወቁ» ይህንን ሰንደቅ ዓላማ ከተረከባችሁበት ከዛሬ ቀን ጀምሮ የምንሰጣችሁ ሕግ ፡ ሕይወታችሁን ለንጉሠ ነገሥታችሁና ለኢትዮጵያ በኰራትና በጀግንነት በሚያመሰግነውም ሥራ እንድታሳልፉ ነው። ይህም የሰው ልጅ ከሚያገኘው የበለጠው ዕድል በወታደርነታችሁ ለናንተ ስለደረሰ ለዚሁ የተገባችሁ ምሳሌ ሁኑ

ንግግሩም እንደተፈጸመ የተሿሚዎቹን ስም መጥራት ተጀመረ። ይኸውም ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው።

የሻለቃ ብርሃነ መስቀል

የሻለቃ አባተ ጓንጉል

የሻለቃ ተድላ መኰንን

የሻምበል አባተ ይመር

የሻምበል በላቸው ይርጉ

የሻምበል መታፈሪያ ከተማ

የሻምበል ታደሰ ገነሜ

የሻምበል ደምሴ አምበርብር

የሻምበል አሰፋ ፋንታ

የሻምበል ክንፈ ሚካኤል ገዳ

የሻምበል ታየ መኰንን

የሻምበል ገብረ ክርስቶስ መኰንን

የሻምበል ብዙ አየሁ ወልደ ዮሐንስ

የመቶ አለቃ ወርቁ ክንፌ

የመቶ አለቃ ገሰሰ ታየ

የመቶ አለቃ ኃይሉ ተሰማ

የመቶ አለቃ አባተ ቡሰሪ

የመቶ አለቃ በፈቃዱ መርጊያ

የመቶ አለቃ መንገሻ ሀብተ ወልድ

የመቶ አለቃ አየነው ቸኰል

የመቶ አለቃ ብርሃኔ አጥናፌ

የመቶ አለቃ ዘውዴ አባጣሰው

የመቶ አለቃ ጣሰው ዘገዬ

የመቶ አለቃ ለማ መንገሻ

የመቶ አለቃ ጥላሁን አዮ

የመቶ አለቃ ስንሻው አይቼው

የመቶ አለቃ ታመነ እንዳለ

የሙቶ አለቃ ፍስሐ አክሊሉ

የሙቶ አለቃ አስፋው ገብሬ

የሙቶ አለቃ ከበደ ገነሜ

የሙቶ አለቃ ሥዩም መኰንን

የሙቶ አለቃ ተፈሪ ሸበሺ

የሙቶ አለቃ ዘውገ በቀለ

የሙቶ አለቃ መኰንን ነጋ

የሙቶ አለቃ ሣህሌ እንቆ ሥላሴ

የሙቶ አለቃ በትረ ተስፋ

የሙቶ አለቃ በቀለ በላቸው

የሙቶ አለቃ ወዳጆ አሰፋኸኝ

የሙቶ አለቃ በቀለ በላቸው

የሙቶ አለቃ ታገለ ትርፌ

የሙቶ አለቃ ገረመ ይልማ

የሙቶ አለቃ አለሙ ካሣ

የሙቶ አለቃ በቀለ አበበ

የሙቶ አለቃ ልመንህ አሞኘ

የሙቶ አለቃ ታመነ ዋሴ

የሙቶ አለቃ ዘለቀ ወልዴ

የሙቶ አለቃ ፈንታ ዓለሙ

ከዚህ በላይ እንዳሳየነው ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት አብረዋቸው የሚሰለፉትን በመምረጥና ደግሞ ወደ ልዩ ልዩ ግንባር የሚዘምቱትን የጦር አለቆች በማስተንተን ሲሠሩ ቆዩ።

ግርማዊነታቸው ወደ ጦሩ ግንባር ለመጓዝ ከመነሣታቸው በፊት በልዩ ልዩ ምክንያት የወታደር አገልግሎት እንዲሠሩ ያልተፈቀደላቸው ሰዎች የገንዘብ እርዳታ እያወጡ ከመስጠት አላቈረጡም ነበር። ከዚህም በላይ ምንም ለጊዜው ባይፈቀድልን ፡ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ዝግጁዎች ነን እያሉ በመልካም ፈቃድ የጋለ ስሜታቸውን ሲገልጹ እጅግ ደስ አሰኝተዋል። ስለዚህም ከሌላው ጊዜ በቀር በጥቅምት ወር መጨረሻ ከንግድ ሚኒስቴር ባልደረባቸው ስለቀረበው እርዳታ ግርማዊነታቸው ፡ የተናገሩት ቀጥሎ የተመለከተውን ነው።

«ሕፃን ጎልማሳ ፡ ሽማግሌም ቢሆን ኢትዮጵያዊ ከሆነ ከኢትዮጵያ አየር ሳይመገብ ያደገ የለም። ስለዚህ ማንም ሰው ቢሆን በጉልበት በገንዘብ በደምም ያገለገለ አንድ ላይ ሲደምሩት ሁሉ ለሀገሩ ረዳ ይባላል። አሁንም ለአገራችሁ ያደረጋችሁትን እርዳታ ከሰልፍ ሂደው ደማቸውን እንዳፈሰሱት ያህል ቆጥረን አገልግሎታችሁን አናስቀርባችሁም»

## ምዕራፍ ፮።

## ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጅጅጋን ስለ መጐብኘታቸው።

ከዚህ በኋላ ጃንሆይ ወደ ሰሜን የጦር ግንባር ለመሄድ የሚነሡበት ጊዜው ስለ ደረሰ በውጋዴን ግንባር ከልዩ ልዩ አዝማች ጋራ የተሰለፈው የጦር ሠራዊት ምን ሞያ እንደ ሠራ ለመመልከትና ለማጽናናት ይልቁንም ብዙዎቹ የጦር አለቆች ከጃንሆይ ጋራ እንድንሠለፍ ይፈቀድልን ሲሉ ለምነው ነበርና በየትኛውም የጦር ግንባር የሚሠራውን ለማወቅ ጃንሆይ ቅርብ መሆናቸውን ለማስረዳት ኅዳር ፱ ቀን ፲፪ ሰዓት ሲሆን ከአዲስ አበባ ተነሥተው ቃኘው ይባል በነበረው አኤሮፕላን ጅጅጋ ልክ በ፲፪ ሰዓት ደረሱ። እንዲሁም ግርማዊነታቸውን የሚአጅቡ ሌሎች ሁለት አኤሮፕላኖች ነበሩ። ከዚያም የጦሩ ጠቅላይ አዝማች ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል የወታደር ሰልፍ አድርገው ተቀበሏቸው። ግርማዊነታቸው ሰልፉን ከተመለከቱ በኋላ በተለይ ወደ ተዘጋጀው ማረፊያ ገብተው ለወታደሩ ግብር አደረጉ።

በማግሥቱ ኅዳር ፲ ቀን በጠቅላዩ አዝማች በደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል አቅራቢነት በተለየ የጀብዱ ሥራ የሠሩት ወታደሮች ለጃንሆይ ግዳይ ሲጥሉና የጀግንነታቸውን ሞያ በፉከራ ሲተርኩ ዋሉ። ከዚያም ውስጥ አገልግሎታቸው በርግጥ የተመሰከረላቸው ብዙ ሴቶች የወንድ ልብስ ለብሰው የጦር መሣሪያ ይዘው ፎክረዋል። ጃንሆይም ለያንዳንዳቸው አገልግሎት የሚገባ ሽልማት ከሰጡ በኋላ ለተሰበሰቡት የጦር ሠራዊትና ሹማምንት ቀጥሎ የተመለከተውን ዲስኩር ተናገሩ።

«የዛሬ አርባ ዓመት የኢጣልያ መንግሥት በግፍ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማጥፋት ስለ ተነሣ በዚያን ጊዜ የነበራችሁት አሁንም በሕይወት ያላችሁ አርበኞች በአድዋም ጦርነት ያልነበራችሁት በዚያው የነበሩ አባቶቻችሁ ደማቸውን በማፍሰስ አርበኝነታቸውን አሳይተው የአገራቸውንና የርስታቸውን ነፃነት ከጠላታቸው ከኢጣልያ ዳኑ። አሁን የኢጣልያ

መንግሥት ያንኑ የዛሬ አርባ ዓመት ድል የሆነበትን ጦርነት ብድር ለመመለስ በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊቱ አልቋልና አለ ችግር እንዋጋቸዋለን ብሎ ለሕዝቡ ሰብኮ፣ ያልሞታችሁትን እንደሞታችሁ አድርጎ የታወቀውን በዓለም ታሪክ ተጽፎ የሚገኘውን የኢትዮጵያን ልጆች ጀግንነት አዋርዶ ነፃነታችሁን ለማጥፋት፣ ርስታችሁንና ቤታችሁን ለመውረር፣ አሮጌ አባት እናታችሁን በባርነት ለመግዛት ፡ ልጆቻችሁን ስደተኞች ለማድረ ፡ የኢትዮጵያን ጀግኖች እንደሌሉ አድርጎ ለማስቆጠር በሰሜንም በደቡብም ጦር አምጥቶ ለማጥቃት ጦርነት ጀመረ። የዓለም መንግሥታት ሁሉ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ በግፍ መነሣቱዋን አውቀው ሁሉ ለኛ ረዳቶች ሆነዋል። ኢጣልያ የኢትዮጵያ አርበኞች ምንም ያለቁ ቢመስላትና ያሉትም ከምንም ሳትቈጥራቸው ብትቀር በዘራቸውና በኢትዮጵያ ላይ የተደረገባትን ግፍ ጠላታችንን በማሸነፍና በግፍ ከያዙት ግዛታችን በማባረር ጀግንነታችሁን ማደስ የተገባችሁ ዋና ነገር ነው።

ሰው ለዘለዓለም ነዋሪ ሊሆን አልተፈጠረም፣ መጨረሻውም ከዓለም የሚለየው ሞት ነው። ይህ ሞት ይቀድማል ይከተላል እንጂ ለሰው ልጅ ሁሉ አይቀርለትም። ከመቃብር በላይ ፡ እየሰፈፈ የሚታይ ዓለም እስኪያልፍ ድረስ መታሰቢያ ሆኖ የሚኖር ስም ነው።

የዛሬ ዓርባ አመት በዓድዋ ይህ ጠላታችን በተዋጋን ጊዜ የኢትዮጵያ ጀግኖች ድል ስለመቱት፣ እንኳንስ በሕይወት ያላችሁት በዚያውም የቀሩት ቢሆኑ ስማቸው ሳይረሳ ለዘለዓለም ሲጠራ ይኖራል። አሁንም ላለው ትውልድ ዋና የሚያኮራ ነው። ደግሞ ለወንድ ልጅ እንኳንስ አገሩንና ርስቱን የሚቀማ ወገኑን ወደ ስደት የሚያደርስ ጠላት ተነሥቶበት እንዲያውም ቢሆን ዋና ምኞቱና የሚያኮራው ሞት በጦርነት የሚደርስበት ነው። ዶሮ እንኳን ጫጩቶቹዋን ከአሞራ ለማዳን ትተናነቃለች። ይህ ከሆነ በአእምሮም በጉልበትም ብዙ ሺ ጊዜ የሚበልጥ ሰው ምን ያህል ከጠላቱ ጋራ መታገል እንደሚገባው እወቁ። እንግዲህ ለሰው ልጅ ሞት በመጨረሻው የማይቀርለት ከሆነ የማይጠፋ ስሙን ለመትከል አሮጌ አባትና እናቱ ሚስቱን ልጆቹን እንዳያሳድዱበትና ዛሬ በነፃ አገራቸው በኢትዮጵያ ተከብረው ሲኖሩ ነፃእንት

የጠፉ እንደ ሆነ ይህ ክብራቸው ቀርቶ ከውርድት እንዳይወድቁ ለማድረግ የመጣውን ጠላት በመውጋት ሕይወታችሁን ብታሳልፉ ክብራችሁ የቱን ያህል ይሆን።? የከበረ ስማችሁም በልጆቻችሁና በወገኖቻችሁ ዘንድ ሲመሰገንና በዓለም ታሪክ ሲጠራ ይኖራል። ከዚህ ቀደም ጠላታችን በልጆቻችሁና በወገኖቻችሁ ዘንድ ሲመሰገንና በዓለም ታሪክ ሲጠራ ይኖራል። ከዚህ ቀደም ጠላታችን ይህንኑ የአጥቂነት አሳቡን ለመፈጸም ማሰቡን አውቀን በሰላም ጊዜ የምንገዛችሁ ንጉሠ ነገሥታችሁ በጦርነትም ጓዜ ከመካከላችሁ ሆነን ደማችንን ለማፍሰስ መቍረጣችንን ነግረናችሁ ነበር። ይኸው አሁንም ከናንተ ጋር አለን።

ኢጣልያኖች ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ቢያበዙ ካወቃችሁበት ምንም ሊጎዳችሁ አይችልም። አውሮፕላንም የተባለው በሚቀጥለው ቦምብ ጩኸት ለማስደንገጥና ልብ ለማስነፍ ነው እንጂ ሌላ የሚጠቅም ሥራ አይሠራም ስለዛሬው ዘመን የጦርነት አኳኋን ብዙ ጉዳት ሳያገኛችሁ ጠላታችሁን ለማጥቃት እንድትችሉ በያለቃችሁ በኩል የሰጠናችሁን ምክር መከተል ነው። ለአገራችሁ ነፃነት ለመከላከል በዚህም ባላችሁበት ሥፍራ በችግራችሁ ሁሉ በገንዘብም በስንቅም ችግራችሁን ለማቅለል እርዳታችንን አናጓድልባችሁም። አሁንም ለሀገራቸውና ለወገናቸው ክብር የተገባ ሥራቸውን ሲሠሩ ሕይወታቸውን ላሳለፉ አርበኞኖች ለወገኖቻቸውና ለቤተ ዘመዳቸው ሁሉ ችግር እያንዳንዳቸው ንጉሠ ነገሥትም አባትም ሆነን እንጠብቃቸዋለን። ስለዚህም በያለቃቸው ስማቸው ተጽፎ እንዲቀርብልን የጦር እንደራሲያችንን አዘናል። እኛም ሕይወታችን እስኪያልፍ ድረስ ዘወትር ከናንተ ጋራ ነን።

ግርማዊነታቸው ከዚህ በላይ የተመለከተውን ዲስኩር ተናግረው ከፈጸሙ በኋላ የተሰበሰበው ሕዝብ በጭብጨባ መልካም ስሜቱን ገለጸ። ወዲያውም ነጋሪት እየተጐሸመ በጀግንነት ለተዋጉ ሰዎች የማዕርግ ስም መስጠት ተጀመረ። ከተሿሚዎቹ አንደኛው ጥቅምት ፳፫ ቀን የጠላት

አኤሮፕላን ባደረገው ቦምባርድማ ቆስሎ በጅግነት የሞተው ግራዝማች አፈወርቅ ወልደ ሰማዕት ነው። ስመ ማዕርጉም የውጋዴን ደጃዝማች አፈወርቅ ተብሎ በአዋጅ ተነገረ።

የውጋዴን ደጃዝማች አፈወርቅ የውጋዴንና የጅጅጋ አውራጃ ዲሬክተር ሁኖ ይሠራ በነበረበት ጊዜ በ፲፱፻፳፮ ዓ.ም የሸቦለ ሡልጣን አሎል ጂኒሌ የሚባለው በኢጣልያ ተንኮል ከኛ መንግሥት ከድቶ አስቸግሮ ስለ ነበረ የዚሁ የሱልጣን ዐመፅ ያነሣውን ሁከት በማረጋጋት ያደረገው ሥራ ስመ ጥሩ አደረገው። የወልወልም ግጭት ከተነሣ በኋላ ፭፻ ወታደር ይዞ ጊርሎጉቢ የተባለውን ከኢጣልያኖች ሠፈር ትይዩ የነበረውን ቦታ ይዞ ተከላከሏል። ጦርነቱም ከመነሣቱ ትንሽ ቀደም ብሎ በቆራሂ ላይ ምሽግ ሠርቶ ነበረና በዚሁ በምሽግ ውስጥ የጠላትን ወራሪነት እየተከላከለ ብዙ ጊዜ ቆይቷል። ባቅራቢያውም ሁኖ የሚረዳው ከሌሎቹ ጋር ዑመር ሰማተር የሚባለው የአቢያ ባላባት ነበር።

የውጋዴን ደጃዝማች አፈወርቅ በቆራጥነትና በጀግንነት ሲሠራ በነበረበት ጊዜ እላይ እንደተናገርነው ጥቅምት ፳፫ ቀን በቦምብ ፍንጣሪ ከፋኛ ቆስሎ ወደቀ። ወዲያውም በርሱ መውደቅ ምክንያት ወታደሮቹ ለጠላት መሬት እንዳይለቁ ከዚያው ይቀብሩት ዘንድ ለመናቸው። ነገር ግን እርሱ እንዳለው ሳይሆን ወደ ደገሐቡር ይዘውት ሲሄዱ በመንገድ አረፈ። የሱም መሞት በግንባሩ የነበረውን መልካም ሁኔታ ሊለውጠው ቻለ።

ወደ ቀደመው አሳባችን በመመለስ የተሿሚዎቹን ስም ቀጥለን እናስታውሳለን

ግራዝማች ዝግታ የፊታውራሪ ስመ ማዕረግ አገኙ።

ናደብ የሚባለው ሱማሌ ፊታውራሪ ተባለ

ግራዝማች አበበ በያን ቀኛዝማች ተባለ

ባላምባራስ አሊኑር ቀኛዝማች ተባለ

ባላምባራስ አበበ ወንድም አገኘሁ ግራዝማች ተባለ

ባላምባራስ ተረፈ በላቸው ግራዝማች ተባለ።

ለእነዚህ ከዚህ በላይ ለተጠሩት ጀግኖች ስመ ማዕርግ ፡ ለቍስለኞች መታከሚያ የሚሆን የገንዘብ እርዳታ ካደረጉ በኋላ በጅጅጋ ዙሪያ የተሠራውን ምሽግና ከጠላት የተማረኩትን አራት ታንኮች ጐበኙ። እንዲሁም ከጠላት ጋራ ለተሰለፉት ጀግኖች የፍቅር ሰላምታና ማጽናኛ የሚሆን ንጉሣዊ ቃላቸው እንዲደርሳቸው አድርገው ወዲያው ሌሊቱን ወደ ድሬዳዋ ተመለሱ። እግረ መንገዳቸውን ሐረርን ከጐበኙና በዚያም ለሚገኙ የጦር ቁስለኞች የገንዘብ እርዳታ ካደረጉ በኋላ ኅዳር ፲፮ ቀን በዚያው አባ ቃኘው በሚባለው አኤሮፕላን ተሣፍረው አዲስ አበባ ገቡ።

ኢጣልያኖች በመጨረሻው እንዳያገኙት ኢምፎርማሲዮን ንጉሠ ነገሥቱ በሚመለሱበት ጊዜ ጉዟቸውን ለማሰነካከል የአየር ተዋጊዎች የነበሩ አራት አኤሮፕላኖች ልከው ነበር። ነገር ግን ኢምፎርማሲዮኑ የደረሳቸው በጣም ዘግይቶ ነበርና በቃኘው ሊያደርሱበት ባለመቻላቸው ከሐረርና ከአሩሲ መገናኛ ድንብር ተመለሱ።

## ምዕራፍ ፯።

## ጃንሆይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሰሜን ግንባር ስለ መጓዛቸው።

በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በሐምሌ ወር በምክር ቤት ስብሰባ ሆኖ ጃንሆይ ዲስኩር ሲያደርጉ «አሁን የሚናገራችሁ ንጉሣችሁ በዚያን ጊዜ በመካከላችሁ ይገኛል ፡ ለኢትዮጵያም ነፃነት ደሙን ለማፍሰስ ተዘጋጅቷል ብለው በተናገሩት መሠረት ሌላውን ድርጅት ከፈጸሙ በኋላ ኅዳር ፲፰ ቀን ከአዲስ

አበባ ተነሥተው ወደ ሰሜን ጉዟቸውን ጀመሩ። ተከታዮቻቸውም የተመለከቱት ናቸው።

ልዑል መኰንን ኃይለ ሥላሴ

ፊታውራሪ ብሩ

ደጃዝማች ወንድ ይራድ

ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ዐባይነህ

ደጃዝማች አደፍርስ

ደጃዝማች ወልደ አማኑኤል

ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ

በጅሮንድ ፍቅረ ሥላሴ

አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ

ቀኛዝማች መኩሪያ ባንቲርጉ

ከርማዊነታቸው ጋር አብረው እንዲጓዙ የተመደቡ መኳንንቶች ብዙዎቹ ነበሩ። ነገር በዚያው ሰሞን ልጅ ኢያሱ ማረፋቸው ስለተሰማ ስለርሳቸው ቀብር ግርማዊነታቸው ወደ ሐረር ሔደው እስኪመለሱ ድረስ መኳንንቱ ቀድመው እደሴ እንዲጠብቁ ተደረገ። መዋዕለ ኃዘኑም ሲፈጸም ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መኳንንት አስከትለው ኅዳር ፳ ቀን ከማታው በ፩ ሰዓት የጦር ዋና ሠፈር ከነበረው ደሴ ከተማ ገቡ። ከዚያም እንደደረሱ ሕዝቡ በእልልታ ወታደሩ በሆታ ተቀበላቸው።

ግርማዊ ጃንሆይ እደሴ ከመግባታቸው ከ፮ ቀን በኋላ ፳፩ የኢጣልያ አኤሮፕላኖች መጥተው በደሴ ከተማ ላይ ብዙ ቦምብ ጣሉ። ባደረጉትም አደጋ የቀይ መስቀልን እንኳ ሳያከብሩ በመቅረታቸው ከሌሎቹ ጋር አንዲት አስታማሚ የነበረች የአሜሪካ ሴት በብርቱ ቆሰለች።

በዚያን ጊዜ ጃንሆይ ኦርሊኮን የተባለውን የአኤሮፕላን ማውረጃ መድፍ ጠምደው በጀግነት ሲተኩሱ ዋሉ። ስለዚህም መኳንንቱ እስካሁን ድረስ ኢጣልይኖች በደሴ ከተማ የአኤሮፕላን አደጋ ሳያደርጉ ቆይተው አሁን መጀመራቸው የግራማዊነትዎን ሕይወት ለመቃወም እንደፈለጉ ያስረዳል። በእውነትም ኢጣልያኖች እንዳሰቡት ፡ ለማድረግ ቢችሉ ለኛ ለባለተስፋዎቹ ሕዝቦችዎ የመጨረሻ ጥፋታችንን የሚያመጣና የኢጣልያኖችን ዕድል የሚያስከትል ይሆናል። ስለዚህ ግርማዊነትዎ የአኤሮፕላን አደጋ በሚሆንበት ጊዜ ከተዘጋጀው ዋሻ እንዲሆኑልን» ሲሉ ልመናቸውን አቀረቡ። ነገር ግን ገና ጦርነቱ ከመነሣቱ አስቀድሞ «በሰላም ጊዜ የምንገዛችሁ ንጉሠ ነገሥታችሁ በጦርነትም ጊዜ ከመካከላችሁ እገኛለሁ» ብለው የተናገሩትን መሠረት በማድረግ ከመኳንንቱ የቀረበላቸውን ልመና ሊቀበሉትና ሊፈጽሙት አልቀዱም። እንዲያውም ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ሕዝቡ ከአኤሮፕላን አደጋ የሚጠበቅበትን ዘዴ ያስጠኑ ጀመር።

በመጀመሪያው ጊዜ ስለ አኤሮፕላን አደጋ የተሰጠውን ጥንቃቄ ለማስፈጸም እጅግ አስቸጋሪ ነበረ። ከብዙዎችም ምክንያቶች አንደኛው በሰላም ጊዜ የኢትዮጵያን ወታደር ለማሰልጠን መጥተው የነበሩት የውጭ አገር ኦፊሰሮች በጠላት መካከል በእጁ መሣሪያ ይዞ የሚገኝ ማንኛውም ኤውሮፓዊ ያላንዳች ክርክር በጠመንጃ ይደበደባል» ሲሉ የኢጣልያ ባለሥልጣኖች የተናገሩት ዛቻ ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያን ትተው ወዳገራቸው ከመግባታቸው የተነሣ ዘመናዊውን ሥልጣኔ ተከትለው ወታደሩን በሚገባ ለማስጠንቀቅና ለመምራት የሚችሉ የኦሰሮች ቁጥር እጅግ ጥቂት ስለነበረ ነው።

ዛቻውን ስለፈሩና መንግሥታቸው በኢትዮጵያ እንዲሠሩ የሰጧቸውን ፈቃድ ስለወሰዱባቸው በችግር ጊዜ ኢትዮጵያን ትተው የሄዱት የውጭ አገር ኦፊሰሮች ሁኔታ ሲያሳዝን የመጣው ይምጣ በማለት የኢትዮጵያን መንግሥት የረዱት ዳግም ታላቅ ወሮታ እንዳይላቸው አይዘነጋም። ከዚሁም የኩባው

ካፒቴን አሌክሳንድሮ ዴል ቫሌና በውጋዴን ክፍል ከደጃዝማች ነሲቡ ጋራ ዘምቶ በቴክኒክ ክፍል ረገድ ያገለገለው የቱርኩ ጄኔራል ዊሂብ ፓሻ ስመ ጥሮች ናቸው።

ግርማዊ ጃንሆይ እደሴ በቆዩበት ጊዜ ሁሉ የጠላት አኤሮፕላኖች እየተመላለሱ ቦምብ ከመጣል አላቋረጡም ነበርና እንደ መጠኑ በቤቶችና በሰላማዊ ሕዝቦች ላይ ጉዳት ማድረጋቸው አልቀረም። እንግዲህ የአኤሮፕላንን አደጋ ለመቃወም የምንችልበት ምን ዓይነት መሣሪያ ኖሯል? ሲባል እሾህ በሾህ ይነቀላል እንደተባለው ለአኤሮፕላን ከአኤሮፕላን በቀር መቃወሚያ የሚሆን አዲስ ብልሃት ለማግኘት ከቶ አልተቻለም።

ኢጣልያ አኤሮፕላን በመንዳትና በልዩ ልዩ ብልሃት ረገድ የውጭ አገር ሰዎች ለኢትዮጵያ መንግሥት ተቀጥረው በጦርነቱ እንዳይገለግሉ መከላከያ ያደረገች «፩ሺ የኡንጋሪያ ፈቃደኞች ወታደሮች ከኢጣልያኖች ጐን ተሰልፈው በኢትዮጵያ መሬት ለመዋጋት ቢጠይቁ ኢጣልያ ሳትፈቅድ ቀረች» ማለትን ነበረ። ነገር ግን በችግር ምክንያት በ፩ቱ ማዕዘን ተበታትነው የነበሩት ኢጣልያኖች እንደመሪያቸው ቃል አዲስ ዓለም ለመውረስ ተጠርተው ሲሰበሰቡ በተደረገው ግምት ፡ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመውጋት ቀርቶ ሌላም ጦርነት የጠማው መንግሥት ቢኖር በቂዎች ናቸው ቢባል አያሳፍርም ነበርና በዚያን ጊዜ ኢጣልያ በእውነትም እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ አገር ርዳታ አላስፈለጋትም።

## ምዕራፍ ፰።

## <u>የደቡብ ጦርነት።</u>

በውጋዴን ደጃዝማች ነሲቡ ፡ በቦረና ራስ ደስታ ጠቅላይ አዝማች ሁነው በሠሩበት በመጀመሪያው ጊዜ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነገር ተፈጽሟል።

ምንም እንኳ ጥቅምት ፳፫ ቀን በሰሜን እንደተረገው ሁሉ ጠላት የድንበሩን መሥመር አልፎ ዶሎን ለመያዝ ቢችል በመካከለኛው ሰዓት ራስ ደስታ የታመኑ ወታደሮቻቸውን አስቀድመው ወደ ፊት በመግፋታቸው በሱማሌ ውስጥ ታላቅ ድንጋጤና ሽብር ሆኖ ነበረ። ፕላናቸውም እንደ ሚከተለው ነው።

በደቡብ በኩል የጠላት ጦር አዝማች የሆነው ጀኔራል ግራዚያኒ ዋና የጦር ሠፈር ያደረጉት ባይዶኔ የሚባለውን ለውጋዴንና ለቦረና ግንባር አማካይነት ያለውን ስፍራ ነበር። ስለዚህ ራስ ደስታ በውጣቸው የሚገኙትን የጦር ሠራዊት ይዘው አብዛኛው የግራዚያኒ ጦር በውጋዴን በኰል ሰሞኑን የበረታ ጦርነት ያደርግ ስለ ነበረ ለጊዜው ከርሱ ጋራ የአለውን የጦር ኃይል ጥሶ በስተጀርባ ለመከበብ አስበው ነበረ። ነገር ግን ኢጣልያኖች የዚሁ አደራረግ ፕላን በሰላዮች አማካይነት ደርሷቸው ስለ ነበረና ይልቁንም ራስ ደስታ ከአዲስ አበባ ግንኙነት የሚያደርጉበትን የራዲዮ የቁጥር ቃል ብዙ ጊዜ ለማግኘት ስለቻሉ በነገሩ እንዲጠነቀቁበት ሆነ። ስለዚህም አኤሮፕላኖች እየተምላለሱ አደጋው በሚያሰጋበት በኩል ያለውን የኛን ወታደር በቦምብ ከመደብደባቸው የተነሣ መንገድና ፋታ ከለከሉት።

ከራስ ደስታ ወታደሮች ተከፍለው ባንድ በኩል ወደ ከፍተኛው ጁባ ሲጓዙ ግራዚያኒ ኦሎን ጂኔሌ የሚባለውን የሸባሌን ባላባት አደጋ እንዲጥላባቸው አዘዘው።

ይህ ኦሎል ጂኔሌ ጦርነቱ ከመነሣቱ አስቀድሞ በኢጣልያኖች ገንዘብ ተታሎ ስለ ነበረ በውጋዴን አውራጃ ብዙ ሁከት እያስነሣ አስቸግሮ ነበር። ጦርነቱም እንደ ተነሣ ወዲያው የኢትዮጵያን መንግሥት ከድቶ ከኢጣልያኖች ጐን ተሰለፈ። እንዲሁም ከግራዚያኒ እንደተቀበለው ትእዛዝ የኛ ወታደሮች ሠፈር ወደ አደረጉበት አንፃር ወደ ጋባ ተጓዘ። ምንም እንኳ ከርሱ ጋራ የነበሩት የኢጣልያኖች ቁጥር ያነሰ ቢሆን የተጣራ መሣሪያ የያዘ

ከ፫ ሺ በላይ ወታደር ነበረው። ይኸውም ሆኖ እርምጃው ከሥጋት ጋራ ነው።

የኛ ወታደሮች ኅዳር ፲፪ ቀን ጥቂት ግጭት ካደረጉ በኋላ አሎልን ከነሠራዊቱ ከበው መንገድ በማሳጣት አስጨነቁት። ለጊዜውም መሽጐት ከነበረው ሠፈር ተጠግተው ብዙ ሥራ ሠሩ። ይሁን እንጂ ከርሱ ጋራ የነበረው ማርኮኒስታ ሰርጀንቴ ኦቼርቢ ባለማቋረጥ ለግራዚያኒ ቴሌግራም ያደርግ ነበርና አኤሮፕላኖች ደርሰው ታላቅ እርዳታ አደረጉለት። ስለዚህም ለጥቂት እጁን ከመማረክ አዳነ። የሆነ ሆኖ ሳያቋርጥ ከግራዚያኒ ጋራ ግንኙነት ያደርግ የነበረው የራዲዮ ፡ አንቴናው ሳይቀር ከኛ ወታደሮች መትረየስ ስለተደበደበና ራዲዮ ቴሌግራፊዎቹንም ከሥራቸው ስለ አቋረጣቸው «ጥይት አልቆብናል።» ሲሉ ሁለት ቃሎች ብቻ ለግራዚያኒ አስተላልፈው ጭጭ እንዳሉ ሆነ። ወዲያው ብዙ አኤሮፕላኖች ተልከው ለአሎል ወታደሮች መከላከያ የሚሆን ልዩ ልዩ መሣሪያ ከጣሉባቸው በኋላ በኛ ወታደሮች ላይ ዳግም የቦምብና የመትረየስ በረዶ ያፈሱባቸው ጀመር። በዚህ ፡ አኳኋን ጦርነቱ እየተጋጋለ ሲቀጥል ፡ በሌላው ግንባርም እንዲሁ ተፋፍሞ ነበር።

የራስ ደስታ ወታደሮች በማያወላውል ቈራጥነትና ሊነገር ፡ በማይቻል ድፍረት ጦርነቱን ፡ እንደመከቱና የጠላትን እርምጃ እንዳገዱት ግራዚያኒ ስለተመለከተ ዶሎ በሚገኘው ፡ የኢትዮጵያ ሠራዊት ላይ ጋዝ አስፊክሲያን የሚባለው መርዝ ከቦምብ ጋራ እንዲጣልበት አዘዘ። ስለዚህ ታኅሣሥ ፳፩ ቀን ጧት በ፭ ሰዓት ፲፪ የኢጣልያ ፡ አኤሮፕላኖች መጥተው በጦር ሠራዊታችን ላይ እያንዣበቡ በተባራሪ ወረቀት ታትመው ግራዚያኒ የፈረመባቸውን የዛቻ ደብዳቤዎች በተኑ። የተጻፈውም ቃል ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

«ምርኮኞች የተቀደሱ እንደ መሆናቸው መጠን ሊከበሩ ሲገባቸው ፡ እናንት ዩንቴርናሲዮናልንና ሰብአዊ ሕግን በማፍረስ ከአኤሮፕላን ነጅዎቻችን

አንዱን ምርኮኛ ገድላችሁ ራሱን ቆርጣችሁት። የዚህን ብድር፥ እንደሚገባችሁ ትቀበላላችሁ፡-

እነዚህን ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ደብዳቤዎች ሲበትኑ ቆይተው፣ ሩብ ሰዓት ያህል ካለፈ በኋላ በመርዝ የተቀመመውንና በሌላም ዓይነት የተሰናዳውን ቦምብ ፡ መጣል ጀመሩ። እንዲሁም የቀይ መስቀልን ሳይቀር የመትረየስ በረዶ አዘነሙበት። በዚያን ዕለት ከሞቱትና ከቆሰሉት በመርዝም ከተሰቀዩት ኢትዮጵያን በቀር ሁለት የስዊድን ቀይ መስቀል ፡ ሠራተኞች በብርቱ ቆሰሉ። እነዚሁም የአንቡላንስ ፡ ሕክምና አለቃ ዶክቶር ሂላንደርና፥ አስታማሚው ሊንድስትሮም ነበሩ።

ሊንድስትሮም ቁስሉ በጣም የጸና ኖሮ ጥቂት ቆይቶ ሞተ። የርሱ ሞት በስዌድን ከተማ በስቶኮልም በተሰማ ጊዜ ታላቅ ኃዘን ሆኖ ባንዲራዎች ሁሉ ዝቅ ብለው ተሰቀሉ። በዚያን ወራት ኢጣልያኖች የጦርነት ሕግ በመሻር ስለአደረጉት ጭካኔ በእስተኮልም ከተማ ታላቅ ቊጭትና ንዴት ነበረ።

ታኅሣሥ ፡ ፳ ቀን በተደረገው የቦምብ አደጋ ምክንያት በጉዞም ሆነ በሠፈር የነበሩ ወታደሮች ተለያይተው ነበርና መንገሻ ያለው የሚባለው ሰው በግግሩ ፡ ውስጥ ከድቶ ወደ ኢጣልያኖች ለመግባትና ለጊዜው የኢትዮጵያ ጦረኞች የሚገኙበትን ሁኔታ ዘርዝሮ ለማስረዳት ተመቸው።

ይህ መንገሻ ያለው የጎጃም ሰው ነው ሲባል አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ባሪያ ከሚባሉት ወገን ከመሆኑ በቀር ተወላጅነት የለውም ይሉ ነበር። ኢጣልያኖች በ፲፱፻፫ ዓ.ም ሊብያን ለመያዝ ይዋጉ በነበረበት ጊዜ ከጐናቸው በባዙቅነት ተሰልፎ ከ፫ላይ እስኪቆስል ድረስ ታላቅ አገልግሎት አድርጎላቸዋል። ስለዚህ የቡሉቅባሽነት ማዕርግ ስጥተውት ነበር።

በወታደርነት እንዲያገለግል የተስማማበት ጊዜ እንደተፈጸመ ወዲያው በ፲፱፻፳፩ ዓ.ም ስንብት ተቀብሎ ወደ መቀሌ ተመለሰ። በመቀሌ ተቀምጦ ከኢጣልያኖች በምንዳ ያገኘውን ገንዘ እያጣራ ሳለ በኢጣልያና በኢትዮጵያ

መካከል ይህ ጦርነት ስለ ተነሣ ላገሬ እሞታለሁ ሲል ቃሉን ሰጠ። ሰለዚህም የአምሳ አለቅነት ተቀብሎ በደቡብ በኩል ከራስ ደስታ ጦር ጋር ተሠለፈ። ነገር ግን እንደ አጋጣሚ በደቡብ በኩል የጠላት ጦር አዝማች ሆኖ የመጣው በሊቢያ ጦርነት ጊዜ የቡልቅባሽነት ማዕርግ የሰጠውና ሁለት የጦር መስቀሎች (ክሮቼ ዲ ጉየራ) የተሸለመው ጄኔራል ግራዚያኒ መሆኑን ስለሰማ የማምለጫ ምክንያትና ጊዜ ጠብቆ ሶስት ራሱን ሆኖ ኮበለለ። እንዲሁም ከጠላት የሚገኛኝበት መንገድ በማጣት ብዙ ጊዜ ዱር ለዱር ከባዘነ በኋላ ለስለላ ከመጣ ካንድ የኢጣልያ ኦፊሲዬር ጋር ተገናኘ። ለርሱም «ቪቫ ኢታሊያ ሮማ ናፓሊ ፡ ሚላኖ ጄኖቫ» ሲል በመዘባረቅ ጮኸለት። ኦፊሲዬሩም በዚህ ድንገተኛ ጩኸት ክው ብሎ ደነገጠ። በኋላ ግን ወደ ርሱ እንዲቀርብ አድርጎ መሠረታዊ አሳቡን ተረዳና ዋና የጦር ሠፈር ወደ ነበረው ወደ ሉግ ላከው። እዚያም እንደ ደረሰ ከጄኔራል ግራዚያኒ ተገናኘ።

መንገሻ ምንም እንኳ ግምት የሌለው አንድ ተራ ሰው ቢሆን የሚገኝበትን ሁኔታ ሌላውንም አስፈላጊ ነገር ሁሉ የዓይን ተመልካች ከሆነው ከመንገሻ ጠይቀው በሚገባ ካጠኑ በኋላ ያደረጉት ማነጣጠር የተሳበት ጊዜ እጅግ ጥቂት ነው።

ከብዙ ቀን ጦርነት በኋላ በባሌና በቦረና ግንባር ያሉ የኛ ወታደሮች የአኤሮፕላን አደጋ ስለበረከተባቸውና ይልቁንም በየሠፈሩ የወደቀው የአኤሮፕላን አደጋ ስለበረከባቸውና ይልቁንም በየሠፈሩ የወደቀው የከብት እሬሳ እየተበሳበሰ የፈጠረው ልዩ ልዩ በሽታ ብዙ ሰው ስለጐዳባቸው ጦርነቱን ተሰቅቀው ወደኋላቸው መመለሳቸው ተሰማ። ስለዚህም ደጃች ገብረ ማርያም የሚያስፈልገውን በማድረግ አጽናንተው እንዲመልሷቸው ከንጉሠ ነገሥት ታዘው ቀጥሎ ከተመለከተው አዋጅ ጋር ተላኩ።

# አዋጅ።

## የሲዳሞ የጦር ሠራዊት።

ይህ ዓለም ኃዘንና ደስታ የተቀላቀለበት ስለሆነ፣ ሰው አንድ ቀን ሲበረታ አንድ ቀንም ሲደክም ነው። እስከ ዛሬም እበረሃ ወርደሕ ለጦር፣ ለበሽታ፣ ለቦምብ መመከትህን በየጊዜው ራስ ደስታ አታውቆኛል፣ እንኳን ለግዛትህ ለሌላው አገር ተርፈህ ሥራ የምትሠራውን ፡ እንዴት ጠላት ሲዳሞን ወንድ እንደሌለበት አድርጎ ይግባበት? አሁንም ወደፊት የምመለከተው ሥራህን ነው እንጂ ባለፈው ጥፋትህ ምሬሃለሁና እንኳን ወታደር ወንድ ልጅ ለብረት የደረስክ ራስ ደስታ አስታወቀህ ቦታ ድረስ ከተህ እርዳ። ጥር ፲፱ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በባሌ ክፍለ ወደሚገኙትም በዚሁ ዓይነት ተጽፎ ተልኮላቸዋል።

በውጋዴን ክፍል የተሰልፉት ወታደሮች ጠንክረው በሚዋጉበት ጊዜ ኢጣልያኖች ጥቅጥቅ ብሎ በሚታይ ጉም አምሳል ብጫ ዓይነት ጋዝ የሚያፈልቅ ቦምብ ወረወሩባቸው። ይኸውም የተጣለው ጋዝ የሚያስከትለው ሥቃይና ሕመም እጅግ ጠንካራ ነበር። ስለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት እየመላለሰ አቤቱታውን ለዓለም መንግሥታት በቴሌግራም አስተላለፈ። ይሁን እንጂ ኢጣልያኖች በመርዝ የተቀመመ ቦምብ እያመጡ አብዛኛውን በሰሜን ግንባር በኩል እያስፋፉ ይሠሩበት ዘንድ ያገዳቸው ነገር የለም። ይልቁንም ይህ አደራረግ በጦረኞቹ ላይ ላይ ብቻ ሳይሆን አንዳች የጦር ሠራዊት በማይገኝባቸው መንደሮች በሴትና በሕፃናት ፡ በሽማግሌዎችም ላይ መፈጸሙ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከፍ ያለ የኃዘን ስሜት ጣለበት። ስለዚህም እንደ ፈረንጅ ቊጥር ጥቅምት ፲፫ ቀን ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ላሄ በምትባለው በሆላንድ ከተማ ከተወሰነው ድንጋጌ ፳፫ ኛውንና ፳፭ኛውን አንቀጽ እየጠቀሰ አቤቱታውን አደሰ።

ከኢትዮጵያ መንግሥት በኩል እንዲህ እየተደጋገመ የሚቀርበው አቤቱታ ጉባኤውን ዕረፍት ሊሰጠው ከቶ የማይችል ነበረ። ይሁን እንጂ ወደ

መጋቢት ወር መጨረሻ በሎንዶን ከተማ ስብሰባ እንዲሆን ቀጠሮ ከመስጠቱ በቀር ለጊዜው የተወሰነ ነገር አልነበረም።

የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ላይ መርዝ እንዲጣል ያደረገበትን አኳኋን ሲያመካኝ በምርኮኞች ላይ ስለ ተደረገው ጭካኔ በሚገባ ብድር መከፈል ይሆን ዘንድ ታስቦና ታውቆ የተፈጸመ ነው ብሎ ተናግሩዋል ፡ ለዚሁም ማረጋገጫ እንዲሆን መርዝ ከመጣሉ ትንሽ ቀደም ብሎ «ፖፖሎ ዲ ሮማ» የተባለው የኢጣልያ ጋዜጣ እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር።

«እኛ በጦርነት ላይ ነን ይህንንም ጦርነት የኤንቴርናሲዮናልንና ሰብአዊ ሕግን ፈጽሞ ማክብር ጋራ እናደርገው ዘንድ በፈቀድን ነበር። ነገር ግን በማናቸውም አደራረግ እንድንዋጋ ጠላት በሚያሰቅቅ የጭካኔ ሥራው ያስገድደናል። ስለዚህም ጦርነቱ በታላቅ ጭከና እንዲቀጥል እንጠይቃለን። በሥርዓት የማይተዳደሩት የንጉሠ ነገሥቱ ጦረኞች ከወታደርነት ክብር ጋር ሊዋጉ ምንም አይችሉም። እኛ ወታደሮች ሕይወት በጣም ቅዱስና ውድ ስለሆነች በማናቸውም አደራረግ እንድንከላከል ማመንታት አይገባም። አንዳችን ማመንታት አንዳች ማፈር ፡ አንዳች ርኅራኄ የለብንም።»

ይህን የመሳሰሉ ጭካኔን የሚያነሣሱና የሚያበረታቱ አርቲክሎች (ጆርናሌ ዲታልያ) ና (ላቦሮ ፋሽስታ) የሚባሉ ጋዜጦች እየተደጋገሙ ከተጽፉ በኋላ ብድር ለመክፈል ነው በሚል በቂ ባልሆነ ምክንያት የተሸፈነው የኢጣልያ ያረመኔነት ሥራ መርዝ በመርጨት ላይ ተመሠረተ።

እንደ እውነቱ በኢጣልያ ጦረኞች ላይ የደረሰባቸው ከሰብአዊ ሕግ የወጣ አደራረግ ይኖራል ብሎ ማሰብ እጅግ እፁብ ነገር ነው። ከኢጣሊያኖች አደራረግ ጥቃቅኑን ሳይለቃቅሙ ጎልቶ የሚታየውን ሲእምለከቱት ግን እጅግ የሚያሰቅቅ ነገር አለበት ይኸውም ቁስለኞችን መጨረስ ብዙዎቹን ሰዎች ከዛፍ ጋር በምስማር እየቸነከሩ መስቀል ፡ ሴቶችንና ሕፃናትን በመርዝ ማሳወር የጦር ሠራዊት የሌለባቸውን ባዶ መንደሮች በቦምብ መደብደብ

የቀይ መስቀልን አለማክበር፣ አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል ነው። በቦምብ ከቀለጡት ከብዙዎቹ ባዶ መንደሮችና ከተሞች ሐረርን እናነሣለን።

ሐረር ከኅዳር ፳፫ ቀን ጀምሮ የጦር ሠራዊት የሌለባት ክፍት ከተማ መሆንዋ በኦፊሲዬል ተረጋግጦ ነበር። ነገር ግን ከዚያ በኋላ የኢጣልያ አኤሮፕላኖች እየተመላለሱ ለጦር የማያገለግሉትን ደካሞች ሊነገር በማይቻል ጭካኔ ደበደባቸው።

የሐረር መደብደብ ካሳዘናቸው ከብዙዎቹ የውጭ አገር ሰዎች አንደኛው ሞንሴኘር ዣሮሶ ለቤተ ፡ ዘመዶቻቸው የጻፉትን ደብዳቤ ቀጥለን እንገልጸዋለን።

«የኢጣልያ አቪዮን ርኅራኄ የሌለውን የቦምብ አደጋ ከጣለ ከማርስ 29 (ከ፩ ወር) ጀምሮ መጠጊያ የሚሆነኝ ዋሻ ለመፈለግ ሐረርን ትቼ በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ገጠር መሸሽ ግዴታ ሆነብኝ። የሽምግልና ጉልበቶቹን ከማስደግፍበት በቀር ሌላ ቢሮ ስለሌለኝ እነዚህን መስመሮች ስጽፍ በዚህ በጎሬ (ዋሻ) ተኰራምቼ ነው።

ምንም የጦር ክፍል ሠራዊት የሌለበት መሆኑ በኦፊሲዬል ተነግሮ ሰላማዊነቱ በተረጋገጠው በሐረር ከተማ የተደረገው የኢጣልያ ቦምብ አደጋ ስለ ጦርነት የተወሰነውን ሕግ የሚሽር ነው። ካቶሊካዊ በሆነ መንግሥት የተደረገው ይህ የሕግ መጣስ ሥራ ለኛ ከፍ ያለ ከባድ ነገርን ሊያስከትል ቻለ። ይልቁንም በሐረር የሚገኘው የኛ ቤተ ክርስቲያን መቅደስ በጠላት ቦምብ መጥፋት ያልታሰበ ነገርን ወለደ፣ ማለት ኢጣልያዊነት የሆነች የሃይማኖትን ቁም ነገር በኛ ሐዋርያነት ላይ ለማየት ያለው አሳብ አቋረጠ። የሚፈነዳ መሣሪያ የሚወረውሩ ፫ የኢጣልያ አኤሮፕላኖች አስር ደቂቃ ካንዣበቡባት በኋላ የኛ ሚሲዮን አስር ቦምቦች ተቀበለች። ከነዚሁም ስምንቱ ከፍ ያለ ግምት ያለው ጥፋት አደረጉ። በከተማውም ላይ ከተጣሉት ከ፫፻ ቦንቦች ፺ው ፍጻሜያቸውን ሲያገኙ፣ አብዛኞቹ መለኮታዊ በሆነ በእግዚአብሔር ጥበቃ ምንም በሌለበት ባዶ ሥፍራ ወደቁ።

ከዚህ በላይ እንደ ተመለከተው የሚበቃ ምስክርና ማስረጃ ያለው የኢጣልያ የአረመኔነት ሥራ አንዳች ማስታወሻ ሳይኖረው ለኢትዮጵያ አደራረግ ብድር መክፈያ ነው ቢባል ዋጋ የሌለው ነው።

## ምዕራፍ ፱።

## <u>ግርማዊነታቸው በደሴ።</u>

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከኅዳር ፳ ቀን ጀምሮ እስከ የካቲት ፲፫ ቀን ድረስ እደሴ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፣ ታላላቅ ሥራዎች ፈጽመዋል። ከነዚሁም ጕልቶ የሚታየው

(ሀ) ማዕከላዊ በሆነ ሥፍራ ላይ ተገኝተው የማናቸውም ክፍል ጸጥታ እንዲጠበቅ መድከም ፡

(ለ) የጠላት አኤሮፕላኖች በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ ሳላይሽ ከሚባለው ስፍራ እየወጡ ኦርሊኮን በመተኮስ ለጀኖች መንፈስ የደፋርነትና የቈራጥነት ምሳሌ መሆን ፡

(ሐ) ከውጭና ከግቢ ፖለቲክ ጋር መታገል ፡

(ሠ) ለጦር ወታደር ስንቅ በቶሎ እንዲደርስ ማሰብ ነው።

ይህን የመሳሰለውን ታላላቅ ጕዳይ እያከናወኑ እደሴ ተቀምጠው ሳሉ ፡ የእንግሊዝ መንግሥት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሰር ሳሙኤል ሆርና የፈረንሳዊ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ምሲዩ ፒዬር ላቫል እንደ ፈረንጅ ቁጥር ታኅሣሥ ፲ ቀን በፓሪስ ከተማ የተነጋገሩበትን የዕርቅ ድርድር ፡ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አማካይነት በቴሌግራም አስተላለፉላቸው። አኳኋኑም እንደሚከተለው ነው።

ማናቸውም በኢጣልያ መንግሥት ላይ የተደረገው ጭቆና ጦርነቱን ሊያቆመው ስላልቻለ ፡ በዓለም መንግሥታት ማኅበር የልዩ ልዩ አገር እንደራሴዎች ሆነው ይሠሩ የነበሩት ታላላቅ ሰዎች ፡ ሁለቱን ጠበኞች መንግሥታት ጉዳይ መከታተል የሚያስፈልገው በዕርቅ መንገድ ነው ሲሉ ለጉባኤው እየደጋገሙ ከማስታወሳቸው የተነሣ ፡ የቤልጅክ ጠቅላይ ሚኒስት ቫን ዚላንድ ባቀረበው አሳብ መሠረት እንደ ፈረንጅ ቍጥር በጥር ኅዳር ፪ ቀን ኮሚቴ ደኮአርዶናሲዮን የተባለው ስለዚህ ጉዳይ የፈረንሣዊና የእንግሊዝ መንግሥታት አደራ ይባሉ ዘንድ ቆረጠ። በዚሁም ጊዜ ስምምነቱ ከማኅበሩ ሥርዓት ጋር ሳይፋለስና ሳይቃወስ እንዲሆን፣ ደንቡንም ከማክበር ጋር እንዲፈጸም በሰፊው ተነግሮ ነበር። ስለዚህ ይህን የዕርቅ አሳብ በምን አኳኋን ለመወሰን እንደሚቻል ብዙ ምርምርና ሰፊ ክርክር ሲደረግበት ቆየ። በመጨረሻውም ጊዜ እንደፈረንጅ ቍጥር በታኅሣሥ ፯ና ፰ ቀን ቀጥለው የተመለከቱት መንግሥታት የኦፊሲዬል ሠራተኞች በፋሪስ ጉባኤ አደረጉ።

<u>በፈረንሳዊ መንግሥት በኩል።</u>

ምሲዩ ላቫል ፒየር (የምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)

ምሲዩ ሌጄ (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዋና ጸሐፊ)

ምሲዩ ዶሴን ኬንተን (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ክፍል ዲሬክተር)

<u>በእንግሊዝ መንግሥት በኩል።</u>

ሰር ሳሙኤል ሆር (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር)

ሰር ጆርጅ ክለርክ (በፓሪስ አንባሳደር)

ሰር ፔቴርሶን (በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለ ምሥራቅ ክፍል አማካሪ)

በነዚህ ከዚህ በላይ በተመለከቱት ሰዎች ጉባኤ የሚያሳርፍና የሚያሳዝን የዕርቅ አሳብ ተመሠረተ። እርሱም

፩ኛ ለኢጣልያ መንግሥት ትግሬና ውጋዴን በግዛት እንዲሰጠው ፡

፪ኛ በኢትዮጵያ ደቡብ በሚገኙት አውራጃዎች ላይ ሁሉ ሰፊ የኤኮኖሚክ መብት እንዲኖረው ፡ በሕዝብም አምጥቶ ሊያሰፍር እንዲቀፈድለት ነው። እንዲሁም ይህን ጥያቄ ለማስፈጸም ማባበያና ማግባቢያ ይሆን ዘንድ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት በአሰብ ወደብ ላይ በነጻ እንዲወጣና እንዲገባ የኢጣልያ መንግሥት ይፈቅዳል የሚል ተጨምሮበት ነበር።

አስታራቂዎቹ ለቫልና ሆር ከዚህ በላይ የተመለከተው ዓይነት የተመሠረተውን የዕርቅ አሳብ ለሁለት ጠበኞች መንግሥታት ካስታወቁ በኋላ እንዲሁ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ሁኔታውን አመለከቱ።

በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ተጠቂ ሆኖ ሳለ ፡ አጥቂው በኃይል ሊያስገድደው ከተነሣበት አሳብ ጋር ፈጽሞ የሚቃረብ አስተያየት የዓለም ማኅበር አባል ከሆኑ መንግሥታት የዲፕሎማቲክ ሰዎች በማቅረቡ እየተቃወመ ጉባኤው በተቻለ ፍጥነት ተሰብስቦ በሰፊእው ይመረምረው ዘንድ ጠየቀ። ይሁን እንጂ የጉባኤው ዋና ጸሐፊ ጥያቄውን አለተቀበለውም ነበር። ምክንያቱም በዚሁ አኳኋን ጉባኤው እየተነጋገረበት ስላ፣ ወደ ፊት ቆርጦ የሚያስታውቀውን አሳብ መጠበቅ የሚሻል መስሎ ስለታየው ነው።

ለቫልና ሆች ያቀረቡት ይህ የዕርቅ ድርድር፣ ተጠቂን በማስካስ ፈንታ አጥቂን መሸለምና ማበረታታት ነው ሲሉ ብዙ ሰዎች በቃልም ሆነ በጽሕፈት ወቀሷቸው። ይልቁንም ዴሊ ሄራልድ የተባለው ትራቫይስት የእንሊዝ መንግሥት በዚህ አስተያየት ላይ እንዲገኝ በመደረጉ የሚኒስትሮችን ምክር ቤት ከሰሰ። ይህን የመስለው የተጋጋለ መውቃወም በሕዝቡ ዘንድ እየተስፋፋ ስለሄደ እነሙሴ ኤደን ያደረጉት የማረጋጋት ሥራ አልበቃ ብሎ የእንግሊዝ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ስለሚሆነው ክርክር ያለውን አስተያየትና በፓሪስ የተመሠረተውን የዕርቅ ድርድር ሁኔታ የሚገልጽ አንድ መጽሐፍ ተዘጋጅቶ እንዲነዛ አደረገ። ይሁን እንጂ

«ከውርደት ጋራ ሰላም ምን ዋጋ አለው?» በማለት ላይ የተነሣው ሕዝብ ምንም በተሸነፈ አኳኋን ልዩ ልዩ አስተያየት ቢቀርብለት ስሜቱን ሊለውጠው አልቻለም ነበረና ከብዙ ክርክር በኋላ ሙሴ ለቫልና ሙሴ ሆር ከሹመታቸው ተሻሩ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከእንግሊዝ ከፈረንሳዊ መንግሥታት የዲፕሎማቲክ ሰዎች የቀረበውን የዕርቅ ድርድር በመቃወም ስለ አቀረቡት አቤቱታ ፍጻሜውን እየተጠባበቁ በደሴ ከተማ ሳሉ ታኅሣሥ ፱ ቀን የመሻራቸው ዜና ደረሳቸው።

ግርማዊነታቸው በደሴ ሆነው ሌላውን ሥራቸእውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በውስጥም ሆነ በውጭ አንዳንድ የሚያሳዝን ነገር ይደርሳቸው ነበርና የላቫልና የሆር የዕርቅ ድርድር ደርሷቸው ሳለ ፡ እንዲሁ ደግሞ ደጃች ገሡሠ የተባለው የጎጃም ሰው ፡ ከአዝማቹ ከራስ እምሩ ከድቶ ወደ ሀገሩ መመለሱን ሰሙ።

ይህ ሰው ጥቂቶቹ መሰሎቹን ይዞ እጐጃም እንደ ደረሰ በዘማቾች ቤትና ገንዘብ ላይ ፡ የማይገባ ሥራ እየሠራ የተከላካዮቻችንን ሕሊና በሁለት ወገን ስለከፈለው ከአዲስ አበባ በግራዝማች ሣህሌ የሚመራ ጦር ይታዘዝ ዘንድ ግርማዊነታቸው ፈቀዱ። እንዲሁም ለጊዜው በዚህ በከንቱ ሥራ ለመተባበር የመንደር ጎረምሶች ተነሥተው ነበርና ለዚሁ ቀጥሎ የተመለከተውን አዋጅ አዘጋጅተው እንዲበተን አደረጉ።

«ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ።

የጎጃም ሰው ከርስትህ የሚነቅል ሚስትንና ሴት ልጅህን በኃይል እየወሰደ የሚያረክስ ፡ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖትክን የሚለውጥ ኢጣልያንን ያህል ጨካኝ ጠላት መጥቶ ሳለ ስለ አገርህ ስለ ኢትዮጵያ ነፃነትና ስለ ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖት ደምህን ከማፍሰስ በቀር ትክደኛለህ ብዬ

አልጠረጥርህም ነገር ግን ደጃች ገሠሠ ፡ ፊታውራሪ ታምራት ፊታውራሪ ገሠሠ ንጉሠ ፡ ፊታውራሪ ዘለቀ ካሣ ፊታውራሪ ዘለቀ ወሌ ቀኛዝማች አየለ ኃይሉ ፡ ቀኛዝማች መርድ ዋሴ ፡ ቀኛዝማች ዘለቀ አሰጌ አገራቸውን ኢትዮጵያንና ንጉሠ ነገሥታቸውን እኔን ከድተው ከዘመቻ መመለሳቸው ፡ እንክርዳድ በስንዴ መካከል እንደሚበቅል ያህል ነው። ቢሆንም ለጊዜው ያገርህን የጐጃምን ስም ለማጥፋት ነው። እንጂ ሌላውን ይቅርና ራሳቸውን ለማዳን እንደማይችሉ ታውቀዋለህ።

እነ ፡ ደጃች ገሠሠንና እነ ፊታውራሪ ታምራትን ተከትለህ ከዘመቻው ወደጐን የተመስህ ሰው ሁሉ ጥፋቱ በአለቆችህ በይሁዳዎቹ ላይ ነው እንጂ ባለፈው ምሬሃለሁ። ነገር ግን የኛን አዋጅ ጥሰው የጳጳሱን ውግዘት አፍርሰው አገራቸውን ኢትዮጵያን ከደው መሪ ሆነው ከዘመቻ የመለሱህን እነዚህን ጠላቶችን በሄዱበት ሥፍራ እየተከተልህ ያዝልኝ። ተከትለህ ስትወሳልት ፡ የተገኘህ እንደሆነ ባላገርም ለኛ ሳትረዳ ቀርተህ በቤትህ ፡ አሳድረህ እህልና ወሀ ሰጥተህ የተገኘህ እንደሆነ ምሕረት የሌለው ቅጣት እቀጣሃለሁ።»

ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም

እንዲሁም ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አዋጅ ከተነዛ በኋላ ጳጳሱ አቡነ ቄርሎስ ገሠሠን የተከተልክ አውግዝሃለሁ ሲሉ ለጎጃም ካህናትና መኳንንት ለመላውም ሕዝበ ክርስቲያን ጽፈው አስታወቁ። ቃሉም ቀጥሎ የተመለከተው ነው።

መልክት ዘፈነዋ ቄርሎስ ፡ ሊቀ ጳጳሳት

<u>ዘኢትዮጵያ።</u>

ገብሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወልዱ ለቅዱስ ማርቆስ ወንጌላዊ።

ይድረስ በጐጃም አውራጃ ካላችሁ የተባረካችሁና፣ የከበራችሁ ፡ በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት የዳናችሁ ልጆቼ የመንፈስ ቅዱስ ሰላም ከጸሎቴ ጋራ ለናንተ ይሁን።

ልጆቼ ሆይ የኢጣልያኖች አሳብ ሁሉ ክፋት የሌለበትን ደጉንና ክርስቲያኑን የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በሱ እያጣሉና እያፋጁ በኋላ እነሱ ያለ ችግር ሰተት ብለው ገብተው እርስታችሁንና ገንዘባችሁን ለራሳቸው ለመውሰድ ወንድ ልጆቻችሁን ላሽከርነት ሴት ልጆቻችሁን ለግርድና ለማድረግ ነው። ይህን ከዚህ ቀደም ብዙ ጊዜ ጀምረውትና መክረውት ነበር ነገር ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ እግዚአብሔር ያልተለየው ነውና ነገሩን ፡ እየተመራመረ ኢጣልያኖች በኢትዮጵያ የሚሠሩት ሁሉ ፡ የተንኰል ሥራ መሆኑን ስለተረዳው እርስ በርሱ የማይጣላና የማይዋጋ መሆኑን ባወቁት ጊዜ ከዚህ ቀደም የዛሬ ፵ ዓመት እንዳደረጉት ዛሬም በብዙ መሣሪያና በሠራዊታቸው ኮርተው ለጦርነት ቢመጡ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ ከመላው ፡ የኢትዮጵያ አርበኞች በ፩ ልብ ሆነው ወደ ዘመቻው ለመሄድ ቁርጥ አደረጉ። ኢጣልያኖች ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከታላቁ እስከ ትንሹ ባንድ ልብ ሆኖ ስለ ሀገሩ ነፃነት በኃይል ለመዋጋት መነሣቱን በሰሙ ጊዜ በግንባር ፊት ለፊት ተጋጥመው ለመዋጋት የማይችሉ መሆናቸውን ስለተረዱት ተንኰል የማታለልና የሐሰት ቃል እየጻፉ በአየር ላይ በአውሮፕላን እያበረሩ ይበትኑ ጀመሩ።

በጐጃም እንደ ይሁዳ የተረገመው ደጃች ገሠሠ ፡ ለኢጣልያኖች ረዳት ሆኖ መነሣቱን ብሰማ በርሱ ምክንያት የክርስቲያኑ አገር ጐጃም እንዳይጠፋ አስቤ ባላገሩና ወታደሩ የሱን ነገር እንዳይሰሙ፣ እሱንም እንዳይከተሉ እህል ውሀም እንዳሰጡት በቤታቸውም እንዳያሣድሩት ደጃች ገሠሠብ ተከትሎ አገሩን ኢትዮጵያንና ንጉሠ ነገሥቱን የከዳ ሰው ቢሞት ካህናቱ እንዳይፈቱት ፡ በቤተ ክርቲያንም እንዳይቀብሩት በታኅሣሥ ፰ ቀን የተጻፈ የውግዘት ፡ ቃል ልኬ ነበረ። ግን ደጃች ገሠሠ የከሐዲ ሥራ ሠርቶ እስካሁን በጐጃም አውራጃ መቀመጡ የኔ የውግዘት ቃል ባይደርስላቸው ይሆናል እንጂ

ደርሷችሁስ ቢሆን እስካሁን በጐጃም ውስጥ ታቆዩታላችሁ ብዬ አልጠራጠርም። አሁንም ከዚህ ቀደም እንደጻፍንላችሁ ቃል ንጉሠ ነገሥቱን የከዳውን አገሩን ኢትዮጵያን ለባዕድ ለኢጣልያ አሳልፎ ለመስጠት የተነሣውን ደጃች ገሠሠንና ሌላውንም እንደርሱ ያለውን ከሐዲ አትከተሉ። ኢጣልያኖችም ከ፫ሺ ዓመት ይበልጥ በነፃነት የኖረችውን ኢትዮጵያን ለመውሰድ ፡ እርስ በርሳችሁ የሚያጣላና ደም የሚያፈስ ተንኮል የማታለልና የሐሰት ቃል እየጻፉ ፡ በአውሮፕላን ቢበትኑላችሁ አትመኑ። ምንም ቢሆን ከእናት ሞግዚት እንዳትሻል ታውቃላችሁና ፡ ከሰሎሞንና ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ተያይዞ ከመጣው ከጥንታዊ ንጉሠ ነገሥታችሁ ኢጣልያ የሚሻል እንዳይመስላችሁ አስጠነቅቃችኋለሁ ይኸንን ከዚህ በላይ የተናገርኩትን ምክሬንና ቃሌን ባትሰሙት ግን እንደ አርዮስ አውግዣችኋለሁ ፡ እረግሜአችኋለሁ። ጥር ፱ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ.ም።

## ምዕራፍ ፲።

## የልዑላን ራስ ካሣና ራስ ሥዩም ፡ የራስ ሙሉጌታም ፕላን።

ከኅዳር ወር ጀምሮ ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም ደብዳቤ በመጻጻፍ መልካም ግንኙነት ነበራቸውና ስለ ጦሩ ማስማራት ቃል በቃል ተገናኝተው በሰፊው ይነጋገሩበት ዘንድ ልዑል ራስ ካሣ ከመጠየቃቸው የተነሣ ቀጠሮ ተቀባበሉ። ይሁን እንጂ ተንቤን በሁለት በኩል ሊመጣ የሚችለውን የጠላት የጉዞ መሥመር ለመቁረጥ የተመቸ ስፍራ ስለሆነ ሁለቱ የጦር መሪዎች ማዕከላዊ በሆነ ቦታ ላይ ተገናኝተው በሚነጋገሩበት ጊዜ ጠላት አዘንግቶ ተንቤንን አንዳይዝባቸው መጠባበቅ አስፈላጊ ከመሆኑ የተነሣ የሁቱም መሳፍንት ሠራዊቶች ተባብረው ለመከላከል ይችሉ ዘንድ «ሰው ይላክልኝ» ሲሉ ልዑል ራስ ሥዩም ጠየቁ።

በመጨረሻው ልዑል ራስ ፡ ሥዩም ወደ ልዑል ራስ ካሣ ተጉዘው ኅዳር ፳ ቀን ሙጃ ከሚባል ተራራ ተገናኙ። እንዲሁም የፍቅር ሰላምታ ከተሰጣጡ ፡ በኋላ ለተከታዮቻቸው መልካም የራት ግብዣ ተደረገ።

በማግሥቱ ፡ ሁለቱ ልዑላን ስለ ጦሩ አመራር የሚያስፈልገውን ፕላን ለማዘጋጀት ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ጉባኤ አድርገው ዋሉ። ይሁን እንጂ ይህ ጉባኤ በሚደረግበት ጊዜ የጠላት አኤሮፕላኖች ፡ መጥተው ቦምብ መጣል ስለ ጀመሩ ስለ ጥንቃቄ የጉባኤው ሥራ ቆመ። በዚሁም ጊዜ ሕዝቡ ያለማቋረጥ በአኤሮፕላኖቹ ይተኵስባቸው ነበር። አኤሮፕላኖቹ የተሸከሙትን ቦምብ አራግፈው ሲመለሱ በተራራው ሸለቆ ዝቅ ብለው ነበርና ሕዝቡ በተኰሰባቸው መሣሪያ ተመትተው ሊወድቁ ስለመሰለው እልል እያለ ከተደበቀበት ወጣ። ነገር ግን ልዑል ራስ ካሣ የአኤሮፕላኖቹ ፍጻሜ የሚመረምሩ መልክተኞች ቢልኩ የደረሱበትን ሳያውቁ ፡ ከነጂዎች የወደቀ አንድ ኮትና አንድ የመንደር ማመልከቻ ካርታ አግኝተው ስለ ተመለሱ ምናልባት ዘልቀው ይሆናል ፡ ተባለ። ስለሆነ በአኤሮፕላኖቹ አደጋ ጥቂት ሰዎች ሞተው ነበርና በልቅሶና በቀብር ምክንያት ጉባኤውን ለመቀጠል ሳይቻል ቀርቶ ለማግሥቱ ተቀጠረ።

ለኅዳር ፲ ቀን በተሰጠው ቀጠሮ አስቀድሞ የተጀመረውን ምክር በመቀጠል በሰፊው ተነጋገሩበት ተከራከሩበትም። በማናቸውም ወገን ለጉባኤው የቀረበው ልዩ ልዩ አሳብ ከተጠና በኋላ ፡ በዚያ ጊዜ የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉጌታ በጉዞ ላይ ነበሩና እሳቸው እስኪደርሱ ተጠብቆ በኅብረት ፡ የመረዳዳት ጦርነት እንዲያደርጉ አብዛኛው ወገን ስለ ቆረጠ ስምምነቱ በዚሁ ተፈጸመ። ነገር ግን ልዑል ራስ ካሣ በምክር የተቆረጠውን አሳብ ለንጉሠ ነገሥቱ ለማስታወቅ አስበው ሳሉ የቴሌፎኑ መስመር በባላገሮች በመበላሸት ምክንያት ችግር ሆነ። ስለዚህ ልዑል ራስ ካሣ የዋጅራትን ባላባቶች ጠርተው ይህን የመሳሰለው የአገርን ሰላምና ጸጥታ የሚነሣው ነገር እንዳይደረግ ያስቡበት ዘንድ አስጠነቀቋቸው። እንዲሁም

ባላባቶቹ ለጊዜው የቅንነትና የመልካም አሳቢነት የመቈርቈርም መንፈስ ስለታየባቸው የልብስና የገንዘብ ሽልማት ሰጧቸው።

በላይኛው ፓራግራፍ እንዳታወቅነው ልዑል ራስ ሥዩም ከልዑል ራስ ካሣ ጋራ ለመገናኘት ገንቤንን ለቀው በተጓዙበት ጊዜ ተንቤን በጠላት እጅ እንዳትገባ ወታደሮች ከሁለቱም ወገን ተደርገው እንዲከላከሉ አስፈላጊነቱን ተመልክተው ነበርና በዚያ መሠረት ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ፡ ደጃዝማች ኃይሉ ተስፋዬ ጸሐፌ ትእዛዝ አፈወርቅ በጠቅላላው ፫ ደጃዝማች በበርጅሮንድ ለጥ ይበሉ ገብሬ አዝማችነት በግምት ከ፲ሺ ወታደር ጋራ ተላኩ። ይሁን እንጂ እነዚህ የጦር ሹማምንቶች ከመድረሳቸው አስቀድሞ ተንቤን በጠላት እጅ ተይዞ ኖሮ ከከተማው ራቅ ብሎ መስፈር ግድ ሆነባቸው።

የራስ ሙሉጌታ መቃረብ በተሰማ ጊዜ ልዑል ራስ ካሣ የሚበቃቸውን ያህል ዋሻ እንዲዘጋጅ እንዲጠረግ ለወታደራቸው ትእዛዝ ሰጡ። ነገር ግን በዚያ የነበሩትን ዋሻዎች አስቀድመው ከነበሩት ከነደጃዝማች ወንድ ወሰንና ከነደጃዝማች አድማሱ ከነፊታውራሪ አንዳርጌና ከሌሎችም ታላላቆች ሰዎች ተርፈው ፡ ራስ ሙለጌታን ለማዳበል የማይችሉ ነበረ። ቢሆንም በመጣበብ ይደላደሉ ዘንድ ግድ ሆነ። እንዲሁም ከጥቂት ቀኖች ጀምሮ ይጠበቁ የነበሩት ራስ ሙሉጌታ ከልዑል ራስ ካሣ ሠፈር ወደ ታኅሣሥ ወር መጀመሪያ ደረሱ። እንዲሁም ፫ቱ ራሶች በተለየ ምክር እያደረጉ ሰነበቱ። በምክሩም የተወሰነው ልዑል ራስ ሥዩምና ልዑል ራስ ካሣ ወደ ተንቤንና ወደ ገረአልታ ራስ ሙሉጌታ ወደ አጉላ ምሥራቅ እንዲጓዙና ግማሻቸው መንገድ በመቁረጥ ግማሻቸው ፊት ለፊት በመግጠም ለመዋጋት ነበር። ይኸንኑ ፕላን ለመፈጸም እየተዘጋጁ ሳለ፣ የጠላት ጦር ወደ ፊት መግፋቱን ደጃዝማች ጨቡድ የተባሉ የልዑል ራስ ካሣ ሰው አይተው ስለ አስታወቁ ጦራቸውን ቀስቅሰው ወዲያው ጉዞ ተጀመረ። እንዲሁም የጠላትን ጉዞ መስመር በመገመት በአይቤቶና በአላጌ በኩል ሲያስጠበቁ ጠላት ወደአልታሰበበት አንፃር ስላመራ ሶስቱ ራሶች ጉዞአቸውን ወደ ፊት ይቀጥሉ ዘንድ አሰቡ። ይሁን

እንጂ አላጌን የሚከበው ተራራ ለቆ ወደ ፊት ማለፍ ጠቃሚ አልመሰላቸውም። በእውነትም እነዚህ ስፍራዎች በተፈጥሯቸው ምሽግነት ያላቸው ስለሆኑ መልቀቁ አስፈላጊ አልነበረም። ስለዚህ ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም በአላጌ ዙሪያ ካሉ ተራራዎች በስተግራ ፡ ራስ ሙሉጌታ በስተቀኝ ያለውን ክፍል ይዘው ሰፈሩ። በዚያን ጊዜ በአይቤቶ ላይ ምናልባት ፳ ሺየሚያህል ጦር ፊዜርብ ሆኖ ይጠብቅ ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በአላጌ ላይ እንዲቆዩ የቆጠሩትን አሳብ በማሻሻል ወደ ፊት ጉዞ ጀመሩ። እነዚህ ፫ቱ ራሶች አብረው በሚጓዙበት ጊዜ ከሠራዊቱ ብዛት የተንሣ መንገድ አልበቃ ብሏቸው ነበርና ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ሥዩም ወደ ተንቤን ከዚያም አልፈው ወደ ገረአልታ ሄደው ከአድዋና ከአዲግራት ወደ መቀሌ ከሐውዜን ወደ ተንቤን በሚመጣው የጣላት ጦር ላይ አደጋ እንዲጥሉ ራስ ሙሉጌታ ግን በእንጣሎና በአምባ አራዳም በኩል እየተጠበቁ እንዲቆዩ ቀረጡ።

## ምዕራፍ ፲፮።

## የባዶሊዮ ፕላን።

እስከ መቀሌ መያዝ ድረስ የኢጣልያን የጦር ሠራዊት ይመራ የነበረው ጀኔራል ደቦኖ እግሩን በለማፋጠኑና ወደ ፊት ባለመግፋቱ መሶሊኒ ቅር መሰኘቱን ምንም እንኳ ለርሱ ባይገለጽለት በሌሎቹ ዘንድ የታወቀ ነበር። ስለዚህም ቀደም ብሎ በግብጽና በእንግሊዝ ሱዳን በኩል ሌላ የጦር ግንባር ለመክፈት ይቻል እንደሆነ በመመርመር አመካኝቶ ያን ጊዜ የቅኝ አገር ክፍል ዋና ጸሐፊ የነበረውን ማሬሻሎ ባዶሊዮን ከሴሶና ጋራ ልኮት ነበርና ፡ በተመለከተው መጠን የጦርነቱን ሁኔታ በማናቸውም አኳኋን ከርሱ በቀር ሊያውቀው ለመራ የሚችል የለም ሲል ለጄኔራል ደቦኖ ምትክ አድርጎ እንደገና ላከው። በጄኔራል ደቦኖም ላይ ያለው የቅሬታ ስሜት እንዲሸፈን

ጦርነቱን በተከናወነ አካሄድ እስከ መቀሌ በማድረስህ የኢጣልያ ማሬሻሎነት ማዕርግ ፡ ሰጥቼሃለሁ ሲል ደለለው።

ማርሻሎ ደቦኖ በመጀሪያው ጊዜ የመሶሊኒ ፡ ባለሟልና ምሥጢረኛ እንደነበረ ነበር። በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በጳደይ ወራት ነበርን። በምሥራቃዊ አፍሪካ ይደረግ ዘንድ ስላለው ጦርነት ዱቼ ለማንም አልተናገረም። እርሱና እኔ ብቻ ይሆን ዘንድ ያለውን ነገር እናውቅ ነበረ ፡ ሕዝብ ሊያውቀው የሚችል ግልጽ ነገር ይኖር ዘንድ አይገባም ነበረ»።

ከዚህም በቀር የወልወል ግጭት ከተነሣ ካ፲፫ ቀን በኋላ «የአበሻን ጉዳይ ለመቈጠር የሚያመለክቱ ድርጅቶችና ፕላን» በሚል አርእስት ሙሶሊኒ በአምስት ግልባጭ ብቻ ያዘጋጀውን ረዥም አሳብ መጀመሪያ ጊዜ ለመመልከት ይቻለ ማርሻሎ ደቦኖ ነው። እንዲሁም በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በሐምሌ ወር መጨረሻ «የጦርነቱ ግጥሚያ ከመጀመሪያው መብረቃዊ (እንደመብረቅ ድንገተኛ) መሆን ይገባዋል ዝግጁም ለመሆን ከ፩፻፳ ቀን በቀር የለዎትም» ብሎ ፡ ምሥጢረኝነትና ባለሟልነትን ያስረዳል። ይህ ሁሉ ደቦኖ በሙሶሊኒ ዘንድ የነበረው ምሥጢረኝነት ባለሟልነት ያስረዳል።

ጦርነቱ ከተጀመረ በኋላ ግን ያ ሁሉ ምሥጢረኛነት ቀረና ፡ መጨረሻው ሺረት ሆነ።

ማርሻሎ ባዶሊዮ ጓደኛውን ደቦኖን ያስነቀፈው ዝግ ማለቱ እንደ ሆነ ስለሚያውቅ የጦርነትን ሕግ ሣይጠብቅ በማናቸውም አደራረግ፣ ማለት መርዝ መበጣልና ለጦርነት ባልተሰለፉት ሕዝቦ ላይ ቦምብ በመወርወር ሥራውን ቀጠለ።

ይህም ሕግ ተላልፎ የሚሠራው ግፍ ምክንያት አለው ለማሰኘት እንደ ፈረንጅ ቊጥር በ፲፰፻፷፯ ዓ.ም ሴን ፔቴርዝቡር ላይ የተከለለውን ፡ ከዚያም በኋላ በሕግ መከልከሉ እየተረጋገጠ የታወቀውን ዱም ዱም ጥይት

ኢትዮጵያውያን በጦርነት ይሠሩበታል ሲል በቴሌግራም አስታወቀ። ይሁን እንጂ ይህን ዱም ዱም የተባለ ጥይት ወዲያው ጦርነቱ እንደተነሣ ኢጣልያኖች ይሠሩትበት ኔበረ። ይኸውም ሊታወቅ በጅጅጋ የነበረው የአሜሪካ ቀይ መስቀል አባል ዶክቶር ሮቤርት ሾክማን ባደረገው ምርመራ ከኢጣልያ አኤሮፕላኖች መትረየት ተኲስ የተነሣ የሱፍ አህመድ የተባለው የኢትዮጵያ ዜጋ በዱም ዱም ጥይት መቁሰሉን አረጋግጦ ተናግሯል። ስለዚህ ጥይቱን ኢጣልያኖች በአኤሮፕላን አምጥተው እንደነዙት የተሠወረ አይደለም።

የኢጣልያ መንግሥት በዚህ በዱም ዱም ጥይት ምክንያት በማስመሰል ላቀረበው አቤቱታ የኢትዮጵያ መንግሥት እያስተባበለ በታኅሣሥ ወር ማጋመሻ መልስ ሰጠ። ይልቁንም ይህን የመሣሰለውን መሣሪያ ለማደራጀት የኢትዮጵያ መንግሥት ፋብሪካ የሌለው ከመሆኑ በላይ ማናቸውንም የጦር መሣሪያ የሚያመጣው ከጐረቤቶቹ ፡ መንግሥታት ስለ ሆነና ያውም በጥብቅ እየተመረመረ ስለሚላክ ይህ በሕግ የተከለከለ መሣሪያ ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ጎረቤቶቹ መንግሥታት ይፈቅዳሉ ብሎ ለማመን በጣም የሚያስቸግር ነው ሲል ማስረጃውን አቀረበ። ከዚህም በቀር ኢጣልያኖች የዱም ዱም ጥይት ክምር አገኘንበት ብለው ባስታወቁበት ክፍል በተፈሪ ከተማ የነበረው ማዦር ዶቴ የጻፈው ደብዳቤ ለምስክርነት ያገልግል ዘንድ ፓሪስ በነበረው በኢትዮጵያ ሚኒስትር አማካይነት ላከው። ይኸውም ደብዳቤ ማጆር ዶቴ የኢትዮጵያ የክፍል ጦር እየመራ በነበረበት ጊዜ ሁሉ ዱም ፡ ዱም ጥይት በፍጹም አለመኖሩን ያረጋግጥ ነበረ። የሆነ ሆኖ የኢጣልያ መንግሥት አስቀድሞ ያቀረበውን ክስ በማረጋገጥ ላይ ጸና። ማስረጃም ሲያቀርብ ኢጣልያኖች እየገፉ በያዙዋቸው ልዩ ልዩ ቦታዎች ዱም ዱም ጥይት እየተከመረ ተገኝቷል ፡ ከዚህም በቀር በደምበጉና በዓቢይ አዲና በሌሎችም የአደጋ ጦርነት በተደረገባቸው ስፍራዎች የቆሰሉት የኢጣልያ ወታደሮች በዱም ዱም ጥይት መሆኑ ተመርምሯል ፡ ከነዚሁም አንደኛው ኰሎኔል ሊቤራቲ ነው ብሏል።

ይልቁንም ማሬሻሎ ባዶሊዮ ያቀረበው ማስታወሻ ይህ ዱም ዱም የተባለው ጥይት ከእንግሊዝ አገር የመጣ ነው የሚል ስለ ነበረ በኢጣልያና በእንግሊዝ መንግሥታት መካከል ሞቅ ያለ የዲፕሎማሲ ንግግር ተጀመረ። እንዲሁም የኢጣልያ መንግሥት በዚህ ዱምዱም ጥይት ምክንያት በሎንዶን በሚገኘው ኤሊ ብራዘርስ ሊሚትድ በተባለው የመሣሯ ፋብሪካ ቤት ያቀረበው ክስ በታኅሣሥ ወር ከዠኔብ ደርሶ ነበርና የእንግሊዝም መንግሥት ይህንኑ እየተቃወመ ለዓለም መንግሥታት ማኅበር ለማስረዳት በሚቻልበት መንገድ ተከራከረ። ነገር ግን የኢጣልያ መንግሥት ምሥጢራዊ በሆነ ተንኮል የመሣሪያው ኤቲኬት ነው ሲል አንድ ማስታወሻ ስላቀረበ የተሰወረው እስኪገለጽ ድረስ ነገሩ በሰፊው ሊያከራክር ቻለ። እንዲያውም ከ፳፪ ዓመት አስቀድሞ ወደ አፍሪካ ለአውሬ አደን የሄዱ ሰዎች ይዘውት ሲያልፉ ምናልባት በኢትዮጵያውያን እጅ ገብቶ ይሆናል እስከ ማለትም ተደረሰ። ነገር ግን የኢጣልያ መንግሥት በመጀመሪያው ጊዜ ያቀረበው ክስ አልበቃ ብሎት እንደገና በእንግሊዝ አገር የሚገኘው የጦር መሣሪያ ፋብሪካ «ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚላክ መሣሪያ» በሚል መጠቅለያ የታሠሩ መሣሪያዎች አሰናድቶ በሎንዶን ለሚገኘው የኢትዮጵያ ሚኒስትር ከደብዳቤ ጋራ ልኮለታል ሲል የፋብሪካውን ኤቲኬት ጭምር በጋዜጣ ለማውጣት ደፈረ። ስለሆነ ይህ ብዙ ጊዜ ያከራከረው ጉዳይ በመጨረሻው በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ተገለጸ።

ሃንሪ ሎውሬንሣ የተባለው የእንግሊዝ ተወላጅ ፡ ኰሎኔል ፔሮድ ሎፔዝ እባለሁ ብሎ ከቢርሚንግሀም ፋብሪካ ዲሬክሲዮን ከቀረበ በኋላ በማስመሰል የተጻፈውን የውሸት ደብዳቤ አሳይቶ የኢትዮጵያ መንግሥት መልክተኛ ነኝ ለማለት ደፈረ። ይህ በራሱ የተሰየመው የኢትዮጵያ መንግሥት ወኪል በኢትዮጵያ መንግሥት ስም የጦር መሣሪያ እገዛ ዘንድ ታዝዣለሁ ሲል ምክንያት ሰጥቶ የዋጋ ድርድር እንደ ጀመረ ፡ ደግሞ በኢትዮጵያ አውራጃ የዱር አውሬዎችን ለማደን የዱም ዱም ጥይት እንደሚያስፈልገው ተናገረ። በዚህ ጊዜ የዱም ዱም ጥይት ለዓይነት ያህል

(ኤሻንትዮ) ለማግኘት ስለቻለ ወስዶ በሎንዶን ለሚገኘው የኢጣልያ አምባሳደር አስረከበው። ከዚህ በኋላ ዓይነቱን ምክንያት በማድረግ የኢጣልያ መንግሥት ምሥጢራዊ የሆነ ተንኮል ሊያስወራ ቻለ።

ወደ መጀመሪያው አሳብችን እንመለሳለን።

ባደሊዮ ለግፈኛነቱ መሽፈኛ ምክንያት እንዲሆነው የፈጠረው ነገር ሁሉ ምንም እንኳ ከመገለጽ ባይዘገይ በእልከኝነት የሚሠራው የበለጠ ነበር። ስለዚህ እርምጃውን ለማፋጠን የሚችልበትን ማናቸውም አደራረግ ሳይቆጥብ በመፈጸም የጦር ሠራዊቱ ተንቤንን ለመያዝ ቻለ።

## ምዕራፍ ፲፪።

## የተንቤን የመጀመሪያ ጦርነት።

በምዕራፍ ፲ እንደተናገርነው በበጅሮንድ ፡ ለጥ ይበሉ አዝማችነት ተንቤንን እንዲይዝ የተላከው ጦር ከመድረሱ አስቀድሞ የተንቤን ከተማ ዓቢይ ዓዲ በጠላት ተይዞ ነበረ። ስለዚህ የኛ ወታደሮች ፡ ተሐማ በሚባለው ላይ ሰፍረው ምን ፡ ማድረግ እንደሚገባቸ እያሰቡ ሳሉ በድንገት የጠላት ጦር ገጠማቸው። እንዲሁም ቀኑን ሙሉ ሲዋጉ ውለው ጨለማው ስለገላገላቸው ሁለቱም ወገኖች ሰፈራቸውን ሳይለቁ አደሩ። ነገር ግን አንዱ ወገን ፡ የሌላው ወገን ኃይል ሚዛን ያለ ስለመሰለው ማለት እርስ በርሳቸው ሰለተገማመቱ በየበኩላቸው ሰፈራቸውን ለቀው ወደ ኋላ ለመመለስ ምክር ያደርጉ ነበር። እንዲሁም የኛ ወታደሮች በዚህ አሣብ ላይ በሚከራከሩበት ጊዜ ኢጣልያኖች ዐቢይ ዓዲን ለቀው ወደ ኋላ መመለሳቸውን ያየ አንድ ለስለላ ተልኮ ወታደር ስላነጋገራቸው ከተማውን ለመያዝ ቻሉ። ከዚያም አልፈው መስፋፋት ጀመሩ።

ከጥቂት ቀን በኋላ ማለት ጥር ፩ ቀን ልዑል ራስ ካሣ ከአቢይ አዲ ከተማ ስለ ደረሱ ፡ በደብረ አምባ ተራራ ላይ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ወጥተው ፫ ወይም ፮ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ በሹማርዌ አጠገብ የሰፈረውን የጠላት ሁኔታ ለመመልከት ቻሉ። ከዚህ በኋላ በዓቢይ አዲ አቅራቢያ የሚገኙ ከአኤሮፕላን አደጋ መጠለያ የሚሆኑ ዋሻዎች በመጠኑ ስለ ነበሩ ጥቂቶቹ መኳንንቶች በመገባበዝ ሊስተናገዱባቸው ሲችሉ የቀሩት በመረዳዳት አዲስ መጠለያ ያሰናዱ ጀመሩ። በዚያው ሰሞን ፡ ኢጣልያኖች በማይ በለስ አሻጋጋሪ ወደ ደብረ እምባና ወደ ወርቅ አምባ መድፋቸውን አልበው እሳት ይተፉበት ነበር። ከዚህ በኋላ በልዑል እራስ ካሣ የሚመራው ጦር በሚከተለው አኳኋን ስፈር አድርጎ እንዲጠባበው ታዘዘ።

ሀ) ደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ የዐቢይ ዓዲን ምሥራቅና ኤርበዶሮን እንዲሁም ከደብረ አምባ አድርገው ያዙ።

ለ) ደጃዝማች አበራ ፡ ካሣ በዙሪያው ካሉ ተራሮች ጋራ የዐቢይ ዓዲን ከተማ በሞላውና የደብረ አምባን ምዕራብ ከፍለው ያዙ።

ሐ) ደጃዝማች አድማሱ ብሩ (የጁ) ከደብረ አንሳ ምዕራብ ከፍለው ያዙ።

መ) ፊታውራሪ አንዳርጌ (ላስታ) የደብረ አምባን ሰሜን በከፊልና የወርቅ አምባን ተዳፋ ዙሪያ ያዙ። እርሳቸውም ግንባር ቀደም ፡ ወይም ቃፊር መሆናቸው ነው።

ሠ) የልዑል ፡ ራስ ሥዩምና የበጅሮንድ ለጥ ይበሉ ሠራዊቶች የደብረ አምባን ተዳፋና በኤርባ ደሮ የሚገኘውን ክፍል ያዙ።

በዚያው ሰሞን ልዑል ራስ ካሣ በደብረ ዓምባ ላይ መድፍ አስጠምደው የኢጣልያንን ሰፈር ባሻጋጋሪ አስደበደቡት። ስለዚህ የኢጣልያ አኤሮፕላኖች ብድር ለመክፈል ሲሉ ፡ ፋታ የማይሰጡ ሆነ።

ጥር ፲፩ ቀን በ፮ ሰዓት ግድም እግረኛ የጠላት ጦር መጣ ተባለና ተለፈፈ። ስለዚህ ወታደሩ እንደ ቀትር ንብ ተቀስቅሶ ይጐርፍ ጀመረ። ነገር ግን ጦረኞች ሳይሆኑ ከብት ለማጠጣት የተላኩ ባንዶች ኖረው ከብቶቻቸውን ጥለው ስለሸሹ የኛ ወታደሮች ጥቂቶቹን ማርከው ወደ ሰፈራቸው ተመለሱ። እንዲሁም በዚያው ሰሞን ደጃዝማች ወርቅነህ በማልፋ በኩል ከጠላት ፡ ጋራ ጦርነት አድርገው ስለቆሰሉ ፡ ደጃዝማች ወንድ ወሰን ለእርዳታ እንዲደርሱላቸው ተደረገ።

በመጨረሻውም ጥር ፲፫ ቀን በአንድ ሰዓት የጠላት ጦር ወደ ጢኒ እየገፋ መምጣቱ ፡ ስለተሰማ የኛ ወታደሮች ለመከላከል ተሰለፉ። ቀጥሎም የላስታና የየጁ ጦር በምዕራብ ሲገጥም የትግሬ ጦር በደቡብ ምዕራብ ወደ ፊት ይገፋ ጀመር። እንዲሁም የቀረው የጦር አለቆቹ በሚያመለክቱት በልዩ ልዩ ግንባር ተሰልፎ መከላከል ጀመር።

በ፫ ወገን ፡ የገፋው የጠላት ጦር ይልቁንም ቬንቲ ኦቶ ኦቶብሬ የተባለው የካሚቻኔራ ክፍል ስፍራውን ለቆ በመጣበት ፡ ይመለስ ዘንድ በኢትዮጵያ ጦረኞች ተገደደ። ተኝቶ ወይም መከታ ሰጥቶ በሩቅ የሚደረገው የነፍጥ ጦርነት የወኒን አኳኋን ለማስደሰት ስላልቻለ የኢትዮጵያ ጦረኞች እንደ ልማዳቸው በጐራዴ ገቡበት። ነገር ግን የጠላት ወታደሮች በየጐናቸው ያንጠለጠሉት ፡ ሳንጃ ለእይታ ብቻ ከመሆኑ በቀር ለጐራዴ መልስ አድርገው ሊሠሩበት አልቻሉም ነበርና መወዳሪያቸው የእጅ ቦምብ ብቻ ሆነ።

በዚያን ዕለት ከሁለቱም ተዋጊዎች ወገን የወደቁት ወታደሮች ቊጥር እጅግ ከፍ ያለ ፡ ነበር። እንዲሁም የኢትዮጵያ ጦረኞች ሶስት ዕርድ (ምሽግ) አስለቅቀው ጠላትን እስከ ዓዲ ዙማ ድረስ ወደ ኋላ አሸሹት። ስለዚህ የመጨረሻውን አንድ ምሽግ ብቻ (ያውም በአቅራቢያው ወሀ የማይገኝበት) ይዞ በመከላከል ቆየ። ምክንያቱም እላይ እንደተናገርነው ብዙ ሰው አልቆ ነበርና ኢትዮጵያን ከ፫ ቀን ጦርነት በኋላ ከወገናቸው የሞቱትን ማስቀበር

ግድ ሆኖባቸው ወደ ሰፈር ስለተመለሱ ነው እንጂ ጦርነቱን ፡ ቀጥለው ቢሆን ኖሮ በተንቤን ስንዝር መሬት ሊቀረው ባልተቻለ ነበር።

ጥር ፲፰ ቀን በዚሁ ጦር ሜዳ የጀብዱ ሥራ የሠሩ ጀግኖች በልዑል ራስ ካሣ ፊት እየቀረቡ ይፈክሩ ስለ ሥራቸውም አፈጻጸም ማስረጃ ጉዳይ ይጥሉ ፡ ወይም በምርኮ የያዙዋቸውን የኢጣልያ ወታደሮች ያስረክቡ ጀመሩ። ስለዚህ ልዑል ራስ ካሣ በወታደሮቻቸው ቅልጥፍና ደስ ተሰኝተው ሰነበቱ።

ምዕራፍ ፲፫።

## የአምባራዳም ጦርነት።

ልዑል ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም ወደ ተንቤን አንፃር ሲያቀኑ ራስ ሙሉጌታ ሠራዊታቸውን ይዘው በአምባ አራዳም ሰፍረው ነበር። እዚያም እንዳሉ ለሰሜን ፡ የጦር ግንባር ልዑል ራስ ካሣ ዋና አበጋዝ መሆናቸውን ራሳቸውም በቀጥታ ልዑል ራስ ካሣ በሚያመለክቱት ፕላን እንዲመሩ መደረጉን ከንጉሠ ነገሥቱ በቴሌግራም ተላለፈላቸው። በዚያን ጊዜ መቀሌ ሆኖ የአምባ አራዳምን ተራራ የሚመለከተውን የኢጣልያን ጦር ምቹ ሥፍራ ይዘው ይጠባበቁ የነበሩት ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ (የከንባታ ጦር አዝማች) ደጃዝማች በየነ አባ ስብስብ (የኮንታና የቆጫ ጦር አዝማች) ደጃዝማች መንገሻ ይልማ (የፈረስ ዘበኛ አለቃ) ሌሎችም ጥቂቶች መኳንንቶች በተንቤን በኩል ገፍቶ የመጣውን ጠላት ይከላከሉ ዘንድ እንዲዘዋወሩ ስለ ተደረገ ጠላት አምባውን ለመያዝ የሚችልበትን ፕላን ያዘጋጅ ጀመረ። ወዲያውም ከመቀሌ ምሽጉ ወጥቶ ወደ ፊት መግፋቱን አንድ በአገር ፍቅር የተነካ መነኰሴ አይቶ ራስ ሙሉጌታን አስጠነቀቃቸው። እሳቸውም የጦር ጉባኤ አድርገው እንግጠመው ወይም እናቆየው በሚለው አሳብ ላይ ሲከራከሩበት ሰነበቱ። በመጨረሻውም ፑስቴሪያ የሚባለው የአልፒን ዲቪዚዮን የክፍል ጦር ወደ ጨለቆት ስለተጣጋና በዚያም ምሽግ መሥራት ስለ ጀመረ ራስ

ሙሉጌታ ጦርነቱን ለመግጠም ቁርጥ አሳብ አደረጉ። ለጊዜውም ከርሳቸው ጋራ የነበረው የጦር ሠራዊት ቤተ ደንብ ቀጥሎ እንደ ተመለከተው ነበረ።

የገሙ ጦር በፊታውራሪ ዘለቀ ሀብቴ (ሻለቃና እንደራሴ) በደጃች አውራሪስና በደጃች ወልደ ማርያም መሪነት።

- የወሎ ጦር ፡ በደጃች ወዳጄ መሪነት።
- ውሀ ስንቄና ግንደበል በአጋፋሪ ያረጋል መሪነት
- የፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ የቤት አሽከሮች በፊታውራሪ ኪዳኔ መሪነት።
- ስናድር ያዥ ፡ በፊታውራሪ ተፈረደኝና በቀኛዝማች ደስታ ወልደ ኪሮስ መሪነት።
- የክብር ዘበኛ ፡ በልጅ ዳኜ ወዳጄ መሪነት።
- የሥራ ቤት በአዛዥ ደምሴ መሪነት።
- የጓዳ ቤት የገ ሚ በአቶ ኃይሌ ኪዳነ መሪነት።
- መድፈኛ ፡ በልጅ ታደሰ ሙሉጌታ መሪነት።
- ማለፊያ ጠመንጃ ያዥ ፡ በቀኛዝማች አበበ ረዴ መሪነት ፡
- የሥራ ሚኒስቴር ፡ ባላምባራስ በቀለ ጎሹ መሪነት።

የራስ ሙሉጌታ የቤት አሽከሮች በፊታውራሪ ፈልቀ መሪነት።

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ቤተ ደንቦች ውስጥ የሚታዘዙ እንደራስ ገብረ ሕይወትና እንደ

ደጃች አመዴ እንደነ ደጃዝማች አምባቸውና እንደነ ፊታውራሪ በየነ ሠራዊቱ ያሉ ታላላቅ ሰዎች ይገኙባቸዋል።

ማናቸውም የሚያስፈልገው ድርጅቶች ከተፈጸመ ፡ በኋላ ራስ ሙሉጌታ ለጦር ሠራዊቱ ትእዛዝ ሰጥተው የካቲት ፬ ቀን ረቡዕ እስከ ጨለቆት ሥላሴ ድረስ ሄደው በጠላት ምሽግ የካቲት ላይ አደጋ መጣል ጀመሩ።

ከአምባ አራዳም አስከጨለንቆት ድረስ ያለው ርቀት ምናልባት ከ፺ ኪሎ ሜትር አይበልጥም። ነገር ግን መሬቱ ወጣ መሬቱ ወጣ ገባ በመሆኑ የኛ ወታደሮች ከአምባ አራዳም ሠፈራቸው ገሥግሠው አደጋውን መጣል እስከ ጀመሩበት ጊዜ ድረስ ለጠላት አልተገለጹለትም ነበረ ይሁን እንጂ ከሌላው በቀር በመድፍና በመትረየስ የታጠረውን ምሽግ ለመጣስ ባደረጉት ትግል ብዙ ሰው አለቀባቸው። ይልቁንም ደጀን ሆኖ በሚጠባበቀው ላይ አኤሮፕላኖች የቦምብ ነጐድጓድ ሰለ አወረዱበት ከአሰበው ሥፍራ ደርሶ የልቡን ለመሥራት አንዳንድ ጊዜ ያዳግተው ነበረ። በዚህ ቀን ሁለቱም ወገኖች ከጧት እስከማታ ሲሳጐዱ ውለው ዕርበተ ፀሐይ ገላገላቸውና የኛ ወታደሮች ከቀድሞ ሠፈራቸው ተመልሰው አደሩ።

የሆነ ሁኖ የወሎ ጦር አብዛኛው በጨለቆት ላይ ለስሙ ሐውልት የሚሆን የጀብዱ ሥራ በመሥራት ሞትን ሲመርጥ ጥቂቶቹ ዘዴን መሣሪያ ያድርጉ ዘንድ ፈቀዱ ፡ እንዲሁም ምቹ ሥፍራ ለማዘጋጀት ይቻል እንደሆነ በማለት ሞከሩ።

በአምባ አራዳም ሰፈር የሚገኙ የኛ ወታደሮች የካቲት ፳ ቀን ቆስለው ከመንገድ የወደቁትን ጓደኞቻቸውን በመሰብሰብና የሞቱትን በማስቀበር ፡ ዋሉ። ይሁን እንጂ የአይሮፕላን አደጋ ፋታ አይሰጣቸውም ነበርና ቁስለኛ ሲሰበስብ የዋለው ራሱ ቆስሎ ሲሰብስብ ፡ የሞተውን ሲቀብር የዋለው ራስ ሞቶ ሲቀበር ማየቱ ቀሪው እገሌ ነው በማለት በኩል ለያንዳንዱ ሰው የመኖሩን ተስፋ የሚያስቆርጥ ነበረ። እንዲሁም የካቲት ፺ ቀን ወደ ፊት ስለሚሆነው ድጋሚ ጦርነት ሲዘጋጁ ዋሉ።

በማግሥቱ የካቲት ፺ ቀን ቅዳሜ አንባውን ለመከበብ በቀኝና በግራ ፡ ፊት ለፊትም የተሰለፈ የጠላት ጦር መምጣቱ ሰለ ተሰማ ራስ ሙሉጌታ ከሞትና ከመቁሰል ባክነውም የተረፉትን ወታደሮቻቸውን ይዘው መከላከል ጀመሩ። ነገር ግን ያላቸው ኃይል አምባውን ለመከላከል በቂ አለመሆኑን ስለተረዱት የዚያኑ ዕለት በ፲፪ ሰዓት ወደ ኋላ መመለስ ግድ ሆነባቸው።

እንዲሁም በዚሁ ቀን አምባ አራዳምን ለቀው ወደ አላጌ ተዛወሩ። ከዚያም በነበሩትበት ጊዜ የማይጨው ገዥ የነበሩት ደጃች አበራ ተድላ ኃይላቸውን በማስተባበር የጠላትን እርምጃ እንዲከላከሉ ልከውባቸው ነበር። ነገር ግን ምንም እንኳ ደጃዝማች አበራ ጠላትን ለመከላከል ምቹ የሆነ ሥፍራ ቢይዙ በመከላከሉ ያለው የራያ ሕዝብ አምፆ ነበረና ሠራዊቱ የሚገናኝበትን መንገድ ስለቈረጠው በመረዳዳት ለመከላከል የታሰበውን ሃሳብ የሚያስፈጽም መስሎ አልታያቸውም ስለዚህ ራስ ሙሉጌታ በዚያን ጊዜ ግርማዊነታቸው የሚገኙበትን በኮረም ነበረና ወደ እርሳቸው ዘንድ መሄድ የተሻለ ይሆናል ሲሉ ገመቱ።

ራስ ሙሉጌታ አላጌ ላይ በነበሩበት ሰዓት አቶ ኃይለ ጊዮርጊስ ወልደ አማኑኤል የሚባለው አጎሬ ግምሩክ ሠራተኛ ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጋራ በምሥጢር ይጻጻፍ ኖሮ ደብዳቤው በድንገት ከደጃዝማች ወዳጄ እጅ ስለወደቀ እንዲመለከቱት ሲሉ አቀረቡላቸው። ወዲያው ይህ ሰው ተይዞ ቢጠየቅ በመጀመሪያው ጊዜ ልዩ ምክንያት ሰጥቶ ነበረ። በኋላ ግን የክህደት ሥራውን ስላመነ በባላምባራስ በቀለ ጎሹ ወደ ኮረም ተልኮ ከግርማዊነታቸው ችሎት በተደረገው የጦር ፍርድ መሠረት ተሰቀለ።

ራስ ሙሉጌታ የካቲት ፲፫ ቀን አላጌን ትተው ወደ ኮረም አቃኑ። እንዲሁም ጉዟቸውን በመቀጠል የካቲት ፲፭ ቀን እማይጨው ደርሰው ሳሉ የጠላት አኤሮፕላኖች በመንደሩ ላይ ቍጥር የሌለው ቦምብ አዘነሙበት። እንዲሁም በአደጋው ምክንያት ከፍ ያለ ቃጠሎ ስለ ተነሣ ሕዝቡ መዳኛ የሚሆን ስፍራ በመፈለግ ወዲያና ወዲህ ሲል የራያ ባላገር ጦር ሰርቶ ጓዙን ይዘርፈው ጀመር። ስለዚህ ከባላገር ጋራ የሚሆነው ጦርነት ሞቅ እያለ በመሄዱና የቦምቡም አደጋ በመበርከቱ ለጊዜው ጉዞው አቋረጠ። ነገር ግን በዚያው ሰሞን ከጨለቆት ወዲህ በሚገኘው በዐዲ በቀይቲ በኩል ቢት ወደድ መኰንን ደምሰው ጦርነት አድርገው በጀግንነት ከሞቱ በኋላ የርሳቸው ሠራዊት ወደ ኋላ ተመልሶ ነበረና ከራስ ሙሉጌታ ወታደሮች ጋር በመተባበር የባላገሩን ጦር ስለተከላከሉ ምንም እንኳ ሰላማዊ ጉዞ ባይኖር

ለጥቂት ጊዜ መንገድ ማግኘት ተቻለ። እንዲሁም ወደ ኮረም ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው የካቲት ፲፰ ቀን ረቡዕ እንደገና ብርቱ የሆነ የባላገር ጦርነት በመንገድ ስለ ተነሣ ራስ ሙሉጌታ በጥይት ቆስለው ወደቁ። ከርሳቸውም ጋር ልጃቸው ልጅ ታደሰ ሙሉጌታና ብዙ መኳንንቶቻቸው ሞቱ።

አንዳንድ ሰዎች ራስ ሙሉጌታ ከወደቁ በኋላ ራያዎች እንደ ልማዳቸው ባሕርይ አሳንሰዋቸዋል እያሉ አውርተው ነበር። ነገር ግን አንስከሬናቸውን ገንዘው የቀበሩዋቸው ሰዎች ይህ የአረመኔነት አደራረግ እንደተፈጸመባቸው አላረጋገጡም።

ራስ ሙሉጌታ ከወደቁ በኋላ ከሞት የተረፉት መኳንንት እየተከላከሉ ከንጉሠ ነገሥቱ ሠፈር ከኮረም ለመድረስ ቻሉ። በዚያን ጊዜ የጠላት አይሮፕላኖችና የራያ ባላገሮች በሚሸሸው ሕዝብ ላይ ያወረዱት ሥቃይ ሲገመት በዋናው የጨለንቆትና የአምባ ራዳም ጦርነት ላይ የደረሰው ሞት ክብር ያለው ከመሆን በላይ ግርማው አስፈራሪ ነው ለማለት አንደበት አይደፍርም።

ይኸውም ሊታወቅ ላዲዝዎ ፖርታ የሚባለው ኢጣሊያዊ ጋዜጠኛ በአምባ አራዳም ስለተደረገው ጦርነት የጣሊያኖች ጀግንነት በማድነቅ ሲጽፍ ሊያልፈው የማይቻል በመሆኑ እግረ መንገዱን ስላንዱ ኢትዮጵያዊ እንዲህ ብሎ ጽፏል።

«በንደዚህ ያለ አኳኋን እየቀጠለ የሚሄድ ብርቱ ጦርነት ተደረገ። በዚሁም ጦርነት የክምፓኝየው አዛዥ ስለ ሞተ አንዱ አፈሴር ተተክቶ መከላከሉን ቀጠለ። ይኸውም አፌሴር በአንድ መትረየስ አጠገብ ሆኖ ሳለ አንድ አበሻ ጐራዴውን እያምቦገቦገ እፊቱ ድረስ መጥቶ ጥይት አቀባዩን ሲቀላው አየ። ያም በብርቱ ቆስሎ ወደቀ። ከዚያም በኋላ ኢትዮጵያዊው በሌላው ወታደር ላይ ዘሎ ስለተጣበቅበት ከመቁሰሉ አስቀድሞ ትግል (ግብግብ) ተያያዙ። ሁለት ሰዎች በቡጢ (በጡጫ) እየተጣለዙ አንዱ ባንዱ ላይ ይንከባለሉ ጀመር። አበሻው ከኢጣልያዊው ለመላቀቅ ችሎ ሳለ ፡

ቴኔንቴው የመስኬቶውን (ትንሽ ጠመንጃ) አፈሙዙን ይዞ ተደቀነበት ፡ እንግዲህ ኢትዮጵያዊው በመሬት ላይ ይንከባለል ጀመር። አሁንስ ለሁል ጊዜ ነው»

ምንም እንኳ በማቆላመጥ ባይሆን በጠላት አንደበት ለመደነቅ ያበቃው ይህ ቢሞትም ያልሞተው ያገሬ ጀግና ማን ይሆን?

## ምዕራፍ ፲፬።

## የግርማዊነታቸው ከደሴ መነሣት።

ግርማዊነታቸው እደሴ ላይ ሆነው በሶስት ዋና ዋና ግምባር የተሰለፈው የጦር ሠራዊት ማናቸውም የሚያስፈልገው ነገር እንዳይጐድልበት በመሥራት ላይ ቆይተው ነበር። በኋላ ግን ከራስ ሙሉጌታ ጋራ የተሰለፈው ሠራዊት የሸዋው በወሎ የወሎው በሸዋ እየተመከኞ ወደ ኋላ መመለሱንና በሚመለስበትም ጊዜ የደረሰበትን አደጋ ስለሰሙ ወዲያው የካቲት ፲፫ ቀን ከደሴ ተነሥተው ጉዟቸውን ወደ ፊት ቀጠሉ። ነገር ግን ሰሞኑን ዝናም ይዘንም ነበርና መንገዱ ለካሚዮን ጉዞ አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሣ ብዙውን ጊዜ በየቦታው ሰፈር እያደረጉ ለጒዞ የሚመችበትን ብራ ሰዓት መጠበቅ ግድ ሆኖባቸው ነበር። ከዚህ በኋላ የካቲት ፳፪ ቀን ወደ ማታ እኮረም ገቡ።

በማግሥቱ የካቲት ፳፫ ቀን ኮሚቴ ደ ዲዝ ዊት የተባለው በጋዝ ምክንያት በኢጣሊያ ላይ ሊደረግባት የሚገባው ጭቆና የሚፈጸምበትን መንገድ ለመርመር ስብሰባ አድርጎ ነበረና በዚያ ጊዜ የላቫል ምትክመሲየ ፡ ፍላድን በሁለት ተዋጊዎች መንግሥታት መካከል ጦርነቱን ለማቆም የሚቻል እንዲሆን ይከታተሉት ዘንድ ለጉባኤው አሳሰበ። እንዲሁም የታላቂቱ ብሪታንያና የፓሎኝ ፡ የእስፓኝም መንግሥታት እንደራሴዎች አሳቡን ስለደገፉት ጉዳዩ ለኮሚቴ ደትሬዝ እንዲተላለፍ ተደረገ።

በሚከተለው በየካቲት ፳፬ ቀን እላይ የተጠቀሰው ኮሚቴ ልዩ ስብሰባ አድርጎ ቀጥሎ የተመለከተውን አሳብ በጽሕፈት ካዘጋጀ በኋላ ለሁለት ተዋጊዎች መንግሥታት ላከላቸው።

«የ፲፫ቱ ኮሚቴ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን የምክር ቤቱ ወስኖ በሰጠው ትእዛዝዝ መሠረት ጦርነቱን ወዲያው ለማስቀረት በዓለም መንግሥታት ማኅበር ፕላንና በኪዳነ ቃሉ መንፈስ የዕርቅ ድርድር ይከፈት ዘንድ ሁለቱ ተዋጊዎች መንግሥታት የሚያስቸኩል ጥሪ ያቀርባል።

«የሁለቱን መንግሥታት መልስ ለማወቅ ኮሚቴ ደትሬዝ መጋቢት ፲ ቀን ይሰበሰባል»

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በኮረም ላይ ሳሉ ይህ ከዚህ በላይ የተመለከተው የኮሚቴው አሳብ ስለደረሳቸው የማኅብሩ ቃለ ኪዳን የሚያዘውን ሕግ ከመጠበቅ ጋራ የሚያቀርብላቸውን የዕርቅ ድርድር ለመቀበል ፈቃዳቸው መሆኑን የካቲት ፳፮ ቀን በቴሌግራም አስታወቁ። ይሁን እንጂ የካቲት ፳፱ ቀን ስለዚሁ የኢጣልያ መንግሥት የሰጠው መልስ በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ስለተነሣው ጦርነት ነገሩን ለመወሰን የሚቀርብለትን ጠቅላላ አስተያየት ለመቀበል የሚፈቅድ መሆኑን ሲገልጽ ፡ የማኅበሩን ደንብ ከመከተል ጋር ይፈጽም ዘንድ አልዘረዘረም።

በማናቸውም አስተያየት ከሁለቱ ተዋጊዎች መንግሥታት የቀረበውን መልስ ለመርመር የተባለው ኮሚቴ መጋቢት ፩ ቀን (እንደ ኤውሮፓውያን አቆጣጠር መጋቢት ፲ ቀን) በዠኔብ ላይ መሰብሰብ ነበረበት። ነገር ግን ጀርመን፥ የሎካርኖን ቅል በማፍረሷ ምክንያት ስለ ደረሰው ችግር የጄኔብ ስብሰባ ቀርቶ ለዚሁ በሎንዶን ላይ ከፍ ያለ እንግዳ ጉባኤ ተደረገ።

በ፳ኛው ቀን በመሲየ ደማድሪጋ ፕሬዝዳትነት በተደረገው ጉባኤ አባሎች በሰፊው ከተከራከሩበት በኋላ ጉዳዩን በተለየ ፕሬዝዳንቱ መሲየ ደማድሪጋና ጠቅላዩ ጸሐፊ መሲየ አሸኖል እንዲከታተሉት ወስነው ተለያዩ።

ይሁን እንጂ ፕሬዝዳንቱና ጠቅላይ ጸሐፊው ነገሩን ወዲያው ለመርመር ለሁትን መንግሥታት ጥያቄ ቢያቀርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃዱ መሆኑን ሲገልጽ የኢጣልያ መንግሥት ከፋሲካ አስቀድሞ አይቻልም ብሎ አስታወቀ። ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን በመስለው አኳኋን ነገሩ እየተጕተተ እንዲዘገይ በመደረጉ አቤቱታቸውን በቴሌግራም ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አስተላለፉ።

እላይ እንደጠቀስነው የ፲፫ቱ ኮሚቴ ያቀረበው የዕርቅ ድርድር የዓለም መንግሥታት ማኅበር በደነገገው ቃለ ኪዳን መሠረት እንዲሆን የኢትዮጵያ መንግሥት መላልሶ ሲያስጠነቅቅ የኢጣልያ መንግሥት ልዩ አስተያየት ነበረው። ይኸውም ጦርነቱን ለማቆም ሲታሰብ አርሚስቲስ እንዲጠየቅና በዚሁ ረገድ የሚቀርበውን ዕርቅ እንዲደራደር ነው። ነገር ግን በአርሚስቲስ ረገድ ዕርቅ እንዲያቀርብ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚፈቅድ ቢሆን ኖሮ ከጦር ሹማምንቱ ጋር በመነጋገር ፈንታ የዓለምን መንግሥታት ማኅበር አማካይ ማድረግ በላስፈለገውም ነበር። ስለዚህ በዚያን ጊዜ የኢጣልያ መንግሥት ይህን የመሰለ አስተያየት መግለጹ በዓለም መንግሥታት ማኅበር ደምብ ፊት የሚያደርገውን ፌዝ ለማሳየትና በማንም ዘንድ ሥጋት እንዳልነበረው ለማስረዳት ነው እንጂ በውነቱ ማኅበሩ ፡ አጥቂና ተጠቂ የሚገኙበትን ሁኔታ አክብረው ይቀበሉት ዘንድ ለማፈራረም እንዳልተመሠረተ ደሕና አድርጎ ያውቀው ነበር።

የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳ ለዕርቅ የደከመባቸው ጊዜያቶች የሰጡት ፍሬ ባይኖር ፡ ጉዳዩን በሰላም ለመፈጸም ማሰቡ አላጸጸተውም። ነገር ግን የተመኘው ሰላም የሚመጣበት ጊዜ ገና መሆኑን ለመረዳት ያህል በመጨረሻው ጊዜ የቀረበው ይህ የኢጣልያ መንግሥት አስተያየት በቂ ሆነ።

## ምዕራፍ ፲፫።

# የሺሬ ጦርነት።

የጐጃም አውራጃ ገዥ የነበሩት ራስ እምሩ ኃይለ ሥላሴ ወደ ሰሜን ግንባር እንዲዘምቱ ከአዲስ አበባ በቴሌግራም ትእዛዝ የደረሳቸው ወዲያው የድንበሩ መጣስ እንደ ተጀመረ ነው። እርሳቸውም ተዘጋጅተው ይጠባበቁ ነበርና ትእዛዙ ከደረሰ በኋላ ጊዜ ሳይጠፋባቸው በጥቅምት ፯ ቀን ከደብረ ማርቆስ፥ ተነሥተው ጉዞ ሆነ። እንዲሁም በጥቂት ቀን ጉዞ ጣቁሳ፣ በሚባለው ፡ በበጌምድር ግዛት አልፈው ኅዳር ፯ ቀን በጐንደር ላይ በዓለ ቍስቋምን ከአከበሩ፥ በኋላ የጠላት ጦር ያመራበትን ፡ አንፃር ደህና አድርገው ለመርመር ወዲያና ወዲህ በማለት ጥቂት ዘገዩ። በመጨረሻው በደባርቅ ሠፍረው ሳሉ አቶ ባሕሩ ካባ በአኤሮፕላን ፖስታ ሊያደርስላቸው ስለቻለ የጉዟቸው አንፃር ወዴት ሊሆን እንደሚገባ ይረዱት ዘንድ የቀና ነገር ሆነላቸው።

በዚያን ጊዜ በራስ እምሩ ውስጥ የሚመሩት ከብዙዎቹ ታላላቆች የጎጃም መኳንንቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ነበሩ

ደጃዝማች ያየህ ይራድ ደርሶ።

ደጃዝማች ስብሐቱ ይግዛው

ደጃዝማች መንገሻ ጀንበሬ

ደጃዝማች ሺበሺ ለማ

ደጃዝማች ማዘንጊያ

ደጃዝማች መስፍን ገመች

ፊታውራሪ ኃይሉ እምሩ

ፊታውራሪ ከንፌ

ቀኛዝማች ይነሱ

ሌሎችም ብዙዎች መኳንንቶች ነበሩ።

ምንም እንኳ ደጃች ገሠሠ ኅዳር ፳፫ ቀን ከድቶ ከብዙ መኳንንት ጋራ ማለት ከፊታውራሪ ፡ ተአምራትና ከፊታውራሪ ፡ ደስታ ወንዴ ከቀኛዝማች በላይ መሸሻና ከቀኛዝማች ዘለቀ አሰጌ ከቀኛዝማች ካሣ ሥዩምና ከቀኛዝማች ዓለማየሁ ዘገዬ ከቀኛዝማች አየለና ከቀኛዝማች መኰንን ጂሜ ከሌሎችም ስማቸው ካልታወቀ መኳንንቶች ጋራ ወደ ጎጃም ቢመለስ ፡ ራስ እምሩ በቁጥጥርና በግምት ብዙ ብልጫ ያላአቸውን ታማኞች የጎጃም መኳንንት ይዘው የቀን ጉዟቸውን በአኤሮፕላን ምክንያት የሚያሰጋ ሲሆን ሌሊቱን በችቦ መብራት ይገሠግሡ ነበር።

በዚያን ጊዜ ፡ በሺሬ ፡ በኩል ይከላከሉ የነበሩት ደጃዝማች ገብረ መድኅን ረዳት ጦር እስኪደርስላቸው ወደ ዳር ሆኖ መጠባበቅ ግድ ሰለ ሆነባቸው፣ የኢጣልያ ጦር እሰከ ተከዜ ወሰን ድረስ ገፍቶ ነበርና የደጃዝማች አያሌው የጦር አዝማች ፊታውራሪ ሽፈራው አባ ከንትር ቀድመው ተጓዙ። ስለዚህ የተከዜን ባሕር ለመሻገር የሚቻልበትን አኳኋን ይመረምሩ ዘንድ በየጊዜው ይመላለሱ የነበሩት በማጆር ክሪንቲ የሚታዘዙት ኢጣልያኖች ሰግጠዋ ብለው በደንብ ጉና ምሽጋቸው እግራቸውን ይሰበስቡ ዘንድ ግዴታ ሆነባቸው። እንዲሁም በፊታውራሪ ሽፈራው የሚመራው ጦር ተከዜአን አልፎ ወደ ደንበጉና በአቃና ጊዜ ግራን ሳሶ» የሚባለው የደቪዚዮኑ አዛዥ ታኅሣሥ ፪ ቀን እንዲህ ሲል ትእዛዝ ሰጠ። «በጥንካሬ ለመዋጋት ኃይላችሁን አታባክኑ ነገር ግን ላለመጋጠምና ወደ ኋላ ለማምለጥ የሚቻልበትን አኳኋን ጠብቁ።

ከዚህ በኋላ ማጆር ክሪንቲና ምክትሉ ካፒታኖ ሜሌሎ ማለዳ ተነሥተው ከእንዳ ሥላሴ የሚያገናኘው ዋናው መንገድ እንዳይያዝባቸው ለማድረግ አሰቡ። እንዲሁም የደንብ ጉናን በር በጠነከረ ኃይል (በታንክና

በመትረየስ) አስይዘው ሠራዊቱን ወደ እንዳ ሥላሴ መሸኘት ጀመሩ። ነገር ግን ፊታውራሪ ሽፈራው የእንዳ ሥላሴን መገናኛ በመቍረጥ ኢጣልያኖች የፈሩት ነገር እንዳይደርስባቸው አደረጉ።

በየጊዜው በሁለት ወገን ዕርዳታ የሚጨመርለት የኢጣልያ ጦር በአንድ ወገን ሁለቱንም ለመመለስ ችሎታ ባለው በአባ ክንትር ፊት ለመቆም ሳይቻለው ቀርቶ ተሸበረ። እንዲሁም በሰራዬ፣ በከረን፣ በሀማሴን የተሰየመው የባንዳ ክፍል ያስገኘው ጥቅም የለም። እንዲህ በመቈራቈስ የነበረው ግጭት ታኅሣሥ ፭ ቀን እሑድ ወደ ዋና ጦርነት ተለወጠ።

በዚሁ ቀን ፊታውራሪ ሽፈራው አባ ክንትር በደንብ ጉናና በእንዳ ሥላሴ መካከል ያለውን መንገድ በመቍረጥ ካደረጉት ጦርነት የተነሣ ብዙ የኢጣልያ አፊሰሮች አለቁ። እንዲሁም ደጃዝማች ገብረ መድኅንም በደንበ ጉና ተራራ ሰሜን በኩል በምትገኘው ጠባብ መንገድ ለማለፍ የሞከረውን ጠላት አግደው አስጨነቁት። ከሁለቱም ወገን የተጠመዱት መትረየሶች ይዘፍነ ጥይቶቹ ይደንሱ ጀመር። በዚያን ጊዜ የታንኮች ክፍል ሹም የነበረው ካፒታኖ ክሪፓ በታንኩ ውስጥ መገኘቱ ሳይበቃው ሌላ ከለላ ይፈልግ ዘንድ ፍርሃት አነሣስቶት ስለወጣ ከኛ ወታደሮች የሚተኰሰው መትረየስ ዓይነ ስቡን ብሎ መንጋጋውን አፈለሰለት። ስለዚህ ቴንቴቶዚ የተባለው ከወደቀበት አንሥቶ እታንኩ ውስጥ እንደመለሰው ወዲያው ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ስለሞቴንቴ ፍራንኮ ማርቴሊ የሚባለው የአዛዥነቱን ሥልጣን ያዘ።

በዚህ አኳኋን የጦርነቱ ሁኔታ እየባሰ ሲሄድ የግሩፓው ማጆር ክሪንቲ ጭኑን ቈስሎ ወደቀ ስለዚህ ኢጣልያኖች ፡ በብርቱ ጭንቅ ላይ ሳሉ ፊታውራሪ ሽፈራው የጀግነታቸው ሲቃ ገና በአፍላው እያለ የዚያኑ ዕለት ከጠላት ታንክ ፊት ስለ ወደቁ ወደ ፱ ሰዓት ግድም ያቺን አስጨናቂዋን የቁንበ ጉናን ጠባብ በር ጠላት ባለቤት ሊሆንባት ቻለ። ይሁን እንጂ የዚህች በር ባለቤትነት ለኢጣልያኖች እንዲያመልጡ ከማገልገልዋ በቀር

እንዲኖሩበት አላደረጋቸውም። ስለዚህ ከወደ ኋላቸው እየተከታተለ የሚተኰስባቸውን ሳይመለከቱ ገስግሰው ከእንዳ ሥላሴ ምሽግ ገቡ።

በዚያን ጊዜ ደጃዝማች አያሌው በጦሩ ግንባር አልነበሩምና የፊታውራሪ ሽፈራው ዜና ሞት ስለ ደረሰባቸው ከዚህ ዓለም በመለየታቸው ፡ ሲያዝኑ በጀግነት ሥራቸው ከመደነቅ ጋራ ተደሰቱ።

ከዚህ በኋላ ራስ እምሩና ደጃዝማች አያሌው ተገናኝተው ወደ ፊት መግፋታቸውን በእንዳ ሥላሴ ምሽግ ያለው ጠላት ስለሰማ ምሽጉን ለቆ ወደ አኵስም ተጓዘ። በዚያን ጊዜ ከእንዳ ሥላሴ እስከ አኵስም ድረስ አልፎ አልፎ የነበረው የጠላት ምሽግ ስለተለቀቀ አገሩ ነፃ ሆኖ ነበር። ስለዚህ ለጊዜው ጠላት በግንባራቸው ባለመገኘቱ ወደ ፊት ስለሚደርሰው ጦርነት እየተዘጋጁ ብዙውን ቀን ካሳለፉት በኋላ ወደ የካቲት ወር መጀመሪያ አበራ የሚባል አንድ አገር ወዳድ ካህን በራማ ላይ የሚገኘውን የጠላትን ጦር ሁኔታ መርምሮ ለራስ እምሩ ስለ ነገራቸው በሻለቃ ዮሐንስ አብዶ መሪነት ጥቂቶች ወታደሮ አደጋ ይጥሉ ዘንድ ተላኩ። እነዚህም ወታደሮች ከምሽጉ አቅራቢያ እንደደረሱ የጠላት ቃፊሮች አይተው ስለተኮሱባቸው የተኵሱን መልስ ሲሰጡ አረሩ እቦምብ መጋዘን ላይ ከመውደቁ የተነሣ ቦምቡ ይፈነዳ ጀመረ። እንዲሁም የቦምቡ ፍንጣሪ ሁለቱን ተዋጊ ወገኖች ሊያገናኛቸው የማይቻል ከመሆኑ በላይ ብዙ ፡ ጉዳት ስላደረገ ኢጣልያኖች ራማን ለቀው ወደ ኋላ ሲሸሹ የኛም ወታደሮች ወደ ሰፈራቸው ይመለሱ ዘንድ ግድ ሆነባቸው።

በዚያን ጊዜ አኵስም የነበረው የጠላት ጦር አንዳንድ ጊዜ ነፈረስ እየወረረ የሺሬን አውራጃ ሰብልና የባላገሩን ቤት አቃጥሎ ከመመለሱ በቀር የራስ እምሩ ወታደር እስከሚገኝበት ደርሶ ጦርነት ለመግጠም አልደፈረም ነበር። ከጥቂት ቀን በኋላ ግን የራስ እምሩ የጦር አበጋዝ ፊታውራሪ ከንፌ በሰለክላካ ክፍል በእዳጋ ሰኑይ ሰፍረው ሳሉ የኢጣልያ ጦር መጥቶ የካቲ ፳፩ ቀን ዓርብ አደጋ ስለጣለባቸው በብርቱ ተከላከሉ። እንዲሁም ሰፈራቸውን ሳይለቁ ፫ ቀን ከተዋጉ በኋላ እሑድ ለሰኞ አጥቢያ ራስ እምሩና ደጃዝማች

አያሌው ደረሱላቸው። እነርሱም የጠላት ጦር በስተ ጐን ወይም በስተ ጀርባ እንዳይከባቸው ይጠባበቁ ዘንድ ደጃዝማች መስፍን ገመችን ደጀን አድርገው ከቀሩት መኳንንት ጋር የካቲት ፳፬ ቀን ሰኞ በማለዳ ገጠሙ። የዚያን ዕለት ቦምብ እየጣሉ በአየሩ የሚያንዣብቡት የጠላት አኤሮፕላኖች ከብዛታቸው የተነሣ የፀሐይ ብርሃን ሊጋርዱ ጥቂት ቀርቷቸው ነበር። ደግሞም የታንኩና የመድፉ ድምፅ ከቦምቡ ጋር ሲተባበር የነጐድጓድ በመሆኑ ምድርን የሚያርገበግባት መሰለ። የኛ ወታደሮች «ጋሺና እና ግራን ሳሶ» ከተባሉት ከጠላት የጦር ክፍሎች ጋር በጨበጣ ተያያዙ። በመጀመሪያው ጊዜ የጠላት ወታደሮች በጩቤ ወይም በሳንጃ የኛዎቹ በጐራዴ ሲቃሉ ነበረ። በኋላ ግን ኢጣልያኖች በዚህ አያያዝ ሊገፉትበት ስላልቻሉ የጅ ቦምብ ማፈንዳት ጀመሩ። ስለዚህም ብዙ ሰው አለቀ።

ሁለቱ መሪዎች ከወደኋላቸው የሚበቃ ደጀን ካለመኖሩ በላይ ጠላት በየጊዜው የወታደርና የመሣሪያ ጭማሪ እንደሚገኝ ስለተመለከቱ በተከዚ በረሃ ውስጥ ምቹ ስፍራ ተፈልጎ ይከላከሉ ዘንድ ቈርጠው ወደ ኋላቸው ተመለሱ።

## ምዕራፍ ፲፯።

## ፪ኛው የተንቤን ጦርነት።

ከመጀመሪያው የተንቤን ጦርነት በኋላ ኢጣልያኖች ሰፈር ያደረጉት ከአርቤ ቀረብ ብሎ ከሚገኘው ከአዲ ዙባሃ ሰሜን ነበርና ልዑል ራስ ካሣ ከሐውሴን ወደ ዓዲ ሱባሃ የሚወስደውን መንገድ ለመቍረጥና የአባሮን በር ለመያ የሚቻልበትን አኳኋን በየጊዜው ከባላገሮቹ ጋራ ከመነጋገራቸው በላይ ከመኳንንቱም ጋራ ይመካከሩበት ነበር። በዚያን ጊዜ ከርሳቸው ጋራ የነበረው ጦር በመጀመሪያው ጦርነት ምክንያት ጒዳት አግኝቶት ስለ ነበረ ከራስ ሙሉጌታ ጋራ በአምባ አራዳም ክፍል የነበሩት እነ ደጃዝማች በየነ አባ

ሰብስብና እነ ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ እነ ደጃዝማች መንገሻ ይልማና እነ ፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን በጠቅላላው ፳ ሺ ያሚያህል ወታደር ይዘው የካቲ ፰ ቀን ዓቢይ ዓዲ መግባት ጀመሩ። እነዚህ መኳንንቶች በግባ ወንዝ በኩል ጉዟቸውን ሲቀጥሉ የጠላት አኤሮፕላኖች ዕረፍት ነሥተዋቸው ነበር። እንዚሁም ዓቢይ ዓዲ ከገቡ በኋላ ፡ ጠላት የነሱን መምጣት ሰምቶ የአኤሮፕላን አደጋ እየባሰ እንዲሄድ አደረገ። ስለዚህም አኤሮፕላኖች የቀኑን ሰዓት ተካፍለው አንዱ ክፍል ሲሄድ ሌላው ይተካ ጀመር። አኤሮፕላኖቹ የሚጥሉት ቦምብ አንዳንዱ በቀር ፈጥኖ የሚፈነዳ አንዳንዱ ደግሞ ጥቂት ቈይቶ የሚፈነዳ ፡ ከዚህም በቀረ በልዩ ልዩ ጊዜ የሚፈነዱ ትንንሾች ቦምቦች የያዘ ትልቅ ቦምብ ነበረ። ይህን የመሳሰለው ቦምብ በፈረቃ ሲጣል ፡ በዓቢይ ዓዲ ከተማ ላይ ያደረገው ጉዳት ግምት ያለው ነው።

በዚሁ ቀን በ፲፩ ሰዓት ተሩብ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ይጠበቅ የነበረው የጦር መሣሪያ ለልዑል እራስ ካሣ ስለ ደረሰ ለጦርነት መዘጋጀት ሆነ።

የካቲት ፲ ቀን «ማረሻሎ ባዶሊዮ በመቀሌ ከተማ በእንዳ ኢየሱስ የ፪ኛውንና የ፴ኛውን ኮር ዳርሜ አለቆች ጠርቶ ስለ ጦሩ አመራር ጉባኤ አደረገ። እንዲሁም ከ፫ ቀን በኋላ በዚሬ አውራጃ ጦርነት እንዲጀመር አዝዞ ፪ኛው የተንቤን ጦርነት ለየካቲት ፲፯ ቀን ይሆን ዘንድ አስታወቀ። ከዚህም በቀር የካቲት ፲፩ ቀን የአላጌን በሮች ይዞ የሚጠባበቅ የክፍል ጦር ላከ። የዚህም ፕላን አኳኋን የሚከተለውን ያሳያል።

፩ኛ/ የአላጌና የመተላለፊያውን። ባለቤትነት ከማረጋገጥ በላይ ከተንቤን ወደ ኋላ የሚመለሰውን ጦር መንገድ ለመከላከል።

፪ኛ/ የአላጌን መተላለፊያ የሚይዘው የጦር ሠራዊ የሚተርፍ ሲሆን ወደ ተንቤን ተመልሶ የኢትዮጵያን ጦር በስተ ኋላ ለመከበብ።

በዚህ አኳኋን ማናቸውም ከአደራጁ በኋላ ኢጣልያኖች የካቲት ፲፱ ቀን አሙስ ከጧቱ በአንድ ሰዓት የኢትዮጵያ ወታደሮች ወደ ሚገኙበት ወደ

ደብረ አምባና ወደ ወርቅ አምባ ወደ ደብረ አንሳም የመድፍ እሮምታ መተኰስ ጀመሩ። ስለዚህ በደጃዝማች መሸሻ ወልዴ የሚመራው የከንባታ ጦር ፡ ቀድሞ ፡ ከሰፈራቸው ወጥተው ወደ ፊት የሚገፉትን ኢጣልያኖች በተኩስ ተቀበላቸው። እንዲሁም በልዩ ልዩ የጦር አለቆች የሚታዘዘው ሠራዊት በወርቅ አምባ ክፍል ተሰልፎ ይከላከል ጀመረ።

በዚያን ጊዜ ጠላት የወርቅ አምባ ተራራ ባለቤት ለመሆን አስቦ ከአልፒንና ከጥቁር ቀሚስ ለባሽ ክፍል የተራራ መውጣት ልማድ ያላቸውን ወታደሮች አዘዛቸው። ነገር ግን የኢትዮጵያ ጀግኖች አናስይዝም በማለት ደህና አድርገው ተከላከሉ። ይልቁንም አምባውን ለመያዝ የተመረጡት የአልፒንና የጥቁር ቀሚስ ለባሽ ክፍል ወታደሮች በተለየ ከረጢት የታሰረ ብዙ የጅ ቦምብ አዝለው ነበርና የኢትዮጵያ ወታደሮች ካደረጉት ጠንካራ መከላከል የተነሣ በየገደሉ ላይ ሲሸሹ ቦምቡ እየፈነዳ በራሳቸውም ብዙ ጉዳት አደረገባቸው። በዚያው ክፍል ሁነው ልባዊ በሆነ ቆራጥነት የሚሠሩ ደጃዝማች በየነ አባ ሰብስብ በጀግነት እስኪወድቁ ድረስ የጨረሱዋቸው የጠላቶች ቁጥር እጅግ ከፍ ያለ ነው። የአሟሟታቸውም አኳኋን እንደ ሚከተለው መሆኑ በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ይተረካል።

ኢጣልያኖች ወደ ወርቅ አምባ እየገፉ መምጣታቸውን ደጃዝማች በየነ ወዲያው እንደ ሰሙ ወታደሮቻቸውን ሰብሰበው ጦርነቱን ለመግጠም ወደ ፊታቸው ሲገሠግሱ ከአንድ የሐማሴን ባንዳ ክፍል ጦር ጋር ተገናኙ። በዚያን ጊዜ ይህ የጠላት ጦር አፄ ምኒልክ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም በአድዋ የሠሩትን ሞያ ፡ እየጠቃቀሰ «እኛም የምኒልክ አሽከሮች ነን» የሚል የማታለያ ድምፅ አሰምቶ መንገድ ለቀቀላቸው።

ደጃዝማች በየነ የደመራ ዕለት በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ሲፎክሩ በፖሊቲክ እንዳልረደህ እውቀቴ አጭር ነው ፡ ነገር ግን በድሜ እክስሃለሁ «ብለው እንደተናገሩት ሁሉ የጀግንነት እንጂ የተንኰል ሰው አልነበሩምና ይህን ምሥጢራዊ ተንኰል ሳይከተሉ ፡ ከኢጣልያ ከድቶ ወደኛ የሚገባ ጦር

መስሏቸው ጉዟቸውን ወደ ፊት ቀጠሉ። ነገር ግን ለጊዜው በፊታቸው ተዘጋጅቶ ከሚጠብቃቸው የጠላት ጦር ጋራ ሲዋጉ ያ «እኛም የምኒልክ አሽከሮች ነን» በማለት ድምፅ ያሰማቸው ጦር በስተጀርባ ወደቀባቸው ሳያስጋቸው «ወንዶች አገር መሸሽ ነውር ነው።» እያሉ ወታደራቸውን በማበረታታት ሲሠሩ ቆስለው ወደቁ። ከቆሰሉም በኋላ ኢጣልያኖች ለመማረክ ቢቀርቧቸው «ነፍስ የሌለው ሥጋ ትማርካላችሁ እንጂ እኔ በየነ ሕይወቴ ሳታልፍ እጄን አልሰጥም» ብለው እንደወደቁ በሽጉጣቸው ብዙ ሰው ጣሉ። በመጨረሻው ግን ኢጣልያኖች የመማረኩ ነገር እንዳልሆነላቸው ስለተመለከቱ ሮምታ ተኩሰው ገደሏቸው። እንዲሁም በደጃዝማች በየነ ቀኝ ተሰልፈው በሙሉ ልባቸው ይሠሩ የነበሩት ደጃዝማች መንገሻ ይልማ ከወርቅ አምባ በሚወርድባቸው የመድፍ ናዳ ምክንያት ከወታደሮቻቸው ለጊዜው ተለይተው እዚያው ቀርተው ነበር። ቀጥሎም ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ በብርቱ ስለ ቈሰሉ በየሌላው ክፍል የሚሠራው ጀግና ምንም እንኳ የአለበትን ግንባር አጠንክሮ ቢቈይ ከዚህ በላይ እንደጠቀስናቸው ያሉ የጦር አለቆች በመሞታቸው ወይም በመቍሰላቸው ምክንያት በሌላው በኩል ያለው ኃይል በመላላቱ ይልቁንም የወርቅ አምባ ተራራ በመያዙ ጦርነቱን ሳያቋርጡ ወደ ዓቢይ ዓዲ ማፈግፈግ ግድ ሆነባቸው። ስለዚህም ኢጣልያኖች ዓርብ ከስድስት ሰዓት በኋላ ከወርቅ ዓምባ ወደ ዓቢይ ዓዲ መግፋት ጀመሩ። በዚያን ጊዜ የልዑል ራስ ሥዩም ሠራዊት በመከላከል ያደረገው የጀብዱ ሥራ የማይዘነጋ ነው።

የኢጣልያ ወታደሮች ወደ ዓቢይ ዓዲ ሲገፉ ከኢትዮጵያውያን በኩል የጠነከረ መከላከል በሚደረግበት ጊዜ በልዩ ልዩ ሥፍራ ታልቦ የተጠመደው የኢጣልያኖች መድፍ በራስ ካሣ ሰፈር ላይ ከሚተፋው የእሳት አሎሎ በላይ አኤሮፕላኖች ሊነገር በማይችል ጭካኔ ቦምብ ስላዘነሙበት ልዑል ራስ ካሣ ልዩ የጦር ፕላን ለማዘጋጀት የዓቢይ ዓዲን ከተማ ለቀው ወደ ኋላ

ከማፈግፈጋቸው የተነሣ በዚሁ ቀን በ፲፩ ሰዓት ጠላት መንደሩን ለመያዝ ቻለ።

ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም ደካማውንና ቁስለኛውን ከሸኙ በኋላ በዚያው እየተከላከሉ እንዲቆዩ ጦር ይላክላቸው ዘንድ ጠይቀው ነበረ። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ በጠላት መከበባቸውን ስለተመለከቱ ከአደጋ የተርፈውን ይዘው ወደ ዋናው የጦር ሠፈር መምጣታቸው። እንጂ በዚያ መቆየታቸው ጠቃሚ አለመሆኑን እያስረዱ ጻፉላቸው ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ ወደሚገኙበት ወደ ኰረም መጓዝ ጀመሩ። የሆነ ሆኖ ኢጣልያኖች አስቀድመው የመንገዱን ዋና ዋና በሮች በወታደሮች አስይዘዋቸው ነበርና አንድ ላይ በመጓዝ ምክንያት የሚወርሰውን አደጋ ተመልክተው የሕዝቡ አካሄድ አንዱ ቀደም ፡ ሌላው ከተል በማለት ወይም ልዩ ልዩ መንገድ በመከተል ተለያይቶ እንዲሆን ስላደረጉ ይህ አደራረግ ከጠላት መከበብ የሚያድን ሲሆን ለባላገር ዘረፉ የተመቸ ሆነለት። ስለዚህም የመንደር ጉረምሳ ጭፍራ እየሠራ ወታደሩን ለመዝረፍ ተሰልፎ ነበር። ይሁን እንጂ ወታደሩ እንደሚገባ እየተከለከለ ዘራፊውን ሊያሳፍረው ቻለ።

አስቀድሞ እንደተናገርነው በተንቤን ጦርነት ላይ በጀግንነት ሲዋቱ የቈሰሉት ደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ከቈስሉ ብርታት የተነሣ በጉዟቸው ሁሉ ይሠቃዩ ነበር። እንዲሁም የቈሰሉበትን የቦምብ ፍንጣሪ ከማውጣት በቀር የሐኪሞች እርዳታ ሕመማቸውን ሊቀንስላቸው አልቻለም ነበር። ራስ ካሣና ራስ ሥዩም ምንም እንኳ የችግርና የጭንቅ ጊዜ ቢሆን ለቁስለኛው ለደጃዝማች መሸሻ የሚያስፈልጋቸውንና ሊያደርጉላቸው የሚችሉትን ሁሉ ሳያጓድሉባቸው አስቀጣ ሲደርሱ በመጋቢት ወር በሁለተኛው ሳምንት ውስጥ ዐረፉ። ራስ ሥዩምና ራስ ካሣ በጉዟቸው ዙሪያውን የከበበ የጠላት ጦር ሳያገኛቸው ከደጃዝማች መንገሻ ይልማና ከደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ ፡ ከደጃዝማች አበራ ካሣና ከደጃዝማች ኃይሉ ከበደ ፡ ከሌሎችም መኳንንቶች ጋራ መጋቢት ፲ ቀን ለ፲ አጥቢያ ሌሊቱን እኰረም ደርሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ተገናኙ።

## ምዕራፍ ፲፯።

## የጀነጋብ ጦርነት።

የውጋዴን ግንባር ጠቅላይ አዝማች ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል ዋና የጦር ሠፈራቸውን በደገሀቡር አድርገው በልዩ ልዩ የጦር ግንባር እየተዘዋወሩ ወታደር ባነሰበት እንዲጨመር ፡ መሣሪያ ባስፈለገበት እንዲላክ ስንቅ ባለቀበት እንዲደርስ እያደረጉ ኃላፊነታቸውን በትጋት በመፈጸማቸው መልካም ዓርዓያን ትተዋል። ይልቁንም ለጦርነቱ መልካም አካሄድ ብቻ ሳይሆን መላው የሐረር አውራጃ ጸጥታ የሚያገኝበትን ሁሉ በመሥራት ይደከሙ እንደነበረ እርግጥ ነው። ስለዚህም ለሐረር ሕዝብ ከጻፏቸው ደብዳቤዎች አንደኛው እንደዚህ የሚል ነበረ።

«ይድረስ ከሐረር ላላችሁ መኳንንቶችና ሹማምንቶች ለተከበሩ ሴቶቻችሁም በከተማውም ላላችሁ ዘበኞችና ለሰልፍ ወታደሩም ሚስቶችና ለቀራችሁትም ለቤተ ዘመዱ ሁሉ። እንደምን ውላችሁ አድራችኋል እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን ግርማዊ ጌታዬ የጣሉብኝን ትልቅ እምነትና የተቀበሉትንም አደራ ለመጠበቅ ለአገሬና ለጃንህይ መንግሥት ሕይወቴን ለማሳለፍ ቁርጥ ስላደረግሁ በቀደም ዕለት ከፊታችሁ ስሄድ ልቤ በኅዘን እንደተነካ ሳይታወቃችሁ አይቀርም። አሁንም ሳይበዛ ባጭር ቃል የማስታውቃችሁ ቀጥሎ ያለውን ነው።

የእግዚአብሔር ፍርጃ ካልሆነ በተቀር በጌታዬ ግንባርና በፈጣሪዬ ኃይል ኮርቼ ስለዘመትሁ ምንም ቢሆን በኔ ቸልታና በኔ አላዋቂነት የጌታዬን ቤት ሐረርን በጠላት የማስወስዳት አይመስለኝምና አትርሱኝ። ግን የሰው መቋቋሚያው በመንፈስ ቅዱስ ወገን የሚጠቅም ኀዘን በኑሮው ወገን የሚያስፈልገ ምግብ ሲያገኝ ነውና በዋዛ በፈዛዛ ሳይሆን በጥልቅ ልባችሁ እያዘናችሁና ሲቸግረን እያሰባችሁ መቋቋሚያችንን የበቃ ስንቅ እንድትልኩልን ይሁን። ላገራችንና ለጌታችን አልጋ ስንል ፡ አንድም ለናንተ

ለኑሮአችሁና ለደህንነታችሁ ስንል ከጠላት ጋራ እየተከላከልን ንጹሕ ደማችንን የምናፈስ ስለሆነ በአገር ያለውና በከተማ ያለው ጐበዝ ሁሉ እየዘመተ ሊረዳን የተገባው ነውና እየተሾለከ እመንደር ለቀረ ሰው የሊጥ ፡ ሌባ የሚባል ስም አውጥታችሁለት ከመንደር እያስወጣናችሁ አፋጥናችሁ እየሰደዳችሁልን እንዲረዳን እንድታደርጉልን በራሴ ስምን በወታደሩም ስም ሆኜ በጥብቅ እለምናችኋለሁ። የመንደር ወስላታም ሊያጠቃችሁና ሊያጠቃችሁና ሊጐዳችሁ የፈለገ እንደሆነ ብርቱ ጠባቂዎች አድርገናልና አጥፊው ተመርምሮ እየተያዘ እዚሁ እንደሆነ ብርቱ ጠባቂዎች አድርገናልና አጥፊው ተመርምሮ እየተያዘ እዚሁ ሐረር ላይ እፊታችሁ የተገባ ቅጣቱን እንዲያገኝ እናደግላችኋለን።

ትልልቆቹ ችሎታ ያላችሁ ሰዎች የዘማቹንና የወታደሩን ሚስቶች ጥቃት እንዳያገኛቸው አባቶቹም ዘመናችሁ የማፈቅድላችሁ ሆኖ ከዘመቻም ብትቀሩም ፡ የዘመተው ሁሉ ወገናችሁናን ልጃችሁ ነውና ሌትም ቀንም በማያቋርጥ ልመና ሳታዝኑልን ትቀራላችሁ ብለን አንጠራጠርም ፡ አደራችሁን እንግዲህ እግዚአብሔር አምላክ በፈቀደ ጊዜ ደህና ያገናኘን ደህና ሁኑ ደህና ሰንብቱ።

እላይ እንደተናገርነው ደጃዝማች ነሲቡ የአገሩ ጸጥታ እንዳይደፈርና የጦሩ ግንባሩ እንዳሰበር በሚጥሩበት ጊዜ በአቅራቢያቸው ሆኖ የሚረዳቸው የቱርኩ ጄኔራል ዊሂብ ፓሻ ነበረ። እርሱም በየጊዜው የቆራጥነት መንፈስ ስላሳየ በኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ዘንድ ዋጋ ያለው ሰው መሆኑን አስረድቷል ለማለት ይቻላል።

በደጃዝማች ነሲቡ መሪነት በውጋዴን ግንባር ልዩ ልዩ የጦር ሜዳዎች ከሆኑት ቦታዎች አንደኛው ጀነጋብ ነው። ይኸንንም የጦር ግንባር የከፈቱ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው ፡ ደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸውና ፡ ፊታውራሪ ሽፈራ ባልቻ ናቸው።

ከደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸው ጋራ በካራ መራ አጠገብ በአደው ሬዜርብ ሆኖ እንዲቀመጥ የታዘዘው ፬ሺ የሚያህል የኢሉባቦር ጦር ሹማምንቶች ፡ ስንቃችን ሳያልቅና ኃይላችን ሳይቀንስ ወደ ጦሩ ግንባር እንድንሰለፍ ይፈቀድልን እያሉ በየጊዜው ለአለቃቸው ለደጃዝማች መኰንን ያመለከቱ ነበርና ይህንኑ መልካም ፈቃዳቸውን ወደ ጠቅላዩ አዝማች ወደ ደጃዝማች ነሲቡ ስለአስተላለፉላቸው ፡ ደጃዝማች ነሲቡ ወደ ጅጅጋ መጥተው በነበረበት ጊዜ ስለዚሁ ጉዳይ ምክር ለማድረግ ደጃዝማች መኰንን ዋና ዋናዎቹን ሰዎች ይዘው እንዲመጡ ተፈቀደ። በዚያን ጊዜ የነበሩት የኢሉባቦር ሽለቆ የሚከተሉት ናቸው።

| | |
|---|---|
| ፊታውራሪ አበበ መብረቁ የደጃዝማች መኰንን | እንደራሴ። |
| ፊታውራሪ መኰንን ኃይሌ (የስሌ ምስለኔ) | እንደራሴ። |
| ፊታውራሪ ገብረ ሥላሴ አባውርጌ | እንደራሴ |
| ፊታውራሪ ከበደ ዘውዴ | እንደራሴ |
| ፊታውራሪ ኃይለ ማርያም ጣሴ | እንደራሴ |
| ፊታውራሪ መኰንን ዘርጋው | እንደራሴ |
| ፊታውራሪ ዳርጌ | እንደራሴ |
| ቀኛዝማች ደምሴ (የነፍጠኞች አጋፋሪ) | |
| ቀኛዝማች ግዛው በፈቃዱ | |
| ቀኛዝማች ጣሹ (የዘበኞች አለቃ) | |

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ሹማምንቶች ስለአቀረቡት አሳብ ምክር ለማድረግ ቀጥሎ ያሉት መኳንንቶች በጅጅጋ ተሰበሰቡ።

| | |
|---|---|
| ደጃዝማች ነሲቡ ዛማኔል | የሐረር ገዢ |
| ደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸው | የኢሉባቦር ገዢ |
| ደጃዝማች ዓምደ ሚካኤል | የአሩሲ ገዢ |

| | |
|---|---|
| ደጃዝማች ሀብተ ሚካኤል | የከሎና የኮንታ ገዢ |
| ጄኔራል ውሂብ ፓሻ | አማካሪ |

አሳቡ ለጉባኤው ቀርቦ በሚመረመርበት ጊዜ ፊታውራሪ ኃይለ ማርያም ጣሴ አፈፍ ብለው ተነስተው «አንድ ላይ በመሰብሰብ ምክንያት በሚነሣው ደዌ ከማለቅ አንዳንድ ጠላት እየያዙ መሞት ክብር ነው» ብለው ከተናገሩ በኋላ ወዲያው ፈንቀ አደረጋቸውና ያለፈውን ታሪካቸውን እየጠቃቀሱ ፉከራውን ይደቀድቁት ጀመር። በዚሁ ጊዜ ጄኔራል ውሂብ ንግግር እንዲያደርግ ፈቃድ ጠየቀና ከከፍተኛ ቦታ ላይ ሆኖ በዚያ ለተሰበሰበው ሰው እንዲህ ሲል ጀመረ።

«የኢትዮጵያን ሕዝብ ጀግንነት በጆሮዬ እንደሰማሁት በዓይኔ ላረጋግጥ ጊዜው ስለፈቀደልኝ አጥብቄ እደሰታለሁ ፡ እኔም ወደዚሁ አገር የጦር ሰው ሆኜ ስመጣ ከጀግኖች ጋር መሞት ቅዱስ መስዋዕት መሆኑን በመረዳት ነው»

ጄኔራል ውሂብ በብዙው ተናገሮ የመጨረሻ ምኞቱ ከአርበኛው ሕዝብ ጋር የሞተ ተሣትፎ እንዲኖረው መሆኑን ከገለጸ በኋላ ስቅቅ የሚያደርግ እንባ አነቀውና ንግግሩን አቋረጠ። ስለዚህ በዚያ የሚገኘው ሕዝብ ሁሉ በጥልቅ ተነካ።

እላይ የጠቀስነውን አሳብ ለመመርመር የተሰበሰበው ኮሚሲዮን ነገሩን እንደገና እንዲያጠናው ፡ የሚያስፈልገውም ቢሆን ወደ ንጉሠ ነገሥቱ በቴሌግራም እንዲያመለክት ከተወሰነ በኋላ ደጃዝማች መኰንን ከነሠራዊታቸው ተሰናብተው ወደ ቀደመ ሠፈራቸው ወደ ኢደው ተጓዙ፡

ወደ የካቲት ወር መጨረሻ ደጃዝማች በየነ መርድ የጠላት ኃይል ተጭኖአቸው ወደ ኋላ ማፈግፈጋቸው ስለ ተሰማ ዝም ብሎ መመልከት አስፈላጊ አለመሆኑን በመረዳት ይህንንኑ አስታውቆ ሥንቅና መሣሪያ እንዲያመጣ ወደ ደጃዝማች ነሲቡ ቀኛዝማች መንግሥቱ የሚባለውን

ልከው ወደ ፊት ጉዟቸውን ቀጠሉ። እንዲሁም አስቀድሞ ስለዚሁ ጉዳይ ከደጃዝማች አበበ ዳምጠውና ከፊታውራሪ ሽፈራው ጋር በደብዳቤ ይነጋገሩበት ነበርና ብርቆት ከሚባለው ወንዝ ተገናኝተው ምክር አደረጉ።

በዚያን ጊዜ ኢጣልያኖች በታኅሣሥ ወር መጨረሻ በያዙት በጣናን ላይ ምሽጋቸውን አጠንክረው ወደ ፊት ለመግፋት ድርጅት ያደርጉ ነበር።

ከዚህ በኋላ ደጃዝማች አበበ ዳምጠው፣ ደጃዝማች መኰንን እንዳልካቸውና ፡ ፊታውራሪ ሽፈራው ፡ ጀነጋብ ላይ ሰፍረው የጠላትን ምሽግ ለማፍረስ የሚቻልበትን አሳብ እንዲያጠኑ ጉባኤ ያደርጉ ዘንድ ገና በቀጠሮ ሳሉ ፊታውራሪ ደፈርሻው ጅማ ከአኤሮፕላን አደጋ መጠለያ የሚሆኑ ዋሻዎች ለመፈለግ ተላኩ። ነገር ግን የሚያስፈልጋቸውን ከማግኘታቸው ፡ በፊት በጀነጋብ ወንዝ ላይ ደፍጠው ከሚጠባበቁት የጠላት ቃፊር ወታደሮች ጋር ተገናኝተው ተኲስ ተለዋወጡ። እንዲሁም ተኵሱ እየበረታ ስለሄደ ደጃዝማች አበበ ወደ ደጃዝማች መኰንን መልክተኛ ከላኩ በኋላ አጠገባቸው የሚገኘውን ጦር ቀስቅሰው ቀደሙ። ነገር ግን ቃፊሮቹ ስፍራውን ለቀው ሸሽተው ነበርና ፊታውራሪ ደፈርሻው በፈረስ ተከታትለው የማይደናባቸው ቢሆን ሲመለሱ ለርሳቸው እርዳታ የሚገሠግሡትን ደጃዝማች አበበን በመንገድ አገኙዋቸው። በዚያን ጊዜ ደጃዝማች አበበ ትጥቃቸችንን ያላንዳች ሥራ እንዴት እንፍታው? ሲሉ ወዲያው በጠላት ምሽግ ላይ የመውደቅን አሳብ አቀረቡ። ነገር ግን መኳንንቱ ጊዜው ከመምሸቱ በላይ እንዴት ፡ ወይም በምን እንደተሠራ በማይታወቅ ምሽግ ላይ መውድቅ የማይጠቅም መሆኑን ካስረዱዋቸው በኋላ ወደ ሰፈር ተመልሰው የፋሲካን በዓል ሚያዝያ ፬ ቀን በዚያው አሳለፉ። ሰሞኑንም የጠላት አኤሮፕላኖች ያለማቋረጥ እየተመላለሱ ቦምብ ይጥሉ ነበር።

ጄኔራል ግራዚያኒ ሚያዝያ ፯ ቀን ፡ ደናኔ መጥቶ በጄኔራል ናዚ የሚታዘዘው የሊብያ ዲቢዚዮን ድርጅት እንዴት እንደሆነ ከተመለከተ በኋላ

ስለ ሰዓቱ ምቹነት ለጊዜው የደረሰውን ኢንፎርማሲዮን መሠረት አድርጎ በማግሥቱ ሚያዝያ ፮ ቀን ማክሰኞ ወደ ፊት እንዲገፋ አዘዘ። ይሁን እንጂ የኛዎቹ የሚበቃ ድርጅት ካለማድረጋቸው በላይ ወታደሩ ስንቁን እንዲገዛ በያለበት ተሰማርቶ ነበርና ጠላት የጀነጋብን ወንዝ ለመሻገርና በሰፈራቸው ላይ ድንገተኛ አደጋ ለመጣል ቀርቦ እንዳለ ማየታቸው እንግዳ ነገር ሆነ። ስለዚህ በቅርቡ ለሚገኘው ወታደር የጥሩንባ ምልክት ከተሰጠ በኋላ በጋንጋቦ መሻገሪያ ሚያዝያ ፯ ቀን ረቡዕ ከጧቱ በ፬ ሰዓት ጦርነቱ ተጀመረ።

በዋንዴ በኩል የተሰለፈው የኛ ወታደር መከታ የሚሆን ሥፍራ ሲያገኝ በሌላው በኩል ያለው ለጠላት መሣሪያ ግልጽ በሆነ ቦታ ላይ ጉዳት ማድረጉ ያጽናናል።

ሚያዝያ ፯ ቀን ከጧቱ በ፬ ሰዓት የተጀመረው ጦርነት እስከ ሚያዝያ ፰ ቀን ምሽት ባለማቋረጥ ሲቀጥል ቆየ። ነገር ግን የጠላት ክፍል በመሣሪያ ላይ መሣሪያ ፡ በወታደር ላይ ወታደር እየተጨመረለት ከመሄዱ በላይ በኛ ደጀን ወታደር ላይ ቦምብ ስላዘነመበት ወደ ኋላ ተመልሶ የሚበቃ ድርጅት ማድረግ የተሻለ መሆኑ ተገመተ። ስለዚህ ሚያዝያ ፱ ቀን ዓርብ የኛ ወታደሮች ሰፈራቸውን ወደ ጭቆት ለማዛወር ተነሡ።

ለጊዜው መሪ አድርገው የያዙት አንድ ሱማሌ ከጠላት ጋራ ግንኙነት ያለው ኖሮ ወደ ጭቆት በመምራት ፈንታ የኢጣልያኖች ምሽግ ካለበት ብርቆት ከሚባል ሥፍራ ጣላቸው። በዚያን ጊዜ ይህ ከዳተኛ ሱማሌ እንዲገደል ከተደረገ በኋላ ሊታለፍ የማይቻለውን ጦርነት የሚያዝያ ፲ ቀን እሁድ ሲነጋጋ ገጠሙ።

የኛ ጦር ሠራዊት ወደ ጭቆት ይጓዝ የነበረው በሌሊት ስለ ነበረ መንገድ በመሳሳት ተለያይቶ ሳለ ሊነጋጋ አቅራቢያ ይህ ድንገተኛ ጦርነት በመነሣቱ ምንም እንኳ እንደሚገባ ለመሥራት ጊዜው ባይፈቅድ እስከ ማታ ድረስ በጥንካሬ ሲከላከል ቆዬ። ለዓይን ከያዘም በኋላ ተኩሱ ጋብ ስላለ ያንኑ የሌሊት ጉዞውን ይቀጥል ጀመረ። በዚያን ጊዜ ከደጃዝማች መኰንን

እንዳልካቸው ሰዎች አንድ ትልቅ ጀግና ሰው ወድቆ ነበርና የሞቱትን ሰዎች ለማስቀበር ምቹ ሰዓት ካለመሆኑ የተነሣ የቀረው ወታደር ከታሰበው ሥፍራ ለመድረስ ሲጣደፍ ከ፲፫ እስከ ፲፭ ዓመት ብቻ ሊኖረው የሚችል የዚያ የጀግናው ልጅ ፡ አባቴን አፈር ሳላለብስ ወደ ሌላ ለመሄድ አልንቀሳቀስም ብሎ ከዚያው ቀረ ይባላል።

በለጋዎቹ ወጣቶች ይህን ያህል ድፍረትና ቆራጥነት ሲታይ በታላላቆቹማ ዘንድ ምን ያህል የበለጠ ግምት ሊኖረው ይሆን?

ከዚህ በላይ የጠቀስነው የብርቆት ጦርነት አደራረግ በጀነጋብ ከሆነ ጦርነት ቢበልጥ እንጂ አያንስም። በሁለቱም ተዋጊ ወገኖች ከፍ ያለ ጉዳት መድረሱ አያጠራጥርም።

## ምዕራፍ ፲፰።

## የማይጨው ጦርነት።

ልዑል ራስ ካሣና ልዑል ራስ ሥዩም ወደ ኰረም ተመልሰው ከንጉሠ ነገሥቱ ከተገናኙ በኋላ በግርማዊነታቸው ቀጥተኛ መሪነትና አዛዥነት ስለሚደረገው የማይጨው ጦርነት በኰረም ጉባኤ ተደረገ።

ኢጣልያኖች ከማይጨው ጦርነት አስቀድሞ ግርማዊነታቸው በጠና ታመዋል ሲሉ ያስወሩት ወሬ ለሰሜን ጦርነት ተንቤን መጨረሻው ሊሆን ነውን? በማለት የብዙ ሰዎችን አሳብ በምርመራ ላይ ጣለው። ስለዚህም በትሪቡናል በኩል የጋዜጣ መልክተኞች ከጻፉት አርቲክል አንደኛው እንዲህ የሚል ነበር።

«በዕለት ወሬ አኳኋን በመጨረሻው ስለ ንጉሠ ነገሥቱ ጤንነት በጅቡ የሚዘዋወሩ ቃላት ይሰማሉ ፡ ይኸውም ንጉሠ ነገሥቱ በብርቱ ቆስለዋል

እየተባለ በሚወራበት በአዲስ አበባ ቤተ መንግሥት ብዙ ሥጋት የሚፈጥር ይመስልላ። ምንም እንኳ (ንጉሠ ነገሥት) ኃይለ ሥላሴ ፡ እንዴት ወይም መቼ እንደቆሰሉ ባይረጋገጥ የንጉሡ ልዩ ሐኪም የሆነው የኢጣልያ ግልጸኛ ጠላት ፡ ፍላነር የሚባለው የስዊስ ሰው ወደ ደሴ መጠራቱና የህክምና መሣሪያውን ይዞ በአኤሮፕላን መሄዱ እርግጥ ነው።

ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት እየተጨማመረ ስለ ልዑል አልጋ ወራሽና ስለ ልዑል መኰንን መስፍን ሐረር ስለ ልዑል ራስ ካሣም የተወራው ሐሰተኛ ወሬ ምናልባት ፈጥነው የሚያምኑትን ሰዎች ሊያሸብራችው ችሎ ይሆናል እንጂ በጠቅላላው የሕዝቡ መንፈስ የረጋ እንደነበረ አያጠራጥርም። የሆነ ሆኖ ቆስለዋል ተባለ የተወራባቸው ጠላትን በማይጨው የጦር ከመቁሰሉ በላይ የሚሆነውን ነገር ሊፈጽሙበት ታጥቀው እንደተነሡ በተረጋገጠ ጊዜ ለሐሰተኛው ወሬ ምን ዓይነት መጠገኛ ተሰጥቶ ይሆን?

እላይ እንደተባለው ስለ ማይጨው ጦርነት ጉባኤ ከተደረገ በኋላ መጋቢት ፲፩ ቀን የጠላት የጦርነት ጦር አቀማመጥና የኛም ወታደር ወደ ፊት ገፍቶ ሰፈር ሊያደርግበት የሚቻልበትን ቦታ ፕላን አንስተው የሚመጡ ኦፊሴሮች ላኩ። በዚያን ጊዜ ኢጣልያኖች ብርቱ ምሽግ ሠርተው የሰፈሩበት ከአይላራቅ ብሎ በሚገኘው ተራራ ጥግ ነበረ።

ንጉሠ ነገሥቱ ጦርነቱን በተቻለ ፍጥነት ለመግጠም ምንም እንኳ ቢያስቡ አንዳንድ ሰዎች ጦርነቱን ማዘግየት ጠቃሚ ይሆናል እያሉ አስተያየታቸውን ከማቅረብ አልቦዘኑም ነበር። ነገር ግን ምናልባት ከስሳ ሺህ የሚበልጥ ጦር ከአኤሮፕላን አደጋ የሚጠለልበት በቂ ዋሻ ከማይገኝበት ቦታ አስፍሮ ጦርነቱን ለማዘግየት ማሰብና ማሳሰብ አንዳች ጦርነት ሣያደርግ በየቀኑ በቦምብና በጋዝ ምክንያት ቍጥሩ እንዲቀንስና እንዲመረር ከማድረግ በቀር ጠቃሚነቱ ግምት አላገኘም። ስለዚህ እንደ ንጉሠ ነገሥቱ አሰያየት ሁሉም ስለተስማሙበት ጥድፊያ ያለው ድርጅት ማድረግ ተጀመረ።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሁል ጊዜ እንደሚያስረዱት እምነታቸው በፈጣሪያቸው ላይ ስለሆነ የቅዱስ ጊዮርጊስን ጽላት ይዘው በእጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ በሊቀ ካህናቱ በሊቁ ገብረ ክርስቶስ መሪነት በአቡነ ጴጥሮስና በነሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ አሳቢነት የተከሏቸው ካህናት ጸሎተ ማኅበር በሚያደርጉበት ጊዜ ሁሉ አይለዩም ነበር። እንዲሁም መጋቢት ፲፫ ቀን አይላ ከሚባለው ሥፍራ ለግርማዊነታቸው ማረፊያ ከተዘጋጀላቸው ዋሻ ውስጥ ካህናቱ ጸሎተ ማኅበርና እግዚአታ ሲያደርሱ አንድ ባለ ሶስት ሞተር አኤሮፕላን መጥቶ ዋሻውን ከዞረ በኋላ ወደ ዋሻው ለመግባት የቃጣ መስሎ ታየ። ወዲያውም የያዘውን ቦምብ ሲያራግፈው በአቅራቢያው የሚገኙ ሰዎች ወደ አኤሮፕላኑ ከሚተኩሱት ጋራ የአኤሮፕላኑና፣ የቦምቡ ድምጽ እየተሰባጠር ምድርን የሚያናውጿት መሰለ። በዚያን ጊዜ በብጫ ቀለም አምሳል ከአኤሮፕላኑ የሚፈልቀው ጭስ እንደ ቀስተ ደመና ሰለ ተዘረጋ በዚያ በነበሩ ሰዎች እልልታውን አቀለጡት። ጭሱ ከአኤሮፕላኑ ፈልቆ መታየቱ ቀረና አኤሮፕላኑ በመላው ጭስ ብቻ ሆነ ፡ ማለት ጨርሶ ተቃጠለ።

ግርማዊነውታቸው ልባዊ የሆነ ጸሎተ ማኅበር በሚያደርስበት ጊዜ ሊፈታተን የመጣው ጠላት በእሳት ተከቦ መጨነቁን ለማየት መብቃት ከተአምራት የበለጠ ተአምራት ነው።

ስለዚህ ግራማዊነታቸው ይህን ተአምራት ፡ ጸሎተ ማኅበር ያፈራው መሆኑን በመገንዘብ ለጊዜው ጸሎቱን እንደማቋረጥ አሉና ፍሬውን ለመመልከት ከካህናቱ ጋራ ወጥተው ከማድነቅ ጋራ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ወዲያውም ተመልሰው ጸሎቱ እስኪፈጸም ድረስ ቆዩ።

በዚያው ሰሞን የጠላት አኤሮፕላኖች አላስወጣ አላስገባ ብለው በጣም አሰልችተው ነበር። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያም ወታደሮች ብዙዎቹን ፡ በተኩስ ጥለዋቸዋል። ከዚህ በኋላ መጋቢት ፲፱ ቀን በአቅራቢያው የነበሩ የአዘቦ ጋላ ባላባቶች መጥተው ከግርማዊነታችው ተገናኙ። እንዲሁም የጋራ ጠላታችንን ለመውጋት ዝግጁዎች ነን ሲሉ ቃላቸውን ሰጡ። ስለዚህ

ለታላላቆቹ ካባና ቀሚስ ፡ ለታናናሾቹ እጀ ጠባብና ሱሪ ፡ ከዚህም በቀር የመሣሪያና የብር ሽልማት ሰጥተው አሰናበቷቸው። በማግሥቱ መጋቢት ፳ ቀን እሁድ ወደ ማታ ግርማዊነታቸው የኢጣልያኖችን ሰፈር ለማየት ምቹ ከሆነ በአቅራቢያው ከሚገኘው ካንድ ተራራ ላይ ወጥተው መጀመሪያ የኛ መድፍ ሊጠመድበት የሚገባውን ሥፍራ አመለከቱ ይህ ግርማዊነታቸው የሚገኙበት ተራራ ከኢጣልያኖች ሠፈር የሚርቀው ፫ ኪሎ ሜትር ብቻ ቢሆን ነው። በዚያም ደጃዝማች ወልደ አማኔል ለግርማዊነታቸው ማረፊያ የሚሆን ሥፍራ እያዘጋጁ ነበሩ። ግርማዊነታቸው ግን ለጊዜው እዚያ ሳይርፉ ከኮረም ወደ ማይጨው የሚያልፈውን መንገድ ለመመርመር በዘብጡ በኩል ሲሄዱ በባላገር ጦርነት ምክንያት ከራስ ሙሉጌታ ጋራ የወድቁት ሰዎች ሬሳ ለዱር አራዊትና ለሰማይ ወፎች ተጥሎ በማየታቸው በጣም አዘኑ። ደማቸውም እጅግ ተቈጣ፣ ግን ብድራታቸው የሚከፈልበትን ሰዓት ብቻ መጠበቅ አስፈላጊ ሆነ። ከዚህ በኋላ ግርማዊነታቸው የጦር አለቆችን ሁሉ ጠርተው ቀጥሎ ያለውን ምክርና ትእዛዝ በጽሕፈት እያደረጉ ሰጧቸው።

እንኳን ይህ ያሁኑ የመጨረሻው የታላቁ ጠላታችን ጦርነትና የአውሬ አደን እንኳ ቢሆን ቆራጥ ለመሆን ከቂም ከበቀል መራቅ የሚያስፈልግ ነው። ለጦር የቀረበ ወንድ ልጅም ባለፈው ሁለት ልብ በሆነው ወታደር ሁሉ እግዚአብሔር የፈረደበትን ዓይታችኋልና እግዚአብሔር ይፈርድብኛል ብሎ ልቡን ልቡን ታዛቢ አድርጎ ሥራ ካልሠራ በነጅና በትእዛዝ ብቻ የሚሠራው ሥራ ዋጋ የሌለው ነው። ቆርጦ ከአልሠሩ ሲሸሹም መሞት አለ። እግዚአብሔርም የሚረዳው ልቡ ለቈረጠ ጨከኖ ለሠራ ነውና ስለ አገራችሁ ስለ ኢትዮጵያ የነፃነቷ ባንዲራ እንዳይቀደድ ፡ ግዝቱን ጥጻችሁ ሞት ላይቀር የነፍሳችሁንም የሥጋችሁንም ዋጋ አበላሽታችሁ አትሙቱ።

አለቃየ ሸሸ ፡ ሞተ ሬሣ አነሣለሁ ማለት ፡ ለቁስለኛው አዝኖ አይደለም አለቃው ሲሞት ጠንክሮ የተዋጋ አንዱ ወታደር አለቃ ይሆን የለም?

እግዚአብሔር ቀኙን ቢሰጠን ገንዘባችንና ሀብታችን የኢትዮጵያ መቆም ነውና ለገንዘብ መሻማት አትቸኩሉ።

የቆሰለም ምርኮኛ ፈረንጅ ብታገኙ ምርኮ መገኘቱ የጠላትን ምሥሪር ለማወቅ ይረዳናልና በጁ ጩቤ ወይም ሽጉጥ ወይም የሚፈነዳ ነገር ይዞ የሚያበላሻችሁ ካልሆነ በቀር አትጨርሱት።

ሎሌ ከጌታው ጭፍራ ካለቃው ከተለየ ሽሽት መጀመሩ ነውና የኔም የኢትዮጵያም ጠላት መሆኑን እወቁት። ጦርነቱም ሲጀመር ባግዳይም በምርኮም የቀናው ሰው በመጨረሻ ድሉ ካልተረጋገጠ ያንድ ሰው ገድሎ መምጣት ብቻ ጠላትን ድል ከማድረግ አይቆጠርም። ጦርነቱ እስኪያልቅ መግፋት ነው እንጂ ግዳይ ለመጣል አይመለስም።

ወደ ጦርነቱ በምትቀርቡበት ጊዜ ሌሊት ተጉዛችሁ ነውና ጠላት ድምጻችሁን የሰማ እንደሆነ ፡ መብራት ይዛችሁ ያየ እንደሆነ ጠላትን በገዛ እጅ ማንቃትና ማስጠንቀቅ ስለሆነ ተኩስ እስቲጀመር እርስ በርሳችሁ እንዳትጣሩ እንዳትጩሁ እንዳታቅራሩ መብራት እንዳታበሩ ይሁን። ገንዘብና መሣሪያችን የኢትዮጵያ መዳን ነውና ብረት እንማርካለን ብላችሁ እየተሽከማችሁ ጠላት እንዳታበርሩ ጉልበታችሁን እንዳታደክሙ።

ወደ ጦርነቱም በምትሄዱበት ጊዜ እዚህ የሚቀረው ጓዝ በቡዙ ተበታትኖ እሳት ያንድድ ፡ ምክንያቱም ጠላት መጠጋታችንን እንዳይጠረጥርና ሰው በየሰፈሩ ነው ያለው ብሎ እንዲያምን ነው።

ጦርነቱ ሊደረግ የተወሰነበት በማግሥቱ መጋቢት ፳፩ ቀን ሰኞ ነበረ። እንዲሁም ምንም እንኳ የማይታመን ቢሆን የአዘቦ ጋሎች ለእርዳታ እንደርሳለን ብለው ቀጠሮ የሰጡት በዚሁ በመጋቢት ፳፩ ቀን ነበረ። ነገር ግን የጦር ሜዳ ሊሆን የሚገባውና ጠላትን ለመክበብ የሚቻልበትን ዋና ዋና ሥፍራ ደህና አድርጎ ማጥናት የሚያስፈልግ ከመሆኑ በላይ ራስ ጌታቸውና ሊጋባ ጣሰው ሙሉ ድርጅት ለማድረግ ጊዜ ይሰጠን ብለው ስላመለከቱ ጦርነቱ ለሰኞ መሆኑ ቀርቶ ለማክሰኞ ተወሰነ።

ማረሻሎ ባዶሊዎ ስለ ጦርነቱ በጻፈው ድርሰቱ (ገጽ ፩፻፸፬) የሚበቃ ድርጅት አላስደረግንም የማለት ምክናይት ለመስጠት እንዲመቸው ንጉሠ ነገሥቱ ጦርነቱን ለመቀጠል በቁርጥ መምጣታቸውን በርግጥ እያወቀ የመጠራጠር አኳኋን እንዳለው በማስመሰል ተናግሯል። ነገር ግን በዚያን ጊዜ በሰፈሩ ላይ እንዴት ያለ ሽብርና ድንጋፄ እንደ ነበረ ሽብሩ ድንጋፄው ያጠለቃቸው ኢጣልያኖች ሁኔታውን ምንም እንኳ በጽሕፈት ላይ ለማዋል የሚያሳፍር መስሎ ቢታያቸው፣ በቃላቸው ሲተርኩ ሰምተናቸዋል። ስለዚህም ከማናቸውም ጊዜ የበለጠ ድርጅት ማድረጋቸው አያጠራጥርም።

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት መጋቢት ፳፩ ቀን ሰኞ ጧት ከተራራ ላይ ወጥተው በመሐን ሰፍሮ የነበረውን የጠላትን ጦር በመነጥር ሲመለከቱ ባንድነት እጅብ (ስብስብ) ብሎ መታየቱ የሚያጕመዥ ከመሆኑ የተነሣ ከተራራው የተጠመዱትን መድፎች አስተኰሱበት። መድፎቹ በሚገባ ታልበው የተጠመዱ ከመሆናቸው በላይ ተኳሾቹም አስታዋይዎች ስለሆኑ ያላንዳች ስሕተት ሰፈሩ መደብደቡና ጉዳትም መድረሱ አይካድም። ስለዚህም የጠላት ጦር ለሰፈሩ መከታ ያለው ቦታ መፈለግ ግድ ሆነበት። እንዲሁም ከኛ በኩል ስለተተኰሰው መድፍ ብድር ለመክፈል ኢጣልያኖች ወደኛ የጦር ሠራዊት ሠፈር መድፍ ይተኩሱ ስለ ነበረ አረሩ ግርማዊነታቸው በቆሙበት በኩል ያፏዋጭ ነበረ።

በዚሁ ቀን ግርማዊነታቸው ስለ ጦሩ አመዳደብና አመራር ስለ ሌላውም አደራረግ ከመኳንንቶቻቸው ጋር ከተመካከሩበትና ከተስማሙበት በኋላ ለጠቅላላው የጦር ሠራዊት ፫ አበጋዞች መረጡ። እነዚሁም የሚከተሉት ናቸው።

፩ኛ ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ

፪ኛ ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ

፫ኛ ራስ ጌታቸው አባተ

እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት አበጋዞች የመጀመሪያው በመካከል ፡ የሁለተኛው በቀኝ የ፫ኛው በግራ የሚመራውን ግንባር እንዲከተሉ ተደረገ።

ምንም እንኳ ከ፫ኛው አበጋዝ በቀር የመጀመሪያዎቹ ሁለት አበጋዞች ከአሥር አሥር ሰዎች ጋር ሆነው ግርማዊነታችው ጋር እንዲሰለፉ ቢደረግ ሠራዊታቸው በልዩ ልዩ እንደራሴ መሪነት የተመደበለትን ግንባር አልዘነጋም።

ከግርማዊነታቸው ጋራ እንዲሰለፉ በተለይ የተመረጡት ታላላቅ ሰዎች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው።

| | |
|---|---|
| – ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ | ደጃዝማች ወንድ ይራድ |
| – ብፁዕ እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ | ሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ |
| – ልዑል ራስ ካሣ | ደጃዝማች ወንድ ወሰን ካሣ |
| – ልዑል ራስ ሥዩም | ደጃዝማች አበራ ካሣ |
| – ፊታውራሪ ብሩ | አቶ ወልደ ጊዮርጊስ ወ.ዮ |

ከዚህ በኋላ ከሌሊቱ ፲ ሰዓት ሲሆን የጦር ሠራዊቱ ወደ ፊት እንዲገፋ ትእዛዝ ተሰጠው። በመጀመሪያው እርምጃ ወታደሩ የተሰጠውን ጥንቃቄ ጠብቆ በጸጥታ ይጓዝ ነበረ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ተኳሹ ሳይታወቅ በኛ ሠራዊት መካከል ከ፰ት የማይበልጡ የጠመንጃ ተኵሶች ተሰሙ። ስለዚህ ወታደሩ ለጠብ አኰብኵቦ በሚጓዝበት ጊዜ እነዚህ ተኵሶች መሰማት አበረገገው። እንዲሁም በጠመንጃ ተኵስ ቀርቶ በማናቸውም ድንገተኛ ድምፅ ከመፎከር ሊታገሥ ልማድ የሌለው ከመሆኑ የተንሣ የሚረግጠው ሁሉ ጠላት ስለመሰለው ለተኵስ የተኵስ መልስ ይሰጥ ዘንድ ግድ ሆነበት። ስለዚህ ያለ አንዳች ምክንያት ከኛ ወገን የሚተኰሰው መሣሪያ ጠላትን አታጠቀው። እንዲሁም ከኢጣልያኖች ሰፈር ከመሐን መድፍና መትረየስ እየተሰባጠረ አልፎ አልፎ ይተኰስ ጀመር።

በሁለቱ ተዋጊዎች ግምባር የተጀመረው ተኵስ ከሰዓት ወደ ሰዓት እየሞቀና እየተጋጋለ ስለሄደ ግርማዊነታቸው ወዲያው ወደ ጦርነቱ ስፍራ

ተጓዙ። እንዲሁም ገና ወገግ እንዳለ በግራ ያለው የኢጣልያኖች ምሽግ ስለ ተለቀቀ ተኩስ በዚያ በኩል አቋረጠ። በዚያን ጊዜ ንጉሠ ነገሥቱ እንዳንድ ወታደር መትረየሱን ሲያገላብጡት ሠራዊቱ ስለተመለከተ ወኔው እየታደሰና እየጐለመሰ በመሄዱ ጦርነቱ ለያንዳንዱ ሠርጉ መሰለው።

ሁለት ሰዓት ሲሆን ፫ት ቦምብ ጣዮችና አምስት ባለመትረየስ አኤሮፕላኖች መጥተው በኛ ሠራዊት ላይ ተኰሱበት። ቀጥሎም በቁጥር ከፍ የሚሉ አኤሮፕላኖች በየሰዓቱ እየተመላለሱ መርዝ ሳይቀር ጣሉ። ይሁን እንጂ የተሰለፈው በኛ ወታደር በፊቱ ምድርን ይዞ ከቆመው ጠላቱ ጋራ ከመጋደሉ በቀር በሰማይ የሚያንዣብበውን ለመመልከት ጊዜ አላገኘም ነበር። እንዲሁም ሊነገር በማይቻል ቆራጥነት ቫል ፑስቴሪያ የሚባለውን የጠላትን ዲቢዚዮን አርገበገበው። በዚያን ጊዜ በባላምባራስ መኰሪያ መሪነት የክብር ዘበኛ የሠራው የጀብዱ ሥራ በታሪክ ገጽ የመጀመሪያውን አምድ ሊይዝ የሚገባው ነው። እንዲሁም ምክቱሉ ሹም ግራዝማች ክፍሌ እገቱ (ዛሬ ኮሎኔል) ባለ 75 መድፍ ይዞ በአይላ ፊት ለፊት ከሚገኘው ቊጥቋጦ ውስጥ ነበርና በኢጣልያ ሠፈር ላይ ባለማቋረጥ እየተኰሰ ያደረገው ጉዳት ከታሰበው በላይ ነው።

በዚህ አኳኋን የቀጠለው ጦርነት ጨለማ ስላቋረጠው ፋታ ሳይሰጥ እንደክረምት ነጐድጓድ የንጐድ የነበረው የመትረየስና የመድፍ የአኤሮፕላንና የቦምብ ድምፅ ጋብ ሲል እንግዳ ነገር መሰለ።

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ወታደሮች ከጠላት ያስለቀቁትን ምሽግ በማንም ሳይገደዱ ለቀው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ ፡ ምክንያቱም ከ፪ ቀን ጀምረው በኤውሮፕላን ምክንያት ስንቅ ካለማግኘታቸው በላይ ብዙ ቁስለኞች በውሃ ጥም ስለተሰቃዩባቸው ንው።

በዚህ ቀን በተደረገው ጦርነት ብዙዎች መኳንንቶች ሞተዋል። ብዙዎቹም ቆስለዋል።

## ምዕራፍ ፲፱።

## የጦር ሠራዊቱ መፈታት።

የእግዚአብሔር ኪነ ጥበብ ያስገኘው ስም ምንም እንኳ ከፍጥረት ሁሉ በላይ ቢሆን የሰው ኪነ ጥበብ ካስገኘው ብረት ጋራ ተጋጭቶ መሰበር እንጂ መስበር እንደማይቻል የታወቀ ነው። የሰውም ብልጫው ብረቱን በመሥራቱ እንጂ ከብረቱ ጋር በመጋጨቱ አይደለም። ስለዚህ የኢትዮጵያም ጀግና እንደርሱ ሰው ከሆነው ጠላት ጋር ለመታገል ኃይሉ ሳያንሰው ሰው ሠራሽ ከሆነው ከኤውሮፕላንና ከመርዝ ጋራ ሊዋጋ አስቦ የተነሣበትን ቆራጥነቱን ከማሳየት በቀር የመጨረሻውን ድል ለማግኘት የሚያዳግተው መሆኑን አስቀድሞ ራሱ ፈርዶታል። ይልቁንም የሠራዊቱን መበታተን በግርማዊነታቸው አጠገብ የሚገኙ ልዑላን መሣፍንትና ክብራን መኳንንት አይተው «ይህን ስፍራ ለቀን ሌላ አዲስ የጦር ሜዳ ብንከፍት ይሻላል» ሲሉ አሳብ ቢያቀርቡላቸው ግርማዊነታቸው የሰጠው መልስ ይህ ነው።

«ቀድሞውንም ከጦሩ ሜዳ ስሰለፍ ድል አደርጋለሁ በማለት ብቻ ታምኜ አይደለም ድልም ብሆን ሕይወቱ እስኪያልፍ አንድሠራ ነው እንጂ ስለዚህ ፈቃድ ያለው ከኔ ጋር ይሙት ያለዚያም የመረጠውን»

ይህ አነጋገር ከአንድ የጦር ሹም ወይም መስፍን ሳይሆን ከንጉሠ ነገሥቱ እንደበት እንደመውጣቱ መጠን በያንዳንዱ ሰሚ ላይ ከፍ ያለ ኃላፊነት ስለጣለበት እራሱን ለመሠዋት ይነፍግ ዘንድ አልቻለም። ይሁን እንጂ በሚቻለው ሁሉ የንጉሠ ነገሥቱ ሕይወት መቆጠብ የፖለቲካው ዘዴ ዋና አርእስት ነበረ። ስለዚህ ምንም እንኳ ንጉሠ ነገሥቱ መሥዋዕት መሆንን ቢመርጡ በተደረገው ጉባኤ የመሳፍንቱና የካህናቱ ድምፅህን አሳብ በመቃወም አገደው።

በዚህም ጊዜ በ፲፰፻፷ ዓ.ም በእንግሊዞችና በአፄ ቴዎድሮስ መካከል የተደረገው የመቅደላ ጦርነት ሲታሰብ የጦርነቱ ምክንያት ከማይጨው እንደማይመሳሰል ሁሉ ፡ የመሪዎቹም አስተያየት ጊዜው እንደሚያመለክተ መጠን አንድ ዓይነት ይሆን ዘንድ አግባብ አልነበረውም። ይህንንም እንደሚከተለው እንገልጻለን።

የመቅደላ ጦርነት በሁለቱም ተዋጊዎች ዘንድ ልዩ የሆነ የቤተ መንግሥት ክብር ለመጠበቅ የተደረገ ነው ስንል አንባቢዎች ዝርዝሩን ታሪክ አይዘገኑትም በማለት እንተወዋለን። የማይጨውን ጦርነት ያስነሣው ግን የአገር ነፃነት ጉዳይ ቢሆን እንጂ እንደ መቅደላው ሁሉ ልዩ የሆነ የቤተ መንግሥት ክብር መነካት አይደለም።

ስለዚህ የዓፄ ቴዎድሮስ መሥዋዕት መሆን ጦርነቱ ምክንያት ለሆነበት ለቤተ መንግሥት ክብር ሞገስ ሲሆነው ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ሕይወት ደግሞ ተስፋ ለተደረገበት ነፃነት መደገፊያ መሆን ነበረበት በማለት ብቻ ከሐተታችን ተወነን ወደቀደመው አሳብችን እንመለሳለን።

መጋቢት ፳፫ና ፳፬ በመን ላይ ውሎ ተደርጎ ይህን በመሳሰለው ሁሉ ክርክር ሲደርግ እላይ የተጠቀሰውን የግርማዊነታቸውን ቃል ከሰማው ሕዝብ እየተከፈለ ጦርነቱን ይቀጥል ነበረ። የሆነ ሆኖ ብዙውን ምሽግ ለቆ ለመሸሽ ይዘጋጅ የነበረው የጠላት ጦር በኛ ግንባር የሚደረገው ተኩስ ከቀድሞው በጣም የቀዘቀዘ መሆኑን በመገመት የለቀቀውን ስፍራ ተመልሶ እንደገና ሲይዝ ያግደው ዘንድ የቻለ የለም።

ስለዚህ መሳፍንቱና መኳንንቱ ባቀረቡት አሳብ መሠረት እኰረም ላይ ጦርነቱን ለመድገም ተስማምተው ወደ ኋላ መመለስ ጀመሩ። በዚያን ጊዜም ልዑል ራስ ሥዩም የትግሬን ሕዝብ እያሣበሩ በጠላት ላይ ከወደኋላው አደጋ ይጥሉ ዘንድ ታዘው ከዚያው ስንብት ተሰጣቸው።

በኰረም ላይ ሰፈር አድርጎ ለመዋጋት በምክር እንደተቆረጠው ሁሉ የኛ ወታደር ከተባለው ስፍራ ለመድረስ የኤውሮፕላን አደጋ ከልክሎት ዘግይቶ ነበርና ገና በጉዞ ሳለ ኮረም መጋቢት ፳፺ ቀን እሑድ በጠላት መያዙ ተሰማ።

የኛ የጦር ሠራዊት ከማይጨው ወደ ኮረም በሚመለስበት ጊዜ በቀላየ አሸንጌ አጠገብ የደረሰበትን የቦምብና የኤፐሪት አደጋ ትውልድ ሊረሳው አይችልም ይህም ከጠላት የተጣለው አደጋ ያላንዳች ጉድለት በሙሉ ሳይሳሳት የተፈጸመው በሚከተለው አኳኋን ነው። በዚያን ጊዜ የጦር ሠራዊቱ ቀኑን እያረፈ ጉዞ የሚደረገው በሌሊት ብቻ ነበርና ፍለጋውን ካለማየቱ የተነሣ የኢጣልያ አኤሮፕላኖች ሠራዊቱን ያገኘን እየመሰላቸው የጫካ ወይም የቊጥቋጦ ምልክት በሚታይበት ሁሉ ኤፐሪትና ቦምብ ሳይቆጥቡ ያዘንሙ ነበር። ነገር ግን አብዛኛውን ወዲያና ወዲህ ሲራወጡ የሚያዩዋቸው የተመረዙትና በቦምብ ድምፅ የበረገጉት የዱር አራዊት ስለሆኑ ኢጣልያኖች ሠአዊቱን ለመጨረስ እንዳመቻቸው አዲስ ብልሃት በመፍጠር ቀጥሎ የተመለከተውን ማስታወቂያ ነዙ።

«ወደ ደቡብ በሰላም ልትጓዙ ትችላላችሁ ፡ እኛ የምንፈልገው ንጉሠ ነገሥቱን ነው እንጂ እናንተን አንነካምና ሳትደብቁ በቀን ልትጓዙ ትችላላችሁ»

ኢጣልያኖች ንግግራቸውን ውነተኛ ለማስመሰልና የሠራዊቱን እምነት ለማግባባት ይህን ማስታወቂያ በጣሉበት ቀን ቦምብ ወይም ኤፐሪት ሳይጥሉ ዋሉ። ስለዚህ ያልጠረጠሩትም በገርነት ፡ የጠረጠሩትም ለማታለያ የተወሰነው ጊዜ እስከዚህ ሳይሆን አይቀርም ሲሉ በግምት ማለዳ ተነሥተው ቀን ለቀን ጉዟቸውን ቀጠሉ። እንዲሁም ቀኑን ሙሉ በሰላም ከተጓዙ በኋላ ማታውን ሰፈር አድርገው ሳሉ ንጉሠ ነገሥቱ ይህን ረቂቅ ወጥመድ ባዶውን ለማስቀረት፣ ከጥቂት ዕረፍት በኋላ የሌሊቱ ጉዞ እንዲቀጥል አስለፈፉ። በማግሥቱም ሠራዊቱ ከአውሮፕላን መበደበቁን እንዳይዘነጋ አስጠነቀቁ። ነገር ግን ረሀብና ጦር የቀጠቀጠው እንደመሆኑ መጠን ዕረፍት ለማድረግና

ጣመኑን ለማራገፍ እጅግ ከመጓጓቱ በላይ የአንድ ቀን ፋታ በመስጠት የተበተነው የኢጣልያኖች ማስታወቂያ ሊያታልለው ከመቻሉ የተነሣ ሌሊቱን ሳይንቀሳቀስ ለጥ ብሎ ዐርፎ አደረ። ስለዚህ ይህ የሌሊቱ ዕረፍት ለብዙዎቹ እስከ ወዲያኛው የዘላለም ዕረፍታቸው ሆነ።

በማግስቱ ጧት ሠራዊቱ ተነሥቶ ወደ ሰማይ ቢመለከት አንዳች አኤሮፕላን ስላላየ በኢጣልያኖች ማስታወቂያ የተነገረውን አምኖ የመዝናናት ጉዞ ጀመረ። እንዲሁም ወደ ቀላየ አሸንጌ ሊደርስ ሲቀረው፣ መጠጊያ በሌለበት ሥፍራ አርባ የሚያህሉ አኤሮፕላኖች ከወደ ሰሜን ከተፍ አሉ። እንደ ደረሱም የጉዞውን መስመር ተከትለው በየተራ የያዙትን ቦምብና ኤፐሪት በሠራዊት ላይ እንደ መዓት ካወረዱት በኋላ እነርሱ ባዷቸውን ሲመለሱ ሌልቾ ደግሞ በነርሱ ልክ ተሸከመው ተተኳቸው። የኢጣልያ አኤሮፕላኖች እንዲህ ፋታ ሳይሰጡ በፈረቃ እየተመላለሱ የጨረሱት የሕዝብ ቊጥር በጦርነቱ ላይ ከወደቀው አያንስም።

ከሞት የተረፈው ሠራዊት በቀላየ አሸንጌና በኮረም ምሥራቃዊ ደቡብ ከሚገኘው ተራራ ዋሻ አግኝቶ ዐርፎ ሳለ ያንድ ሰዓት መንገድ ያህል ራቅ ብሎ የከተማቸው ጠላት ጦር፣ ሰፈር ታየ። ስለዚህ ንጉሠ ነገሥቱ በየመንገድ የሚደርሰውን አደጋ ከመታገሥ ከዚህ ከምናየው ጠላት ጋራ ታግለን ብንሞት ይሻላል ሲሉ ለሠራዊቱ አስታወቁት። ነገር ግን ይኸው አሳብ እየተጠና ሳለ በባላገርና በሠራዊቱ መካከል ያለው አምባ ጓሮ እየበረታ ከመሄዱ በላይ ጠላት ግራና ቀኝ ለመከበብ አሰፍስፎ እንዳለ ተረጋገጠ። ስለዚህ የጠላት መሣሪያ ከሆነው ባላገር እየተከላከሉ ወደ ኋላ ተመልሶ በደሴ ላይ መዘጋጀት ይሻላል ተባለና የጉዞው አንፃር ወደ ላሊበላ እንዲሆን ታዘዘ። ምክንያቱም በቆቦ በኩል ያለውን መንገድ ለመከተል ስላልተቻለ ነው።

ባቋራጭ ሳይሆን በዘወርዋራ መንገድ፣ ያውም ቀን ሳይሆን ሌሊት የሚደረገው፣ የኛ ሠራዊት ጉዞ ቀጥታውን መንገድ ተከትሎ የሚገፋውን ጠላት ቀድሞ ለመድረስ የሚበቃ አልነበረምና ፡ የኛ ሠራዊት ገና ብዙ ኪሎ

ሜትር ወደ ኋላ ሳለ የጠላት ወታደር ቀድሞ ከደሴ መድረሱ ተሰማ። ጦርነት ያልቀመሰ አዲስ ወታደርና ለቀህ ያላስፈነጠረ ገና ከፋብሪካው የወጣ መሣሪያ በየጊዜው ከሚልክ ጠላት ጋራ በብዙ የጦር ሜዳ ከመዋሉ በላይ በቦምብ የተደበደበ፣ በኤፕሪት የተመረዘ በረሀብ የተሰበረ በጉዞው ሁሉ የባላገር ጦርነት ያልተለየው የኛ ወታደር አዲስ የጦር ሜዳ ለመከፈት የማይችል መሆኑ ተገመተና አዲስ አበባ ቀድሞ ለመድረስ ጥድፊያ ያለው እርምጃ ይሆን ዘንድ ተቈረጠ። እንዲሁም ግርማዊነታቸው በጃማና በሰላሌ በኩል አድርገው ሚያዝያ ፲፪ ቀን አዲስ አባባ ገቡ።

ግርማዊነታቸው ወደስ ሰሜን የጦር ግምባር ከሄዱ ጀምሮ የጦር ሚኒስቴር እንደራሴ ሆነው የአዲስ አበባና ያውራጃውን ጸጥታ ይጠብቁ የነበሩት ደጃዝማች ይገዙ ነበሩ። እንዲሁም እርሳቸውን በምክርና ኃይል በመሆን የሚደጉዋቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላቴን ጌታ ኅሩይ የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ዋና ዲሬክተር ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋርያትና የንግድ ሚኒስትር ዋና ዲሬክተር አቶ መኰንን ሀብተ ወልድ ነበሩ። እነዚህ ከዚህ በላይ የተመለከቱት የቤተ መንግሥት ባለ ሥልጣኖች በሰሜን ግንባር የማይጨው ጦርነት ከተደረገ በኋላ ኢጣልያኖች ድል አደረግን ፡ ንጉሠ ነገሥቱም ሞተዋል እያሉ ከሚነዙት ወሬ በቀር ፡ እርግጠኛውን ነገር ለማወቅ ካለመቻላቸው የተነሣ በጣም ተቸግረው ነበረ።

ስለዚህ የግርማዊነታቸው አዲስ አበባ በደህና መግባት ይሠጋበት ለነበረው አሳብ መጨረሻ ሆነና ወደ ፊት ለማድረግ የሚቻለውን መምከር ተጀመረ።

ከዚህ በኋላ በታላቁ ቤተ መንግሥት እየተመላለሰ በተደረገው ጉባኤ ከቀረቡት ልዩ ልዩ አሳቦች የግርማዊነታቸው ወደ ኤውሮፓ መሄድና በአጥቂው ጠላት ላይ ክስ አቅርቦ የዓለም መንግሥታትን እርዳታ መጠየቅ የተሻለ ነው የሚለው ድምፅ ብልጫ ስላገኘ ፡ ግርማዊነታቸው የሚያዝያ ፳፬

ቀን ከግርማዊት እቴጌ ፡ ከልዑል መሳፍንትና መኳንንት ጋር ወደ አውሮፓ ለመሄድ በጅቡቲ ባብር ተሣፈሩ።

እንዲሁም አምስት ዓመት ሙሉ ያላቋረጠ የፖለቲካ ጦርነት ካደረጉ በኋላ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በድል አድራጊነት ከዋና ከተማቸው ተመልሰው የአገራቸውንና የሕዝባቸውን ነፃነት እንደገና አቋቋሙ።



## ስለደራሲው በጥቂቱ

ብርሃኑ ድንቄ

## የደራሲው ሥራዎች

1. ቄሳርና አብዮት(ታሪክ)
2. አልቦ ዘመድ(ልብወለድ)
3. የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ(ታሪክ)
4. ከወልወል እስከ ማይጨው(ታሪክ)
5. A Model for World Governement(ምርምር)
6. ንግሥተ አዜብ(ተውኔት)
7. የሕፃናት ምሳሌ: እንቆቅልህ ምናውቅልህ(ወግ)
8. I Stand Alone(ፖለቲካ)
9. አረሩ(ልብወለድ)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY